# የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ደንበኞች አገልግሎት ፖሊሲና ፕሮሲጀር መመሪያ 40/2013

**ማውጫ** **ገጽ**

1.መግቢያ……………………………………………………………………………..7

1.1 አጭር ርዕስ እና አላማዎች……………………………………………………..7

1.2 የደአፖፕ ግምገማ ኮሚቴ……………………………………………………..…8

1.3 የደአፖፕ ግምገማ ባህሪያት……………………………………………………..…9

1.4 የደ.አ.ፖ.ፕ ማሻሻያ…………………………………………………………......10

1.5 በኢ.ኤ.አ ውስጥ ያሉ ማኑዋሎችን የመጠቀም ሁኔታ……………………….................11

2. ትርጓሜዎች እና ምህፃረ ቃላት……………………………………………..12

3. የአቅርቦት ሲስተም እና የተጠቃሚዎች ምድብ………………………………..21

3.1 የአቅርቦት ሲስተም……………………………………………………………….21

3.2 የአቅርቦት ምድቦች……………………………………………………………….21

3.3 ራሱን በቻለ መጋቢ መስመር የኃይል አቅርቦት………………………………….24

3.4 ፓወር ፋክተር………………………………………………………………….25

3.5 የኃይል ጭነት ማመጣጠን……………………………………………………….25

3.6 የደንበኞች የታሪፍ መደብ……………………………………………………….26

3.7 የኤሌክትሪክ አቅርቦት ክፍያዎች…………………………………………….…26

3.8 በህግ የተወሰኑ ክፍያዎች………………………………………………………..27

4. የኤሌክትሪክ አቅርቦት መመሪያ ………………………………………..28

4.1የኤሌክትሪክ አቅርቦት ግዴታዎች…………………………………………………28

4.2 የማሰራጫ መስመር ዝርጋታ ግዴታዎች……………………..……………….29

4.3 የአዲስ ኃይል አቅርቦት አጠቃላይ መመሪያ…………………………………….30

4.4 በኢ.ኤ.አ የሚደረግ ምርመራ…………………………………………………….....33

4.5 የግምት ስራ………………………………………………………….……....34

4.6 የዋና ማሰራጫ መስመሮች መዘርጋት ወይም የሰብስቴሽን ኮሚሽኒንግ ወይም የኃይል ማሻሻል ሳያስፈልግ ኃይል ስለ ማገናኘት……36

4.7 የዋና ማሰራጫ መስመሮች መዘርጋት ወይም የሰብስቴሽን ኮሚሽኒንግ ወይም የኃይል ማሻሻል ሲያስፈልግ የሚከናወን የአዲስ ኃይል አቅርቦት……37

4.8 ከአንድ በላይ ፎቅ ያላቸው ህንፃዎች፣ የተለያዩ አዳራሾች፣ በደንበኛው በተለያየ ቦታ ለሚሰሩ የማህበር ቤቶች የሚቀርብ የኤሌክትሪክ ኃይል……42

4.9 ለጊዜያዊ /Temporary/ የኃይል አቅርቦት የሚቀርብ ማመልከቻ……45

4.10 ለጊዜያዊ ኤሌክትሪክ አቅርቦት የሚዘጋጅ አስቸኳይ የአቅርቦት እቅድ……47

4.11 የተገናኘ ወይም ውል የተደረገበት የኃይል ጭነት……47

4.12 ውል የተደረገበት (የተፈቀደ) ኃይል ጭነት መጠን……47

4.13 የውል ስምምነት……48

4.14 የአቅርቦት መነሻ ቦታ……50

4.15 በኃይል አቅርቦት ቦታ ላይ የሚከናወን የኤሌክትሪክ መሳሪያዎች ተከላ……51

4.16 በተጠቃሚው ይዞታ ውስጥ የሚገኙ እቃዎች ላይ ስለሚደርስ ጉዳት……51

4.17 የኤሌክትሪክ ኃይል ጠያቂ ተጠባባቂ ደንበኞች ዝርዝር……52

4.18 የሚደነገጉ ክፍያዎች……52

4.19 የዋስትና ተቀማጭ ገንዘብ……52

4.20 የአዲስ ኃይል የማገናኘት እና የኃይል ማሻሻያ የአገልግሎት ዋጋ……54

4.21 የክፍያ ዘዴ……55

4.22 በተጠቃሚው ቅጥር ግቢ የሚከናወን የኤሌክትሪክ ሽቦ ዝርጋታ……55

4.23 የAC ሞተሮች ተከላ……56

4.24 የመስኖ/የእርሻ ፓምፕ ገጠማ……58

4.25 ከኢ.ኤ.አ የኃይል አቅርቦት ጋር በ Parallel የሚከናወን ስራ……59

4.26 ከለላ የሚደረግለት የኃይል ጭነት……59

4.27 የአገልግሎት መስመር እና መሳሪያዎችን በተመለከተ አጠቃላይ ሁኔታዎች……60

4.28 ኢ.ኤ.አ የተጠቃሚዎችን የኃይል መስመር ስለ ሚጠቀምበት ሁኔታ……63

4.29 ወደ ተጠቃሚው ቅጥር ግቢ ስለ መግባት……64

4.30 የተለየ የደህንነት ጥበቃ ለሚደረግላቸው ድርጅቶች ወይም ተጠቃሚዎች……………….64
4.31 በኢ.ኤ.አ የተፈቀደለት ሰራተኛ………………………………………………………...64
4.32 ማንኛውም በኢ.ኤ.አ ውክልና የተሰጠው ሰራተኛ……………………………………..65
4.33 የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን የማቋረጥ ፕሮሲጀር………………………………….65
4.34 በጊዜአዊነት የኤሌክትሪክ ኃይል ማቋረጥ…………………………………………….66
4.35 የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን በቋሚነት ማቋረጥ……………………………………..68
4.36 የኤሌክትሪክ ኃይል መልሶ የመቀጠል ፕሮሲጀር……………………………………..68
4.37 በጊዚያዊነት የተቋረጠውን ኤሌክትሪክ ስለ መቀጠል……………………………….....69
4.38 የተሰጠ የኃይል ጭነት ቅነሳ…………………………………………………………….70
4.39 የመንገድ መብራት የኃይል አገልግሎት ማሻሻያ ፕሮሲጀር………………………………71
4.40 ከመንገድ መገልገያ መብራት ውጪ የሚቀርብ የኃይል ጭነት ማሻሻያዎች……………..72
4.41 ስም ማዘዋወርና ታሪፍ መቀየር……………………………………………………….73
4.42 በደንበኞች ይዞታ ውስጥ የመስመር፣ ቆጣሪ እና ተዛማጅ እቃዎች ማዛወሪያ ፕሮሲጀር…75
4.43 የኃይል አቅርቦት ቦታን የማዛወር ፕሮሲጀር…………………………………………..76
4.44 በደንበኛው የሚከናወን የኃይል ሽያጭ………………………………………………….77
4.45 በፍራንቻይዝ (በውክልና) አማካኝነት የኤሌክትሪክ ኃይል ስርጭት አገልግሎት………….78
4.46 የፍርድ ቤት የዕዳ ክስ ሂደትና ሌሎች ጉዳዮች ባሉበት ሁኔታ የኤሌክትሪክ ኃይል ማገናኘት……………………………………………………………………………...80

**5. የቆጣሪዎች አቅርቦት መመሪያ……………………………………………80**

5.1 የኢ.ኤ.አ የቆጣሪዎች አቅርቦት ግዴታ…………………………………………………....80

5.2 የቆጣሪዎች ዓይነት……………………………………………………………………80

5.3 የቆጣሪዎች፣ ሚኒአቸር ሰርኪውት ብሬከር /ሰርኪውት ብሬከር (MCB/CB) አቅርቦትና ተከላ…………………………………………………………………………………….82

5.4 የቆጣሪዎች ባለቤትነት እና አጠቃቀም……………………………………………………83

5.5 ቆጣሪዎችን መፈተሽ……………………………………………………………….84

5.6 የተበላሹ ቆጣሪዎች………………………………………………………………85

5.7 የቆሙ ቆጣሪዎች MDI ያላቸውን ጨምሮ………………………………………...87

5.8 የተቃጠሉ ቆጣሪዎች……………………………………………………………..88

5.9 የተበላሹ/የተቃጠሉ ቆጣሪዎች መተኪያ ወጪ……………………………………...88

5.10 የጠፉ ቆጣሪዎች (አድራሻቸው ያልተገኙ)……………………………………….89

6. የኃይል ፍጆታ ስሌት……………………………………………………………90

6.1 አጠቃላይ ዝርዝር ሁኔታዎች……………………………………………………90

6.2 የግምታዊ የቆጣሪ ፍጆታ ሂሳብ (estimation) የቢል ዝግጅት……………………………92

6.3 የቦታ ይዞታ ለውጥ (ባለ ይዞታው ለቆ ሲሄድ) በቆጣሪዎች ላይ የሚከናወን ልዩ ንባብ…..93

6.4 ቅድሚያ የሚከፈል የኤሌክትሪክ ፍጆታ ሂሳብ………………………………………93

6.5 ክርክር የሚነሳባቸው ቢሎችና ውዝፍ ሂሳቦች………………………………………..94

6.6 በደንበኛ የሚዘጋጅ የክፍያ ቢል…………………………………………………95

6.7 የዘገዩ ክፍያዎች ቅጣት……………………………………………………………95

6.8 ያልተፈቀደ ኤሌክትሪክ ስለ መጠቀም…………………………………………………95

6.9 ከተፈቀደው የኃይል ጭነት በላይ በሚኖርበት ጊዜ……………………………………99

6.10 የክፍያ ስርዓት……………………………………………………………………99

6.11 ደረሰኝ……………………………………………………………………………100

6.12 የተሰበሰበውን ገንዘብ ማወራረድ………………………………………………………….101

6.13 ተመላሽና ለዘገዩ ክፍያዎች ቅጣት……………………………………………………….101

6.14 ክፍያን በጊዜ ገደብ ከፋፍሎ መክፈል (installment payment)…………………………101

6.15 ቀሪ ክፍያዎችን መሰብሰብ…………………………………………………………………102

7. የስራ አፈፃፀም የጥራት ደረጃ፣ የቅሬታ መስተንግዶ እና የካሳ ክፍያ……….103

7.1 አጠቃላይ መመሪያ……………………………………………………………………………..103

7.2 የስራ አፈፃፀም የጥራት ደረጃ……………………………………………………………….105

7.3 የደንበኛ ቅሬታ አያያዝና መስተንግዶ………………………………………………………...119

7.4 ግምገማና ውሳኔ…………………………………………………………………………………120

7.5 የስራ አፈፃፀም የጥራት ደረጃን የተመለከተ መረጃ………………………………………..120

8. የኤሌክትሪክ አውታር፣ቆጣሪዎች ወዘተ በመነካካት፣ ማጭበርበር፣ ማበላሸት ወይም ስርቆት መፈጸም…………………………………………………….121

8.1 በኤሌክትሪክ ተጠቃሚዎች የተፈጸመ የኃይል ስርቆት ጉዳይ አያያዝና አመዘጋገብ…….126

8.2 የተከሰቱ ወይም ሪፖርት የቀረበባቸው አቤቱታዎች ስለመስማት…………………………127

8.3 ውሳኔ የተሰጠበትን ክፍያ ወይም በጊዜ ገደብ የተሰጡ እዳዎች አለመክፈል…………….128

8.4 የማጭበርበር ተግባር የተከናወነባቸውን ቆጣሪዎች በፈቃደኝነት ስለማሳወቅ…………….129

8.5 ማጠቃለያ……………………………………………………………………………………..129

9. አጠቃላይ ዝርዝር ሁኔታዎች……………………………………………………..130

9.1 ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች እና የኃይል አቅርቦት ላይ የተጣሉ ገደቦች………………..130

9.2 የኤሌክትሪክ ኃይልን በአግባቡ ስለመያዝ………………………………………………….130

9.3 ማስታወቂያዎችን ስለ መስጠት........................................................................131

9.4 አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የማስወገድ ስልጣን.....................................................131

9.5 ልዩ ልዩ...................................................................................................132

10. አባሪዎች...............................................................................133

# 1. መግቢያ

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 303/2006 እና በደብዳቤ ቁጥር 68.17/06/06 ታህሳስ 23 ቀን 2006 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን እና በመንግስት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1992 መሰረት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፤ ከቀደሙ ህትመቶች በኋላ በ2011ዓ/ም ከክልሎች አደረጃጀት ጋር አብሮ ሊሄድ የሚችል እና ያልተማከለ አሰራርን ለማስፈን፣ እንዲሁም ከዚህ በፊት በአሰራር ላይ ይታዩ የነበሩ ማነቆዎች እና ክፍተቶችን ለመሙላት የሚከተለውን የደንበኞች አገልግሎት ፖሊሲ እና ፕሮሲጀር/ የደአፖፕ/ማሻሻያ አድርጎ አውጥቷል፡፡

## 1.1 አጭር ርዕስ እና አላማዎች

የደንበኞች አገልግሎት ፖሊሲ እና ፕሮሲጀር 2011 ከዚህ በኋላ (ደ.አ.ፖ.ፕ) ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ለሁሉም የኢ.ኤ.አ የስራ ክፍሎች በሚመለከታቸው ቦታና ለሁሉም ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የኤልክትሪክ ተጠቃሚዎች፤ በኢ.ኤ.አ/የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት የተገለጸው አላማ ማስታወቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

የኢ.ኤ.አ ግዴታዎች እና የደንበኞች ግዴታ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን ምርጥ ተሞክሮ በመከተል ፣ ውጤታማ ፣ ግልጽ ፣ ወጪ ቆጣቢ እንዲሁም ምቹ የሆነ አገልግሎት ለደንበኞች ለመስጠት ግዴታቸውን ያስቀምጣል፡፡ ሰነዱም የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

ሀ. የአዲስ ኃይል ማገናኘት ፣ የኃይል ማሻሻያ ወይም የኃይል ፍላጎት መቀነስ ፕሮሲጀር

ለ. ያልተሰበሰበ የፍጆታ ሂሳብ ገንዘብ ስብሰባና የቢል ዝግጅት ወቅት ፕሮሲጀር

ሐ. የቆረጣ ቅጠላና ኃይል መልሶ ማገናኘት ፕሮሲጀር

መ. በኤሌክትሪክ አውታሮች ፣ ቆጣሪዎችና መስመሮች ላይ ያለአግባብ መነካካት እና ጉዳት ማድረስ ፕሮሲጀር

ሠ. የሚመለከተው የድርጅቱ ሰራተኛ ወደ ደንበኞች ይዞታ ለመግባትና ኃይል ለማቋረጥ ፣ ቆጣሪ ለማንሳት ፣ ለጥገና ፣ ቆጣሪ ለመለወጥ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

ረ. የፍጆታ ክፍያ የቆጣሪ ተከላና የኃይል አጠቃቀም ጥናት ትግበራዎች

ሰ. ለኢ.ኤ.አ የአፈጻጸም ደረጃዎች

ሸ. የደንበኞች ቅሬታ አፈታት ፕሮሲጀር

**1.2 የደ.አ.ፖ.ፕ ግምገማ ኮሚቴ**

የኢ.ኤ.አ የደአፖፕ ግምገማ ኮሚቴ ያቋቁማል፤ ኮሚቴው የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ሲኖርበት ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡

1. ከኢ.ኤ.አ ከደንበኞች ተጠቃሚዎችና እንዲሁም ሌሎች ፍላጎት ያላቸው አካላት ስለ ደንበኞች አገልግሎት ፖሊሲና ፕሮሲጀር ትግበራ አስተያየትና ሀሳብ መውሰድና ከግምት ውስጥ ማስገባት፤
2. በኃይል አቅርቦት ሁኔታዎች፣ በደንበኞች መብት ጥበቃ እንዲሁም ከአጠቃላይ የድርጅቱ አፈጻጸም አንጻር የተሟላ መሆኑን መገምገምና በደአፖፕ ላይ ማሻሻያና ለውጥ ሲያስፈልግ የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብ፤
3. በደንበኞች አገልግሎት ፖሊሲና ፕሮሲጀር ትግበራ ላይ ያጋጠሙ የስራ ላይ ችግሮችን መገምገም፤

ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፣

**ሰብሳቢው፡-** ከኮርፖሬት ዲስትሪቢዩሽን ሲስተም ቴክኒካል እና ደንበኞች አገልግሎት ዳሬክቶሬት

**የአባላት ስብጥር በተመለከተ፡-**

1. ከቪ.ጅላንስ ቢሮ 1 ተወካይ
2. ከኮርፖሬት ህግ ክፍል 1 ተወካይ
3. ከኮርፖሬት ኦዲት 1 ተወካይ
4. ከኮርፖሬት ፋይናስ 1 ተወካይ
5. ከኮርፖሬት ሰብትራንስሚሽን (45 እና 66 ኪ.ቮ) 1 ተወካይና
6. ከ 11 ሪጅኖች የተመረጡ 5 ተወካዮች
7. ከኢነርጂ ማኔጅመንት እና አውቶሜሽን የስራ ክፍል 1 ተወካይ
8. ከ11 ሪጅኖች የተሻለ ልምድ እና አፈጻጸም ያላቸው 2 የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ኃላፊዎች
9. በመንግስት የተሰየሙ ከደንበኛ ተወካዮች (ከነዚህ ውስጥ ሶስቱ ከዝቅተኛ ኃይል ተጠቃሚዎች ሁለቱ ከከፍተኛና በጣም ከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚዎች ፣ አንድ ፤ አንድ ተወካይ ከከተማና ከገጠር ኃይል ተጠቃሚዎች፡፡ ከተወካዮቹ ቢያንስ ሁለቱ ከመኖሪያ አገልግሎት ተጠቃሚዎች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
10. ከደንበኛ ፎረም/ከሸማቾች ማህበር 1 ተወካይ
11. ሌሎች ማንኛውም አባል በሰብሳቢዉ ሲመረጥ የሚሳተፍ ይሆናል፤ እንዲሁም የኮሚቴው ጸሀፊ በሰብሳቢው የሚሰየም ይሆናል፡፡ ከፍተኛው የአባላት ቁጥር 21 ሲሆን ግማሽ የሚሆኑት አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ እንደተሟላ ተቆጥሮ ስብሰባ ማድረግ ይቻላል፡፡

**1.3 የደአፖፕ ግምገማ ባህሪያት**

1. ኢ.ኤ.አ ደንበኞች ወይም ሌሎች ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦች በደአፖፕ ላይ ለውጥ እንዲደረግ ሲፈልጉ ያላቸውን ፕሮፖዛል በጽሁፍ ለኮሚቴው ፀሀፊ በአንድ ሶፍት ኮፒ እና የተፈረመ የጽሁፍ ሰነድ ለውጡ ያስፈለገበትን ምክንያቶች እና ያሉትን ሁኔታዎች በመጥቀስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

2. የኮሚቴው ጸሀፊ ተገቢ የሆኑ አስተያየቶችን ማዘጋጀትና ከስብሰባው ቀን በፊት ለኮሚቴው አባላት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ፀሀፊው በአባላት ስብሰባ ወቅት የተነሱትን አስተያየቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት አስፈላጊ ከሆነ አስተያየት ያቀረበውን ግለሰብ በመጋበዝ ቀርቦ ለውጥ ያስፈለገበትን ጉዳይ እንዲያሰማ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3. ኮሚቴው በአባላት የቀረቡትን አስተያየቶችና ሀሳቦች ከግምት ውስጥ በማስገባት ተያያዥ ጉዳዮችን ለማጥናት ንዑስ ኮሚቴ ሊመሰርት ይችላል፡፡

4. ኮሚቴው የቀረቡትን የደአፖፕ ማሻሻያ ሀሳቦች በማጠቃለል ለኢ.ኤ.አ ከፍተኛ ማኔጅመንት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

5. የኢ.ኤ.አ ከፍተኛ ማኔጅመንት የቀረቡ የማሻሻያ ሀሳቦችን (በደአፖፕ አንቀጽ 1.4 መሰረት) እንዳሉ ወይም የተወሰነ ለውጥ አድርጎ ያጸድቃል፤ ለማኔጅመንት ቦርድም ያሳውቃል፡፡

6. የኢ.ኤ.አ ለደአፖፕ ግብዓት ከደንበኞች ለማግኘት የውይይት ፎረሞችን ወይም የጽሁፍ ግብረ መልስ ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡

### 1.4 የደ.አ.ፖ.ፕ ማሻሻያ

1. የኢ.ኤ.አ የደ.አ.ፖ.ፕ አስተያየቶችን በራሱ ወይም በኮሚቴው አስተያየቶች መሰረት ሊያሻሽል ይችላል፡፡ ነገር ግን ማንኛውንም አይነት የደአፖፕ ማሻሻያ ከመደረጉ በፊት በቀረቡ የለውጥ ሀሳቦች ላይ ከሁሉም የስራ ክፍሎችና ከህዝቡ አስተያየት መወሰድ ይኖርበታል፡፡

2. ማንኛውም በደ.አ.ፖ.ፕ ላይ የሚደረግ ለውጥ በኢ.ኤ.አ እና በሚኒስትር መ/ቤቱ ድህረ-ገጽ ላይ መስፈር ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ለውጥ የተደረገባቸውን ዝርዝር ጉዳዮች

በአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ዘንድ ሰፊ ስርጭት ባላቸው ቢያንስ በሁለት ጋዜጦች ላይ ታትሞ እንዲወጣ መደረግ አለበት፡፡ ቅጅዎች በሁሉም የድርጅቱ የስራ ክፍሎች ይቀመጣሉ፡፡

### 1.5 በኢ.ኤ.አ ውስጥ ያሉ ማኑዋሎችን የመጠቀም ሁኔታ

የኢኤአ በደንበኞች አገልግሎት ፖሊሲና ፕሮሲጀር ባልተገለጹ ጉዳዮች ላይ ከደአፖፕ እና ከሌሎች አዋጆች ጋር ባልተቃረነ መልኩ የራሱን ደንብና መመሪያዎች ሊያጣቅስ ይችላል፡፡

## 2 . ትርጓሜዎች እና ምህፃረ ቃላት

| | |
|---|---|
| አ(A) | አምፒር |
| ኤች.ፒ(HP) | ሆርስ ፓወር (የፈረስ ጉልበት) |
| ሲ.ቢ(CB) | ሰርኪውት ብሬከር |
| ደ.አ.ፖ.ፕ(CSPP) | የደንበኞች አገልግሎት ፖሊሲ እና ፕሮሲጀር |
| ሲ.ቲ(CT) | ከረንት ትራንስፎርመር |
| ኢ.ኤ.አ.ደ.አ.ፖ.ፕ(EE U/CSPP) | ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ደንበኞች አገልግሎት ፖሊሲና ፕሮሲጀር |
| ጂ.አይ.ኤስ(GIS) | ጂኦግራፊካል የመረጃ ስርዓት |
| ጂ.ፒኤ.ስ(GPS) | ግሎባል ፖዚሽን ሲስተም |

| | |
|---|---|
| የከ.ቮ.ማ.ሲ(HVDS) | የከፍተኛ ቮልቴጅ ማከፋፈያ ሲስተም |
| ኪ.አ(KA) | ኪሎ አምፒር |
| ኪ.ቮ(KV) | ኪሎ ቮልት |
| ኪ.ቮ.አ(KVA) | ኪሎ ቮልት አምፒር |
| ኪ.ቮ.አ.ሰ(KVAH) | ኪሎ ቮልት አምፒር ሰዓት |
| ኪ.ቮ.አ.ሪ(KVAR) | ኪሎ ቮልት አምፒር ሪአክቲቭ |
| ኪ.ቮ.አ.ሪ.ሰ(KVARH) | ኪሎ ቮልት አምፒር ሪአክቲቭ ሰዓት |
| ኪ.ዋ(KW) | ኪሎ ዋት |
| ኪ.ዋ.ሰ(KWH) | ኪሎ ዋት ሰዓት |
| ኤል.ኢ.ሲ(LEC) | የተፈቀደ / ፈቃድ ያለው ኤሌክትሪካል ስራ ተቋራጭ |
| ኤም.ሲ.ቢ(MCB) | የሚናቸር ሰርኪውት ማቋረጫ |
| ኤም.አይ.ኤስ(MIS) | የአመራር መረጃ ስርዓት |
| ፒ.ቲ(PT) | ፖቴንሻል ትራንስፎርመር |
| ኤስ.ሲ.ኤ.ዲ.ኤ(SCADA) | የቁጥጥር እና መረጃ አቅርቦት ሲስተም |
| ኤስ.ደብልዩ.ጂ(SWG) | እስታንዳርድ የሽቦ ጌጅ |
| ቪ.(V) | ቮልት |
| ዋ(W) | ዋት |
| ዝ.መ(LV) | ዝቅተኛ መስመር |
| መ.መ(MV) | መካከለኛ መስመር |
| ከ.መ(HV) | ከፍተኛ መስመር |
| በከ.መ(EHV) | በጣም ከፍተኛ መስመር |
| ኤል.ዲ.ሲ(ELDC) | የኢትዮጵያ ሎድ ዲስፓች ሴንተር |

**ትርጓሜዎች**

2.1 በዚህ የደአፖፕ ላይ የተገለጹ ቃላት ዝርዝሮችና አገላለጾች ትርጉም ከኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 ጋር ተመሳሳይ ትርጓሜ ይኖራቸዋል፡፡

በዚህ ደ.አ.ፖ.ፕ ላይ ያሉ አገላለጾች በማንኛውም አዋጅ ወይም በፓርላማ የጸደቁ ህጎች ውስጥ ከሌሉ ከ2011 ዓ.ም በፊት በነበረው የኤሌክትሪክ ኃይል አቅራቢ ድርጅት ትርጓሜ መሰረት ይሆናል፡፡

2.2 በዚህ ደአፖፕ ውስጥ ከነባራዊ ሁኔታ አንጻር አፍራሽ ካልሆነ በስተቀር የሚከተሉት ቃላትና አገላለዖች ተመሣሣይ ትርጓሜ ይኖራቸዋል፡፡

1. **“ስምምነት ”** ማለት በኢ.ኤ.አ እና በደንበኞች በዚህ ደ.አ.ፖ.ፕ መሰረት የሚፈፀም ውል ነው፡፡
2. **“መገልገያ መሳሪያዎች”** ማለት የኤሌክትሪክ መሳሪያዎችና ማሽኖች፣ ተገጣሚዎች እንዲሁም ተያያዥ ቁሳቁሶች ሲሆኑ ለኤሌክትሪክ ማስተላለፊያነት የምንጠቀምባቸው ማለት ነው፡፡
3. **“አመልካች”** ማለት ማንኛውም ህጋዊ የሆነ ይዞታ ያለው ወይም ህጋዊ ውክልና በባለቤቱ የተሰጠው ወይም በቦታው ነዋሪነቱን የሚያረጋግጥ ሶስት ምስክሮችን ማቅረብ የሚችል እና የኤሌክትሪክ ኃይል ጥያቄ ለማግኘት ወይም ማመልከት የሚፈልግ ማለት ነው፡፡
4. **“የአቅርቦት ክልል”** ማለት ኢ.ኤ.አ የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲያቀርብ በመንግስት ስልጣን የተሰጠው ክልል ማለት ነው፡፡
5. **“መርማሪ ኦፊሰር”** ማለት በኢ.ኤ.አ የሚመደብ ባለሙያ ማለት ነው፡፡
6. **“ስልጣን የተሰጠው ኦፊሰር”** ማለት በመንግስት የሚወከል መርማሪ ይሆናል፡፡
7. **“ቅሬታ ሰሚ ባለስልጣን”** ማለት በመንግስት የተወከለ ባለስልጣን ሲሆን በገምጋሚ ኦፊሰሩ ላይ የቀረቡ ቅሬታዎችን የሚሰማ ባለስልጣን ነው፡፡
8. **“የቢል ዝግጅት ጊዜ ወይም ወቅት”** ማለት ለኢ.ኤ.አ የተለያየ ደንበኛ መደቦች ቢል የሚዘጋጅበት ወቅት ነው፡፡
9. **“የኤሌክትሪክ መቋረጥ”** ማለት በመሳሪያዎች ላይ በሚፈጠር ብልሽት ምክንያት በሃይል አቅርቦት ሲስተምና ኤሌክትሪክ መስመሮች ላይ የኤሌክትሪክ መቋረጥ ክስተት ነው፡፡
10. **“የቢዝነስ ደንብ”** በየጊዜው የሚሻሻሉ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ደንቦች ማለት ነው፡፡
11. **“የቀን መቁጠሪያ አመት”** ማለት በያንዳንዱ አመት የመስከረም መጀመሪያው ቀን ጀምሮ በዚሁ አመት ጳጉሜ መጨረሻው ቀን የሚያልቀው የአመቱ ቀናት ይሆናል፡፡
12. “**ደአፖፕ**” ማለት የደንበኞች አገልግሎት ፖሊሲ እና ፕሮሲጀር ማለት ሲሆን የኢ.ኤ.አ ደንበኞች የሚስተናገዱበት ደንብ እና መመሪያ ነው፡፡
13. **“የኤሌክትሪክ አቅርቦት ክልል”** ማለት የኤሌክትሪክ አቅርቦት የደረሰባቸው አካባቢዎች ማለት ነው፡፡

14.“**ኢ.ኤ.አ**” ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 303/2006 የተቋቋመ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ነው፡፡

15.“**ኤሌክትሪክ አስተላላፊ**” ማለት ማንኛውም (ያልተሸፈነ፣ ሽፍን፣ ጠፍጣፋ፣ መሀሉ ክፍት የሆነ፣ ዝርግ) ሽቦ ሆኖ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያስተላልፍ ማለት ነው፡፡

16.“**የተገናኘ ጭነት**” ማለት አጠቃላይ ደንበኛው የሚጠቀምባቸው ኃይል የሚወስዱ መሳሪያዎች የሚወስዱት የኃይል መጠን ልኬት በተገለጸው መሰረት ሲሆን በአምራቾች የተገለጸ ልኬት ከሌላቸው ኢ.ኤ.አ ትክክለኛ የሚሸከሙትን ጭነት ለመለካት በተመሳሳይ ጊዜ ሁሉም መሳሪዎች የሚጠቀሙትን የኃይል መጠን መለካት ይኖርበታል፡፡ ይህም በኪዋ፣ በኪቮአ ወይም በፈረስ ጉልበት ሊለካ ይችላል፡፡ በአባሪ ቁጥር 4.6 መሰረት መለካት ይኖርበታል፡፡

17.“**ደንበኛ**” ማለት ማንኛውም ግለሰብ፣ ድርጅት፣ የእምነት ተቋም፣ መንግስታዊ ተቋም፣ ለራሱ ጥቅም በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ከኢ.ኤ.አ ውል ፈጽሞ የኤልክትሪክ አቅርቦት ያገኘ ሲሆን በተጨማሪም በሚመለከተው አካል ኤሌክትሪክ በጊዜያዊነት የተቋረጠበትን ያካትታል፡፡

18.“**የተጠቃሚ ቅሬታ ፎረም**” ማለት በደአፖፕ 2011 መሰረት የሚመሰረት ፎረም ነው፡፡

19.“**የደንበኞች መስመር ዝርጋታ**” ማለት ሁሉንም አጠቃላይ ኤሌክትሪክ መስመር ሽቦዎች እና ተዛማጅ እቃዎች፣ ትራንስፎርመሮች እና ተዛማጅ እቃዎች በደንበኛው በራሱ ወይም ሌላ ህጋዊ ተወካይ በአንድ ወይም ተመሳሳይ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከአቅርቦት መነሻ ጀምሮ ያለውን ዝርጋታ የሚያካትት ነው፡፡

20.“**ውል የተደረገበት ጭነት**” ማለት ከፍተኛው የኤሌክትሪክ ጭነት በኪሎ ዋት፣ ኪሎ ቮልት አምፒር ወይም በፈረስ ጉልበት በኢ.ኤ.አ ለአቅርቦት ስምምነት የተደረገበት ሆኖ ከተገናኘ ጭነት የተለየ ሊሆን የሚችል ሲሆን በተዋዋይ ወገኖች መካከል ስምምነቱ የሚንፀባረቅበት ነው፡፡ ይህም ወደ ቀጣዩ ከፍተኛ ቁጥር ሊጠጋጋ የሚችል ነው፡፡ ”የተፈቀደ ጭነት” (ውል የተደረገበት ጭነት) የሚለውን ቃል በተመሳሳይ ትርጉም መጠቀም ይቻላል፡፡

21.“**የአቅርቦት መጀመሪያ ቀን**” ማለት ኢ.ኤ.አ ለደንበኛው የአገልግሎት መስመር ዝርጋታ ከዋናው ማከፋፈያ መነሻ ኃይል ያገናኘበት ቀን ነው፡፡

22.“**የኃይል ፍላጎት ክፍያ**” ማለት ደንበኛው ውል ለተደረገበት ጭነት ወይም የተጠየቀ ከፍተኛ ፍላጎት በኢ.ኤ.አ የታሪፍ ደንብ መሰረት የሚፈፀም ሲሆን፣ ይህም የፍላጎት ክፍያ ሌላ የታሪፍ ደንቦች ካሉ በዚሁ መሰረት ይሰላል፡፡

23.“**ዋና የማሰራጫ መስመሮች**” ማለት ማንኛውም የዋና መስመር አካል ሆኖ የአገልግሎት መስመር የተገናኘበት ወይም ሊገናኝበት የሚችል ዋና መስመር ማለት ነው፡፡

24.“**የማሰራጫ ሲስተም**” በኤሌክትሪክ ሽቦዎችና በተያያዥ መሳሪያዎች የተገነባ ሆኖ ከኃይል ማስተላለፊያ ወይም ከኃይል ማመንጫ እስከ ደንበኞች ማገናኛ መነሻ ያለው አጠቃላይ ዝርጋታ ነው፡፡

25.“**የድንገተኛ ማቋረጫ**” ማለት በአጭር ማስታዎሻ ወይም ያለ ማስታዎሻ ለሰዎች እና ለመሳሪያ ደህንነት ሲባል ኃይል የሚቋረጥበት ሁኔታ ነው፡፡

26.“**የኃይል ፍጆታ ክፍያ**” ማለት በደንበኛ ላይ ላለው የኤሌክትሪክ አቅርቦት በኢ.ኢ.ባ ወይም መንግስት በታዘዘ ታሪፍ መሰረት የሚጣል ክፍያ ነው፡፡

27.“**ኢ.ኢ.ባ**” ማለት የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 308/2006 የተቋቋመ ባለስልጣን ነው፡፡

28.“**በጣም ከፍተኛ መስመር**(በከመ)” ማለት 132 ኪሎ ቮልት እና ከዚያ በላይ የሆነ መጠን ሆኖ እንደ ሁኔታው በደአፖፕ መሰረት በሚፈቀዱ መቶኛ ልዩነቶች ሊለዋወጥ ይችላል፡፡

29.“**በጀት አመት**” ማለት ባለው አመት ሀምሌ 1 ቀን ጀምሮ በቀጣዩ አመት ሰኔ 30 የሚያበቃው አመት ይሆናል፡፡

30.“**መጋቢ መስመር**” ማለት (መ.መ)፣ (ከ.መ) ወይም (በከ.መ) አከፋፋይ፣ ከሰብስቴሽን የሚነሳ ሆኖ ማሰራጫ ሰብስቴሽኖች፣ (መ.መ)፣ (ከ.መ) እና (በከ.መ) ተጠቃሚ ደንበኞች የሚገናኙበት መስመር ማለት ነው፡፡

31.“**ቋሚ ክፍያዎች**” ማለት ባለው የታሪፍ ትእዛዝ ደንቦች መሰረት ተፈፃሚ የሚሆን ነው፡፡

32.“**ከፍተኛ መስመር**” ማለት ከ33 ኪሎ ቮልት እስከ 66 ኪሎቮልት ድረስ ያለ ሆኖ ይህም በደ.አ.ፖ.ፕ መሰረት እንደ ሁኔታው የመቶኛ ለውጥ ሊኖረው ይችላል፡፡

33.“**ራሱን የቻለ መጋቢ መስመር**” ማለት ከግሪድ ሰብስቴሽን የሚነሳ ሆኖ ይህም ለአንድ ተጠቃሚ የኤሌክትሪክ አቅርቦት የሚሰጥ ወይም ለደንበኞች ቡድን ለተመሳሳይ ስራ በተከታታይ መስመር የሚያቀርብ ነው፡፡

34.“**የጭነት ፋክተር**” ማለት በተወሰነ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ ሃይል (በኪ.ዋ.ሰ ወይም ኪ.ቮ.አ.ሰ ) ለጠቅላላ የተፈቀደው ሃይል (በኪ.ዋ ወይም ኪ.ቮ.አ) ሲካፈል የሚገኝ ሲሆን በተመሳሳይ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለው ሃይል ከተፈቀደው ሃይል መብለጥ የለበትም፡፡የዚህ ክፍልፋይ ውጤት በመቶኛ የሚገለጽ ነው፡፡

35.“**የጭነት ፋክተር በመቶኛ**” ማለት በተወሰነ ወቅት ጥቅም ላይ የዋሉ ዩኒቶች (ኪሎ ዋት ሰዓት ወይም ኪሎ ቮልት በሰዓት)*100/ከፍተኛው ጭነት ኪሎ ዋት ወይም ኪሎ ቮልት አምፒር (X) በቁጥር የሰአቶች ብዛት አቅርቦት የተፈጸመበት በመጋቢ መስመር ላይ በሚኖረው ጊዜ መሰረት የሚለካ ነው፡፡

36.“**ዝቅተኛ መስመር (ዝ.መ)**” ማለት ከ230 ቮልት የማይበልጥ ሲሆን ይህም በፌዝ እና በኒውትራል ወይም 400 ቮልት መካከል ሆኖ ማንኛቸውም ሁለት ፌዞች በተለመደው ሁኔታ በደአፖፕ መሰረት የሚለዋወጥ መቶኛ ይሆናሉ፡፡

37.“**መካከለኛ መስመር**” ማለት ከ400ቮልት በላይ ሆኖ እስከ 15 ኪሎ ቮልት በተለመደው ሁኔታ በደአፖፕ መሰረት የሚለዋወጥ መቶኛ ይሆናል፡፡

38.“**ከፍተኛ አጠቃቀም**” ማለት አማካኝ የኪሎዋት ወይም የኪሎ ቮልት አምፒር (እንደአስፈላጊነቱ) ሆኖ ከተጠቃሚው ሃይል አቅርቦት መነሻ ጀምሮ በቢል ዝግጅት ወቅት በየ30 ደቂቃ(ለባቡር መስመር ከሆነ 15 ደቂቃ) የሚመዘገብ ከፍተኛ አጠቃቀም ሲሆን በኢኤአ ይህን ጊዜ ለልዩ የተጠቃሚዎች ክፍል የማሳጠር መብት ተጠብቆ አስፈላጊ ከሆነ በመንግስት/ኢ.ኢ.ባ በታሪፍ ማፅደቂያ ሂደት ተፈፃሚ የሚሆን ይሆናል፡፡

39.“**ቆጣሪ**” ማለት የኤሌክትሪክ አቅርቦት መጠን እንደ ኃይል በኪሎ ዋት ሰዓት እና/ወይም ኪሎ ቮልት አምፒር ሰዓት የሚለካ መሳሪያ ሲሆን ከፍተኛው አቅርቦት በኪሎዋት እና/ወይም ኪሎ ቮልት አምፒር፣ ሪአክቲቭ ኃይል ኪሎ ቮልት አምፒር ሪአክቲቭ ሰዓት ወዘተ የሚለካ መሳሪያ ነው፡፡ ይህም ተያያዥ ቁሳቁሶች እንደ ከረንት ትራንስፎርመሮች (ሲ.ቲ) ፖቴንሺያል ትራንስፎርመሮች (ፒ.ቲ) የሚያካትት ሲሆን ከዚህ ቆጣሪ ጋር ተያይዘው ጥቅም ላይ ሲውሉ የዚህን አይነቱን ቆጣሪ ወይም ተያያዥ

ቁሳቁሶች ለመግጠም ወይም ለመሸፈን ጥቅም ላይ የሚውል እና ማንኛውም መሳሪያ እንደ ማብሪያ ማጥፊያ ወይም አውቶማቲክ ወይም ፊውዝ ለደህንነት ወይም ምርመራ አላማ የሚውል ያካትታል፡፡ በተጨማሪም በኢ.ኤ.አ የሚቀርብ ማንኛውም ቆጠሪ ማሸግና ያልተፈቀደ የኤሌክትሪክ አጠቃቀም እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ ይህም የቅድመ ክፍያ ቆጣሪዎችን ያካትታል፡፡

40. **"ባለቤት"** ማለት የኃይል አቅርቦት ጥቅም ላይ የዋለበት ወይም ጥቅም ላይ እንዲውል የታሰበበት ቅጥር ግቢ ባለቤት ወይም እንዲጠቀም ፍቃድ ያለው ግለሰብ ነው፡፡

41.**"በምዕራፍ የተከፋፋለ የኃይል ፍላጎት"** ማለት ምእራፍ ባለው መልኩ ተፈጻሚ የሚሆን የፍላጎት ውል ማለት ነው፡፡

42.**"የአቅርቦት መነሻ"** ማለት ከቆጣሪ ወጪ ሆኖ ወደ ደንበኛው ይዞታ የሚገባ በዝቅተኛ መስመር ሆኖ በከፍተኛና በጣም ከፍተኛ መስመሮች ጊዜ ከደንበኞች መሳሪያዎች በፊት ያለ የመስመር መገናኛ እንዲሁም ለፎቆች ስዊች ጊር ይሆናል፡፡

43.**"ፓወር ፋክተር"** ማለት ዋት ለቮልት አምፒር ያለው ሬሾ ወይም ኪሎ ዋት ሰዓት ለኪሎ ቮልት አምፒር ሪያክቲቭ ሰዓት ሲሆን እንደ ቆይታው ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

44.**"ቅጥር ግቢ"** ማለት የተወሰነ አካባቢ ህንጻ አጥር ግቢ እና መስክ የመሳሰሉት ሆነው ኤሌክትሪክ በአንድ ደንበኛ ስም የተገናኘበት ወይም የሚገናኝበት ይዞታ ነው፡፡

45.**"የማይቋረጥ ጭነት"** ማለት በተለመደ ሁኔታ ከአቅም በላይ ካልሆነ በስተቀር የማቋረጫ ትዕዛዝ የማይዘጋጅለት ማለት ነው፡፡

46.**"የአገልግሎት መስመር"** ማለት የኤሌክትሪክ አቅርቦት መስመር ሆኖ ኃይል የሚቀርብበት ወይም በኢ.ኤ.አ እንዲቀርብ የታሰበ ከአንድ ማከፋፈያ ወደ አንድ ተጠቃሚ ወይም የተጠቃሚዎች ቡድን ከተመሳሳይ ማሰራጫ የሚደርስበት ነው፡፡

47.**"ኤል.ዲ.ሲ"** ማለት በኢትዮጵያ መንግስት የተቋቋመ የኃይል ጭነት ማከፋፈያ ማዕከል ነው፡፡

48.**"የታሪፍ መደብ"** ማለት በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት/መንግስት የሚወሰን የፍጆታ ክፍያ የሚፈጸምበት ለሁሉም የደንበኛ መደቦች የተዘጋጀ የዋጋ ተመን ነው፡፡

49.**"የክፍያ ጊዜ"** ማለት የኤሌክትሪክ አቅርቦት ወቅታዊ ክፍያዎች በተመለከተ እና አገልግሎቶች በኢ.ኤ.አ የሚሰጡበት ወቅታዊ የክፍያ ጊዜ ነው፡፡

50.**“የማስተላለፊያ መስመር”** ማለት ሁሉንም ከፍተኛ ግፊት ያላቸው ኬብሎች ፣ ከመሬት በላይ የሚዘረጉ መስመሮች (የኢ.ኤ.አ ወሳኝ ክፍል ያልሆኑ) የማከፋፈያ ስርአት/ሲስተም ኤሌክትሪክ ለማከፋፈል ጥቅም ላይ የሚውሉ ሲስተሞች አካቶ ከአንድ ማመንጫ ጣቢያ ወደ ሌላ ማመንጫ ጣቢያ የሚዘረጋ ወይም ሰብስቴሽን ከማንኛውም ኃይልን፣ ቮልቴጅን ከፍ ከሚያደርጉ እና ዝቅ ከሚያደርጉ ትራንስፎርመሮች ጋር፣ እስዊች-ጊር እና ሌሎች ስራዎች በዚህ አይነቱን ኬብል ወይም ከመሬት በላይ የሚዘረጉ መስመሮች አካቶ የነዚህን ግንባታዎች ወይም አካሎች እንዳስፈላጊነቱ ትራንስፎርመር ፣ ስዊችጊር እና ሌሎች ስራዎችን ያካተተ ሲስተም ሲሆን ማንኛውንም ሰብስቴሽን እና 132 ኪሎ ቮልት ወይም ከዛ በላይ ያካተተ መስመር ይሆናል፡፡

51.**“ኤሌክትሪሲቲ ግሪድ ኮድ”** ማለት በኢ.ኢ.ባ የሚሰጥ ሰነድ ሆኖ ለኢ.ኤ.አ የሚገለጽ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ የኃይል ሲስተም የማቀድ እና መተግበር ሀላፊነትን ያካትታል፡፡

52.**“ኤሌክትሪክ ያልቀረበለት ክልል”** ማለት በመልማት ላይ ያሉ ቦታዎች እና በዙሪያው ልማት የሚያስፈልጋቸው/እየተካሄደባቸው ያሉትን ጨምሮ ቦታው ምንም አይነት ማከፋፈያ መስመር/አውታር/ ተገቢ ማስተላለፊያ አቅም የሚፈለገውን ኃይል አቅርቦት ያልቀረበበት ቦታ ነው፡፡ የዚህ አይነቱ ክልል ኤሌክትሪክ ሽፋን እስኪሰጥ ኤሌክትሪክ አቅርቦት እንደሌለው አካባቢ ይቆጠራል፡፡

ጥቅም ላይ የዋሉት ቃላት እና አገላለፆች በዚህ ደንብ ስር ያልተገለፁ እና በአዋጆች ስር የተተረጎሙ፣ በዝርጋታ እና ቆጣሪ ኦፕሬሽን ደንቦች ላይ የዋሉ በተገለፀው ደንብ በስራ ላይ ያለው ትርጓሜ ይኖራቸዋል፡፡

## 2.3 (1) ማስታወሻዎችና አገላለፆች

**ማስታወሻ** 1፡ ማንኛውም በኪሎ ቮልት አምፒር ወደ ኪሎ ዋት ሊለወጥ የሚችል ሲሆን ይህም ኪሎ ቮልት አምፒር በ 0.8 በማባዛት ይሆናል ፡፡ የተገለጸው በፈረስ ጉልበት ከሆነ ወደ ኪሎ ዋት በ0.764 በማባዛት መቀየር ይኖርበታል፡፡

**ማስታወሻ** 2፡ የቢሮዎችና የኦፊሰሮች የማዕረግ ስያሜ

በዚህ ደአፖፕ የቢሮዎች ስም እንደ ደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማእከል ፣ የዲስትሪክት ቢሮዎች፣ የሪጅን ቢሮዎች፣ የዋና መስሪያ ቤት ቢሮዎች ፣ የኦፊሰሮች ስያሜ የሚያመለክተው አሁን በስራ ላይ ያሉ ቢሮዎችን፣ የኦፊሰር ስያሜዎችን እና ተተኪ አካላትን ይሆናል፡፡

# 3. የአቅርቦት ሲስተም እና የተጠቃሚዎች ምድብ

## 3.1 የአቅርቦት ሲስተም

ሀ. ኢ.ኤ.አ በተቻለ መጠን ያልተቆራረጠ የኃይል አቅርቦት በፍሪኩዌንሲ ገደብ ውስጥ በመሆን ለኦፕሬሽን ግሪዱ ሃይል ማቅረብ አለበት፡፡

ለ. የተገለፀው የኤሌክትሪክ ሲስተም አቅርቦት ቮልቴጅ እንደሚከተለው ይሆናል

- ዝቅተኛ መስመር (ዝ.መ)/ዝቅተኛ ቮልቴጅ (ዝ.ቮ)- ነጠላ ፌዝ፡ 220 ቮልት በፌዝ እና ኒውትራል መካከል 3ፌዝ፡ 380ቮልት በፌዞች መካከል፡፡
- መካከለኛ መስመር (መ.መ)/መካከለኛ ቮልቴጅ (መቮ) ባለ 3 ፌዝ 15 ኪሎ ቮልት
- ከፍተኛ መስመር (ከ.መ)/ ከፍተኛ ቮልቴጅ (ከ.ቮ) ባለ 3ፌዝ 33 ኪሎ ቮልት/45 ኪሎ ቮልት/66 ኪሎ ቮልት
- በጣም ከፍተኛ መስመር (በከ.መ) ወይም በጣም ከፍተኛ ቮልቴጅ (በከቮ) ባለ 3 ፌዝ 132 ኪሎ ቮልት፣ 230 ኪሎቮልት፣ 400 ኪሎቮልት፣ እና 500ኪሎ ቮልት

## 3.2 የአቅርቦት ምድቦች

የኢ.ኤ.አ የማሰራጨት ሲስተም ቴክኒካዊ ሁኔታዎች አመቺ እስከሆኑ ድረስ ከዚህ በታች በተገለፀው ቮልቴጅና ፌዝ አቅርቦት መፈፀም ይኖርበታል፡፡

### 1 ዝቅተኛ መስመር

- ሁሉም የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታዎች የውል ጭነት እስከ 7.5 ኪሎ ዋት ድረስ ከሆነ እና ማሽኑ ላይ ያለው የጭነት ምልክት 3 ፌዝ የሚጠይቅ ካልሆነ በስተቀር ነጠላ ፌዝ በ220 ቮልት ይሆናል፡፡

- ሆኖም ማሽኖቹ ሶስት ፌዝ የሚፈልጉ ከሆነ ከ7.5 ኪሎ ዋት በታች የሚጠየቅ የኃይል ጥያቄ መስተናገድ ይችላል፡፡
- የመስኖ ፓምፖች እና የግብርና አገልግሎት እንዲሁም ሁሉም ዝርጋታዎች እና የተዋዋሉት ጭነት ከ7.5 ኪሎ ዋት በላይ እስከ 150 ኬቪኤ ከሆነ 3ፌዝ፣ 4 የሽቦ መስመር በ380 ቮልት ማገናኘት ይቻላል፡፡

## 2. የመካከለኛ መስመር

- ውል የተደረገበት ጭነት ከ150 ኬቪኤ በላይ እስከ 5,000 ኬቪኤ ከሆነ 3 ፌዝበ 15 ኪ.ቮልት፣ በቴክኒክ አዋጭነት ጥናት መሰረት የሚሰጥ ሆኖ በተቻለ መጠን እራሱን የቻለ ከሰብስቴሽን ወጪ የሆነ መስመር ቢሰጠው ደንበኛው በቀጣዩ ከፍተኛ የቮልቴጅ ደረጃ አቅርቦት የመጠየቅ አማራጭ ይኖረዋል፡፡

## 3. ከፍተኛ መስመር

- ውል የተደረገበት ጭነት ከ5000 ኬ.ቪ.ኤ በላይ እስከ 10000 ኬ.ቪ.ኤ ሲሆን 3 ፌዝ በ33 ኪ.ቮልት በቴክኒካዊ አዋጭነት ጥናት መሰረት ሆኖ በተቻለ መጠን በአዲስ ራሱን የቻለ ከሰብስቴሽን ወጪ የሆነ መስመር ቢሰጠው ተጠቃሚው በቀጣዩ ከፍተኛ የቮልቴጅ ደረጃ አቅርቦት የመጠየቅ አማራጭ ይኖረዋል፡፡ በአካባቢው የ33 ኪ.ቮልት መስመር ከሌለ የ45 ኪ.ቮልት ወይም 66 ኪ.ቮልት መስመር ካለ ከነዚህ መስመሮች ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 4. በጣም ከፍተኛ መስመር

- ውል የተደረገበት ጭነት ከ10000 ኬ.ቪ.ኤ በላይ ከሆነ 3ፌዝ በ132፣ 230፣ 400 ወይም 500 ኪሎ ቮልት ሆኖ፡-

ሀ. ከላይ የተገለጸው የአቅርቦት ምድብ ለአዲስ ኃይል ማገናኘት፣ ኃይል ማሻሻያ ይህ ደ.አ.ፖ.ፐ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ለ. የኢ.ኤ.አ ካስፈለገው ነባሩን ከፍተኛ መስመር በራሱ ወጪ የከፍተኛ ቮልቴጅ ታሪፍ ጥቅም ሳይኖር ለተጠቃሚ ሊለውጥ ይችላል፡፡ ይሁንና ደንበኛው የከፍተኛ ቮልቴጅ ታሪፍ ተጠቃሚ ለመሆን ከፈለገ ለውጡን በራሱ ወጭ እንዲሰራለት ማድረግ ይችላል፡፡

ሐ. ነባር ተጠቃሚዎች የጭነት መጠን ለመቀነስ ሲያመለክቱ በነበረው የአቅርቦት ሲስተም የመቀጠል አማራጭ ይኖራቸዋል፡፡ ሆኖም የጭነቱ መጠን ከቀነሰ በኋላ ኢ.ኤ.አ የሲስተም ለውጡን ወጪ ለመሸፈን ከተስማማ ደንበኛውና ድርጅቱ አንቀፅ 3.2ን መከተል ይኖርባቸዋል፡፡

መ. በማሰራጫ ሲስተም ቴክኒካዊ ሁኔታዎች መሰረት ኢ.ኤ.አ በተለያየ ቮልቴጅና ፌዝ በአንቀፅ 3.2 ከተገለጸው ውጪ ሊፈጽም ይችላል፡፡

<u>ማስታወሻ</u>

- ጥናት የሚደረግበት ማከፋፈያ ጣቢያ ላይ ያሉት ወጪ መስመሮች የቮልቴጅ መጠን 15 ኪሎ ቮልት ብቻ ከሆነ በደንበኞች የቀረበው የኃይል ጥያቄ መጠን ከማከፋፈያ ጣቢያው የመሸከም አቅም አንጻር ታይቶ እስከ 9000 ኪሎ ቮልት አምፔር ድረስ ያለው የኃይል ጥያቄ በ15 ኪሎ ቮልት ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡
- ጥናት የሚደረግበት ማከፋፈያ ጣቢያ ላይ ያሉት ወጪ መስመሮች የቮልቴጅ መጠን በሁለቱም ማለትም 15 ኪሎ ቮልት እና 33 ኪሎ ቮልት ከሆነ በደንበኞች የቀረበው የኃይል ጥያቄ መጠን ከማከፋፈያ ጣቢያው የመሸከም አቅም አንጻር ታይቶ ከ6000 ኪሎ ቮልት አምፔር በታች ያለው የኃይል ጥያቄ በ15 ኪሎ ቮልት መስመር እንዲስተናገዱ እንዲሁም 6000 ኪሎ ቮልት አምፔር ጨምሮ እስከ 20000 ኪሎ ቮልት አምፔር ድረስ ያለውን በ33 ኪሎ ቮልት መስመር ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ደንበኛው በ33 ኪሎ ቮልት መስመር ብቻ እንዲስተናገድ ጥያቄ ከቀረበ ከ 25 ኪሎ ቮልት አምፔር ጀምሮ እስከ 20000 ኪሎ ቮልት አምፔር ድረስ ያለውን በ33ኪሎ ቮልት መስመር ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡ ከ20000 ኪሎ ቮልት አምፔር በላይ ያለውን የኃል ጥያቄ በ132 ኪሎ ቮልት እና ከዛም በላይ ባለው የቮልቴጅ መጠን መስተናገድ ስለሚኖርበት ጥያቄው ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ቀርቦ መስተናገድ ይኖርበታል፡፡

### 3.3 ራሱን በቻለ መጋቢ መስመር የኃይል አቅርቦት

ሀ. ለአርክ፣ ለኢንዳክሽን ፈርነስ፣ የቆርቆሮ ፋብሪካዎች መካከለኛ የብረታብረት ማሽኖች፣ የብረት ማዕድን ማውጫዎች አነስተኛ የብረት ፋብሪካ ወዘተ የሚሰጥ የኃይል ጭነት 900 ኪ.ዋት እና ከዛ በላይ ከሆነ ከሰብስቴሽን ወጪ በሆነ ራሱን በቻለ ፊደር ብቻ መለቀቅ ሲኖርበት ሁሉም አስፈላጊ ወጪዎች የፊደር ወጪ መስመር ጨምሮ በተጠቃሚው የሚሸፈን ይሆናል፡፡

ለ. በሌሎች ሁኔታዎች ጭነታቸው ከ450 እስከ 900 ኪ.ዋ በ3.3 (ሀ) የተዘረዘሩት ኢንዱስትሪዎችን ጨምሮ በደንበኛው ጥያቄ መሰረት ከሰብስቴሽን ወጪ በሆነ ራሱን በቻለ ፊደር ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ ከ450 ኪ.ዋ በላይ ያሉ ኢንዱስትሪዎች በ3.3/ሀ/ ከላይ በተገለፁት ተካቶ ከ900 ኪ.ዋ ያነሰጭነት በተጠቃሚ/አመልካች ጥያቄ ሁሉንም አስፈላጊ ክፍያዎች ለመሸፈን ፈቃደኛ ከሆነ በቴክኒክ አዋጭነት ሁኔታና፣ ኮሪደር በሰብስቴሽኑ ውስጥ ከመገኘቱ አኳያ ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል፡፡

ሐ. ከሰብስቴሽን ራሱን የቻለ ፊደር ለመፍቀድ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

1. የሰብስቴሽን በቂ አቅም ሲኖር እና መስመሩ የሚያልፍበት አካባቢ መስመር ለመዘርጋት የሚያመች ከሆነ፤
2. አዲስ ደንበኛ ከሌላ ነባር ደንበኛ በጋራ ሲጠቀም የመጀመሪያውን ደንበኛ ስምምነት ማግኘትና ወጪውን የሚጋራ ከሆነ፤
3. በአቅርቦት ጥራት ላይ ተፅእኖ የማይፈጥር ከሆነ፡፡
4. የወጪ መስመር፣ ቆጣሪና ተጨማሪ የሲስተም ለውጦች ወጪ በአዲሱ ደንበኛ የሚሸፈን ሲሆን ነባሩን ሲስተም ለማንሳት የሚኖር ወጪ የተጠቃሚዎች አይሆንም፡፡
5. እራሱን በቻለ መስመር የተዘረጋለት ደንበኛ ሙሉ ስራውን ከጀመረ በኃላ ከተፈቀደለት ሃይል በታች በመጠቀሙ ትርፍ ሃይል መኖሩ የተረጋገጠ ከሆነ እና ይህ ትርፍ ሃይል ተመልሶ እንደማይጠቀምበት በኢኤአ በቂ ማረጋገጫ ከተገኘ ትርፉን ሃይል ለሌላ ደንበኛ ሊሰጥ ይችላል፡፡

### 3.4 ፓወር ፋክተር

ሀ. የኢ.ኤ.አ በማንኛውም የቢል ዝግጅት ወቅት ስልጣን ባለው አካል አስወስኖ የተለየ አማካይ ፓወር ፋክተር መጠን በታሪፍ መደቡ መሰረት ካላወጣ በስተቀር የደንበኛው ጭነት አማካኝ የፓወር ፋክተር መጠን 0.9 መሆን ይኖርበታል፡፡

ለ. በማንኛውም የቢል ዝግጅት ወቅት በታሪፍ መደቡ መሰረት የተለየ አማካኝ ፓወር ፋክተር መጠን እስካልተገለጸ ድረስ መጠኑ ከ0.75 በታች ሆኖ ከተገኘ ኢ.ኤ.አ የደንበኛውን ኤሌክትሪክ በጊዜያዊነት ሊያቋርጥ ይችላል፡፡ ይህም በአንቀጽ 4.36 በተቀመጠው መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ሐ.በማንኛውም የቢል ዝግጅት ወቅት አማካኝ የፓወር ፋክተር ጭነታቸው ከ0.9 በታች ለሆኑ ተጠቃሚዎች ባለው የታሪፍ መደብ መሰረት የገንዘብ ቅጣት የሚጥል ሲሆን ከ0.9 በላይ ለሚያስመዘግቡ ደግሞ ማበረታቻ ሊያደርግ ይችላል፡፡ የማበረታቻውን ዓይነት እና መጠን በተመለከተ ስልጣን ባለው አካል የሚወሰን ይሆናል፡፡

### 3.5 የኃይል ጭነት ማመጣጠን

ሀ. ኢ.ኤ.አ ለባለ 3 ፌዝ ተጠቃሚዎች ከ5% የበለጠ ያልተመጣጠነ ጭነት እንዳይኖር ያረጋግጣል፡፡ ከአቅርቦት መነሻ ቦታ ላይ የአንድ ፌዝ የጭነት ክፍልፋይ ከሌሎች ቀሪ ፌዞች አንጻር ከ10% መብለጥ የለበትም፡፡

ለ. የ3 ፌዝ አቅርቦት የሚወስድ ተጠቃሚ በፌዞቹ መካከል ያለውን የጭነት አለመመጣጠን ከ5% እንዳይበልጥ በራሱ በኩል መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

ሐ.ከላይ በ(ሀ) እና (ለ) ላይ በተገለጹት ተፈጻሚ አለመሆን ያለውን ቅጣት ወይም ካሳ ለመወሰን ኢ.ኤ.አ ፕሮሲጀር አውጥቶ ለኢ.ኢ.ባ ያቀርባል፡፡

### 3.6 የደንበኞች የታሪፍ መደብ

የኢ.ኤ.አ ከኢ.ኢ.ባ ወይም ከመንግስት በሚያገኘው ፈቃድ ደንበኞቹን በተለያየ የታሪፍ መደብ መመደብ እና እንዲመደቡለት ሃሳብ ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ ሲጸድቅ ቀደም ብለው በአንድ የታሪፍ መደብ የነበሩ ደንበኞችን መልሶ በሌላ ታሪፍ ሊመድብ ይችላል፡፡ በወቅቱ ያለው የታሪፍ መደብ በአባሪ ቁጥር 3.1 ተገልፆል፡፡

## 3.7 የኤሌክትሪክ አቅርቦት ክፍያዎች

ሀ. የኤሌክትሪክ አቅርቦት ታሪፍ እና ሌሎች ክፍያዎችን በተመለከተ በኢ.ኤ.አ ወይም በመንግስት መገለፅ ይኖርባቸዋል፡፡ የዚህ አይነቱ ታሪፎች ወይም ክፍያዎች ቢያንስ በ2 ሰፊ ሽፋን ያላቸው እና በየቀኑ በሚታተሙ ጋዜጦች ላይ አቅርቦት በሚሰጥበት ቦታ ሁሉ ከተገለፀ በኋላ ቢያንስ ለ3 ተከታታይ ቀኖች እንዲቆይ ተደርጎ በቀጣዩ ወር መጀመሪያ ቀን ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ክፍያዎቹ የሚከተለውን ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡

1. ዝቅተኛ ወርሃዊ ክፍያ፣ ቋሚ ክፍያዎች፣ አመታዊ ክፍያ
2. የኃይል ፍላጎት ክፍያዎች
3. ለቀረበ ወይም ለሚቀርብ ኃይል የፍጆታ ክፍያዎች
4. ወቅታዊ እና የቀኑ የተለያየ የሰዓት ክፍያዎች
5. የሲንክሮናይዜሽን ክፍያዎች
6. የማይቋረጥ ጭነት ክፍያዎች
7. ለግልፅ አቅርቦት የድጎማ ሱር ክፍያዎች
8. ለአገልግሎት መቋረጥ ማካካሻ ክፍያ
9. በኢ.ኤ.አ የማሰራጫ መስመር ላይ ኤሌክትሪክ ለማሰራጨት ፈቃድ ካለው ግለሰብ ወይም ድርጅት ኤሌክትሪክ የማሰራጫ ሱር ቻርጅ ክፍያ፡፡

ለ. ኢ.ኤ.አ ሌሎች ክፍያዎች ያለገደብ የማገናኘት ክፍያ፣ መልሶ ማገናኘት ክፍያ፣ ለዘገየ ክፍያ፣ የነዳጅ ሱር ቻርጅ፣ የኃይል ግዢ፣ የግሪድ ድጋፍ ክፍያ እና የፓወር ፋክተር መቀጫ ወይም ማበረታቻ ቀደም ብሎ ከመንግስት/ኢ.ኢ.ባ ሲጸድቅ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

ሐ. የታሪፍ መደብ በኢ.ኤ.አ ወይም በመንግስት ከጸደቀ በኋላ የኢ.ኤአ በድረ ገፁ ማሳወቅ እና በብሮሸር ወዲያውኑ ማተም እና ማሰራጨት እንዲሁም ሰፊ ሽፋን ባለው ሚዲያ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## 3.8 በህግ የተወሰኑ ክፍያዎች

በህግ የተወሰኑ ክፍያዎች እንደ የኤሌክትሪክ ግብር፣ ቀረጥ ወዘተ ካሉ በህጉ መሰረት በተጠቃሚው የሚከፈሉ ይሆናሉ፡፡

# 4. የኤሌክትሪክ አቅርቦት መመሪያ

## 4.1 የኤሌክትሪክ አቅርቦት ግዴታዎች

ኢ.ኤ.አ በማንኛውም ባለ ይዞታ (ቅጥር ግቢ ወይም ባለቤት) ለቀረበለት ጥያቄ ወይም ማመልከቻ ሙሉ ክፍያ ከተፈጸመ በኋላ በ4.7(ረ) መሰረት ኤሌክትሪክ ማገናኘት ይኖርበታል፡፡

የዚህ አይነቱ አቅርቦት የዋናው ማሰራጫ መስመር መሳብ የሚያስፈልግ ከሆነ ወይም የአዲስ ሰብስቴሽን ኮሚሽን ማድረግ ካስፈለገ ለዚህ አይነቱ ይዞታ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ወዲያውኑ እንዳለቀ ወይም በአንቀፅ 4.7 በተገለፀው መሰረት ኤሌክትሪክ አገልግሎት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ከመንደር ወይም ቀበሌ ወይም አካባቢ የአቅርቦት ማመልቻ ሲኖር የኤሌክትሪክ አቅርቦት ካልደረሰበት ቦታ ሲጠየቅ ኢ.ኤ.አ የኤሌክትሪክ አቅርቦቱን ጊዜ እንደየ ጉዳዩ ሁኔታ ጊዜውን ማራዘም ይችላል፡፡

በተጨማሪም ከነባር ደንበኞች ያልተከፈለ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ክፍያዎች ሲኖር የአዲስ ኃይል ማገናኘት ስራ የሚፈጸመው ያልከፈሉትን ዕዳ ክፍያ ሲፈጽሙና በአንቀጽ 4.3(ረ) በተገለጸው መሰረት የእዳ ነጻ የምስክር ወረቀት ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡

የአዲስ ኃይል አቅርቦት ክፍያ ሲፈፀም ለአዲስ ባለቤቶች ክፍያዎቹ እንደተፈፀሙ ብቻ የሚለቀቅ ሆኖ ከእዳ ነጻ የምስክር ወረቀት በአንቀፅ 4.3(ረ) መሰረት ሲቀርብ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ተጠቃሚው የኤሌክትሪክ ፍጆታ ክፍያዎች እዳ ካለበት የአዲስ ኃይል አቅርቦት ጥያቄው ለአመልካች አይለቀቅም፡፡

## 4.2 የማሰራጫ መስመር ዝርጋታ ግዴታዎች

ሀ. ኢ.ኤ.አ የደንበኛውን የሃይል ፍላጎት አስተማማኝ ለማድረግ የማሰራጫ መስመሮቹ የተሻሻሉ እና አቅም ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የመስመሮች የማስተላለፍ አቅም እስከ 80 በመቶ ጭነት ጭነው ከተገኙ መስመሮቹን ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት አዘጋጅቶ ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

ይሁንና ከአዲስ መንገዶች ግንባታ ጋር ተያይዞ ለሚመጡ የመንገድ መብራት መስመር ዝርጋታ ጥያቄዎች የአካባቢው አስተዳደርን የሚመለከት ሲሆን በነባር መንገዶች ማለትም የመንገድ መብራት ሳይዘረጋላቸው የቆዩትን በተመለከተ ግን ለስራው አስፈላጊ የሆነው ክፍያ ሲፈጸም በኢ.ኤ.አ በኩል ይስተናገዳሉ፡፡

ኢ.ኤ.አ ኤሌክትሪክ ባልተዳረሰባቸው ክልሎች/አካባቢዎች ይህ በታወቀ በ6 ወራት ውስጥ አስፈላጊ የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማት አቅርቦቶችን የደንበኞችን ቁጥር ጨምሮ ዝርዝር መረጃ ለሚመለከተው ባለስልጣን ማቅረብ የሚኖርበት ሲሆን ይህ መረጃ ለሚመለከተው ባለስልጣን በደረሰ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ደግሞ የስራውን ዝርዝር እቅድ አዘጋጅቶ ለቀጣይ ስራ ዝግጅት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ለ. ኢ.ኤ.አ የነባር ደንበኞችን አቅርቦት እና ለወደፊት የሚመጡ የሃይል ጥያቄዎችን በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስተናገድ የማሰራጫ ሲስተሙን በራሱ ወጭ ማሻሻል የሚጠበቅበት ሲሆን ይህንን ወጭ ከደንበኞች በታሪፍ/የድርሻ ክፍያ (partial payment) እና በመሳሰሉት የወጭ መጋራቶች የሚያገኝ ይሆናል፡፡

## 4.3. የአዲስ ኃይል አቅርቦት አጠቃላይ መመሪያ

ሀ. የሃይል አቅርቦት ሲስተም እና ቮልቴጅ እንደ ደንበኛው የምድብ ዓይነት እና ጭነት መጠን የሚለያይ ሲሆን አፈጻጸሙም በአንቀጽ 3 በተጠቀሱት ዝርዝሮች መሰረት ይሆናል፡፡

ለ.የአዲስ ኃይልና ኃይል ለማሻሻል ወይም ለመቀነስ ለማመልከቻ የሚያስፈልጉ ቅጾች በሁሉም የድርጅቱ ቢሮዎች በነጻ መቅረብ ይኖርበታል፣ በድርጅቱ ድህረ ገጽ ላይም

ደንበኛው በቀላሉ እንዲያገኘው መኖር ይገባዋል፡፡ ኢ.ኤ.አ በድህረ ገፁ ዳውንሎድ (ፕሪንት) እንዲደረጉ ማስቻል፣ ቅጾችን ፎቶ ኮፒ አድረገው ማመልከት እንዲችሉ፣ እንዲሁም በኤሌክትሮኒክ መንገድ ማመልከት እንዲችሉ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

ሐ.የኢ.ኤ.አ በደንበኞች የኃይል አቅርቦት ምድብ እና ጭነት መሰረት በየደረጃው ሰራተኞችን የሚመድብ ሲሆን ማንኛውም የአዲስ ሃይል ጥያቄ ባለቤት በየክልሉ የተቋቋመው ሪጅን ቢሮ ይሆናል፡፡

መ. ከአዲስ ሃይል ጥያቄ ጋር በተያያዘ ማንኛውም አይነት ከፕሮሲጀር፣ ከክፍያ፣ ከፈጻሚ ሰራተኞች ጋር የተገናኙ መረጃዎች አገልግሎት በሚሰጥባቸው የኢ.ኤ.አ ቢሮዎች በሙሉ በማስታወቂያ ሰሌዳ መለጠፍ ይኖርባቸዋል፡፡

ሠ. የአዲስ ሃይል ጥያቄ ፎርም ለመሙላት እና ቀደም ብለው ክፍያ ፈጽመው በመጠባበቅ ላይ የሚገኙ ደንበኞች ጥያቄአቸው ያለበትን ደረጃ ለማወቅ እንደ ኢንተርኔት፣ በማዕከላዊ የጥሪ ማዕከል፣ የጥሪ መቀበያና መልስ መስጫ አገልግሎት(IVRS Facility)፣ በማንኛውም ወቅቱ በሚፈቅደው ቴክኖሎጂ በመጠቀም እና ተገቢ የሆነ የቋሚ ቢሮዎች ግንኙነት በመፍጠር መረጃ መስጠት ይኖርበታል፡፡

ረ. አዲስ ሃይል የተጠየቀለት ቤት ወይም ቦታ ከሌላ ደንበኛ በሽያጭ የሚተላለፍ ከሆነ አዲሱ አመልካች ነባሩ ደንበኛ ከእዳ ነጻ መሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ሲሆን ነባሩ ደንበኛ መረጃ መስጠት ካልቻለ አዲሱ ደንበኛ ንብረቱን ከመግዛቱ በፊት ወደ ኢ.ኤ.አ በመቅረብ እዳ መኖር አለመኖሩን ማጣራት ይችላል፡፡ኢ.ኤ.አ የአዲስ ሃይል ጥያቄ በቀረበለት በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ ከእዳ ነጻ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

ሰ. አንድ ይዞታ በህጋዊ መንገድ በሚከፋፈልበት ወቅት የፍጆታ ሒሳብ ካለ እንደ አከፋፈሉ ሁኔታ የተጠቀሙበት የኤሌክትሪክ ፍጆታ እዳም መከፋፈል ይኖርበታል፡፡

ሸ. ለተከፋፈለው ይዞታ አዲስ ኃይል የሚገናኘው በተከፋፈሉት ባለይዞታዎች አመልካቹ በተከፋፈለው መሰረት የዕዳውን ድርሻ መክፈሉ ከተረጋገጠ በኋላ ነው፡፡ ድርጅቱ ለአመልካቹ ሌሎች ተካፋዮች እዳቸውን ባለመክፈላቸው ምክንያት እዳ የሌለበትን (ድርሻውን ለከፈለ) አመልካች የአዲስ ሃይል አቅርቦት መከልከል የለበትም፡፡ እንዲሁም የሌሎቹን የመጨረሻ ክፍያ መረጃ ከአመልካቹ አይጠይቅም፡፡

### 4.3.1 የኃይል አቅርቦት ማመልከቻ ሂደት

ሀ. የአዲስ ኃይል አቅርቦት ማመልከቻ በአባሪ 4.1 በተገለፀው ቅጽ በማንኛውም ሁኔታ ተሞልቶ ከምዝገባ ክፍያ ጋር በኢ.ኤ.አ በተገለፀ የሪጅን ጽ/ቤት ስር ባሉ ቢሮዎች የሚከተሉት የተረጋገጡ እውነተኛ የሰነዶች ኮፒ ሲሟሉ ማመልከት ይችላል፡፡

1. ማንነትን የሚገልጽ መታወቂያ (የቀበሌ መታወቂያ፣ ፓስፖርት፣ መንጃ ፈቃድ ወዘተ)፤ የኤሌክትሪክ ፍጆታ የመጨረሻ ክፍያ ደረሰኝ (ለሃይል ማሻሻያ/ለተጨማሪ ቆጣሪ )፣
2. በውክልና የሚተዳደር ቦታ ከሆነ በተራ.ቁ.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ ህጋዊ ውክልና፤
3. ለግል ተከራዮች/ድርጅቶች በአከራይ በኩል በተከራይ ስም ቆጣሪ አስገብተው እንዲጠቀሙ ከፈቀዱ እና ለማንኛውም ዕዳ ኃላፊነት እንደሚወስዱ በአባሪ 4.1 መሠረት ማረጋገጫ ሲሰጡ ፤
4. የሽርክና ድርጅት ከሆነ በተ.ቁ 1 የተገለጸው እንዳለ ሆኖ የሽርክና ማረጋገጫ ሰነድ ሲያቀርብ፤
5. በመንግስታዊ አካል ለሚተዳደሩ ቤቶች እና ቦታዎች የሚመለከተው ባለስልጣን ሲፈቅድ እና ተጠቃሚው ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ ሲያቀርብ በመንግስታዊው ተቋም ስም ቆጣሪ የሚገባለት ሲሆን ማንኛውም ኃላፊነት የፍቃድ ሰጭው ተቋም ይሆናል፤
6. ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት ከሆነ በተ.ቁ 1 የተገለጸው እንዳለ ሆኖ የመቋቋም ምስክር ወረቀት፣ የዋና ስራ አስኪያጁ ማንነትን የሚገልፅ መታወቂያ፤
7. የሶስት ፌዝ ጠያቂ ደንበኞች ከሆኑ በባለስልጣን/የኤሌክትሪክ ነክ ፈቃድ ባለው ስራ ተቋራጭ የተሰጠ የውስጥ ኤሌክትሪክ መስመር ምርመራ መጠናቀቅ የምስክር ወረቀት በተረጋገጠ ቅፅ/አባሪ 4.4 መቅረብ ይኖርበታል፤
8. ከ7.5 ኪ.ዋት በላይ በአንድ(1) ቆጣሪ ለሚጠይቁ ደንበኞች የውስጥ ኤሌክትሪክ ዝርጋታ ንድፍ (ኢንስታሌሽን ፕላን)፣ የስራ ማጠናቀቂያ ሪፖርት(ካለ)፣ የምርመራ ሰርተፊኬት በቅጹ መሰረት የታደሰ ፍቃድ ባላቸው ባለሙያወች ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

9. የቀረበውን የኃይል ጥያቄ ከ 7.5 ኪ.ዋት በታች ከሆነ ባመልካቹ በራሱ የቀረበ የቦታ ዝግጁነት ሪፖርት፣

ለ. አስፈላጊ ሲሆን የኢኤአ አመልካቾችን ማመልከቻ ቅፅ እንዲሞሉ ማገዝ ይኖርበታል፡፡

ሐ. ኢ.ኤ.አ ማመልከቻውን እና ሰነዶችን አረጋግጦ ከተቀበለ የመከታተያ ቅጽ መስጠት ይኖርበታል፡፡ የመከታተያ ቅጹ የተወሠነ የምርመራ ቀጠሮ ቀን ማመላከት የሚኖርበት ሲሆን የኤሌክትሪክ አቅርቦት በደረሰባቸው አካባቢዎች ማመልከቻ በተጠናቀቀ በ7 ቀናት ውስጥ እንዲሁም የኤሌክትሪክ አቅርቦት ባልደረሰባቸው አካባቢዎች በ2 ሳምንት ውስጥ የምርመራው ውጤት ይገለጽለታል፡፡መ.በማንኛውም ሁኔታ በህግ መስፈርቶች እና በአዋጆች ኤሌክትሪክ እንዳይዘረጋ የተከለከሉ ቦታዎች ካሉ አዲስ አቅርቦት ማመልከቻ መኖር የለበትም፡፡

ሠ.ኢ.ኤ.አ በመስመር ችግር ምክንያት፣ መሬት ለማግኘት መዘግየት፣ የቴክኒክ ተቀባይነት እና የማሰራጫ አቅም እጥረት እና ሌሎች የማይቆጣጠራቸው ሁኔታዎች ሲኖሩ በተገለፀው ጊዜ ለአመልካቹ የአቅርቦት መዘግየት ሃላፊነት አይኖርበትም፡፡

ረ.በማመልከቻው ላይ የሚቀርብ ማናቸውም መረጃ ስህተት ሆኖ ከተገኘ ወይም ደግሞ ተከላው ትክክለኛ ካልሆነ ወይም የኃይል ስርጭቱ ህግን የሚፃረር ከሆነ የኢ.ኤ.አ የኤሌክትሪክ ስርጭቱን የማይለቅ ሲሆን ይህንኑ ለአመልካቹ በፅሁፍ ይሰጠዋል፡፡

## 4.4 በኢ.ኤ.አ የሚደረግ ምርመራ

በምርመራ ወቅት አመልካቹ ወይም ህጋዊ ተወካዩ ፈቃድ ካለው ተቋራጭ ጋር በመሆን መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡

**በምርመራ ወቅት የኢ.ኤ.አ፡-**

ሀ. በአመልካቹ የቀረበው የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ የስራ ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት እና የምርመራ ሪፖርት ተቀባይነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
ለ. አመልካቹን በማማከር የኤሌክትሪክ ኃይል ለመስጠት ቆጣሪና ተዛማጅ እቃዎች የሚቀመጥበትን ቦታ መወሰን ይኖርበታል፡፡

ሐ. የኃይል አቅርቦት ለመስጠት በአቅርቦት መነሻና በአቅራቢያው ካለው የማሰራጫ መስመር መካከል ያለውን ርቀት ግምት ያወጣል፡፡

መ. የአቅርቦት መስመሩ በሶስተኛ ወገን ንብረት ላይ አለማለፉን ያረጋግጣል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ አመልካቹ ከ3ኛ ወገን ተቃውሞ እንደሌለው የሚገልፅ ማስረጃ ወይም ማመልከቻ እና የፈቃጁ መታወቂያ ኮፒ ማቅረብ ያለበት ሲሆን ይህ ማስረጃ ካልቀረበ ግን ኢ.ኤ.አ መስመሩ የሚዘረጋበትን ሌላ አማራጭ አቅጣጫ በመወሰን ይህንን ለማከናወን አስፈላጊውን ወጪ አመልካቹ ይሸፍናል፡፡

ሠ. በማመልከቻው ቅጽ ላይ ሌሎች ተጨማሪ ዝርዝር ጉዳዮች ማጣራት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ መረጋገጥ አለባቸው፡፡

ረ. ኢ.ኤ.አ የሚቀርብለት ማስረጃ በቂ ሆኖ ካላገኘው ለአመልካቹ ጉድለቱን እንዲያሟላ ወዲያውኑ ያሳውቀዋል፡፡ ምርመራው በሚከናወንበት ጊዜ ጉድለቱ በአመልካቹ ምክንያት ከሆነ ወይም ተጨማሪ ክፍያ የሚያስፈልግ ከሆነ አመልካቹ ይፈጽማል፡፡

### 4.5 የግምት ስራ

ሀ. በምርመራ የጭነት መጠኑ ከተረጋገጠ በኋላ ግምቱ የሚከናወነው በመመሪያና ደንቡ መሰረት ሆኖ በኢ.ኤ.አ ወይም በመንግስት በጸደቀው የክፍያ ሰነድ ነው፡፡

ለ. የኢ.ኤ.አ ማንኛውንም ከደንበኛ የሚጠየቁ ልዩ ልዩ የግምት ዋጋ ተመን (የዕቃ ዋጋ ተመንን ሳይጨምር) በተመለከተ በ2 ዓመት አንድ ጊዜ በሚመለከተው አካል ለማጸደቅ ያቀርባል፡፡ የግምት ዋጋ ተመን ከጸደቀ በኋላ ድርጅቱ ግልጽ በሆነ መልኩ የዋጋ ተመን መመሪያ ያዘጋጀል፣ ለኤሌክትሪክ መስመር፣ ለማቴሪያሎች፣ እና ሌሎች የግምት አዘገጃጀት ዘዴን ጨምሮ ከተዘጋጀ በኋላ የዋጋ ተመን መመሪያ ቅጅ ድርጅቱ ውስጥ ይቀመጣል፡፡ በተጨማሪም ደንበኛው/አመልካች ክፍያውን በምናሳውቅበት ወቅት የራሱን የግምት ዋጋ ዝርዝር ሊሰጠው ይገባል፡፡

ሐ. ግምቱ ተፈጻሚ የሚሆነው ሌላ የተሻሻለ ዋጋ ተመን እስከሚወጣ ድረስ ነው፡፡ የክፍያው ሁኔታ ከተሻሻለ ክፍያው የሚፈጸመው በአዲሱ ዋጋ ተመን ይሆናል፡፡ ነገር ግን የግምት ሂሳብ ከተከፈለ በኋላ ስራው ከመሰራቱ በፊት አዲስ የግምት ሂሳብ ቢወጣ ደንበኛው ቀድሞ በከፈለው ሂሳብ መሰረት ይስተናገዳል፡፡

መ. የመስመር ዝርጋታ ስራ ደንበኛው በግሉ ማሰራት ከፈለገ ፈቃድ ባለው ተቋራጭ መሰራት ያለበት ሲሆን በኢ.ኤ.አ ግምቱ ከተገመተ በኋላ የሠራተኛ ጉልበትና የትራንስፖርት ወጪ 18% ለክትትል ስራው ከመጀመሩ በፊት እንዲከፈል ይደረጋል፡፡ ኢ.ኤ.አ ስራውን በራሱ የሚያከናውን ከሆነ ደንበኛው ሙሉ ክፍያ ይፈጽማል፡፡ ደንበኛው በራሱ የሚያሰራ ከሆነ ከላይ የተጠቀሰው የክትትል ክፍያ 18% እንዳለ ሆኖ ሌሎች ተቋማዊ ወጪዎችን ማለትም ፓርሺያል፤አንሶልድ ኤሌክትሪክ፣ ከ10 ሜጋ ዋት በላይ ለሆነ የኃይል ጥያቄ የቆጣሪ ዋስትና ማስያዣ ወይም የተቀማጭ ባንክ ጋራንቲ፤ የፕላን ማጸደቂያ፣ ደንበኛው መክፈል ይጠበቅበታል፡፡

ሠ. የዋጋ ግምት ላይ ቅሬታ ካለ ኃይሉን ከፈቀደው አካል በአንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ለሚገኝ ኃላፊ የሚመራ ሲሆን አመልካቹ በዚህን ጊዜም ቅሬታው ካልተፈታ ጉዳዩ እንዲዳኝ ለተጠቃሚዎች ቅሬታ መስተንግዶ ፎረም ያቀርባል፡፡

ረ. በኢ.ኤ.አ ስራው ከተጠናቀቀ በኋላ በትክክል ስራው ላይ የዋለው የዲስትሪቢዩሽን እቃ በስራ ማጠናቀቂያ ሪፖርት (Job completion) ወይም (Bill of quantity) ይዘጋጃል፡፡

- የመጨረሻው ቢል ከተገመተው ዋጋ በላይ ከሆነ ልዩነቱ ኃይል ለአመልካቹ ከመለቀቁ በፊት አመልካቹ ይህን ልዩነት ገቢ ያደርጋል፡፡
- ልዩነቱ ከተገመተው ዋጋ በታች ከሆነ ልዩነቱ በቀጣይ በሚከፈሉ ኤሌክትሪክ ፍጆታ ክፍያዎች ቢል ላይ የሚወራረድ ወይም በ60 ቀናት ውስጥ ተመላሽ የሚደረግ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ኢ.ኤ.አ መደበኛ የሆነ ዋጋ (Normative Charge) የሚጥል ከሆነ የመጨረሻው ቢል አስፈላጊ አይሆንም፡፡

ሰ. ግምታዊ ክፍያው ከ10 ሜጋ ዋት በላይ ለሆነ የኃይል ጥያቄ የቆጣሪ ዋስትና ማስያዣ ወይም የተቀማጭ ባንክ ጋራንቲ፣ የኃይል መስመር ዝርጋታ ክፍያ እና የኃይል ጭነት ክፍያ ወዘተ በኢ.ኤ.አ የተወሰኑ ወይም በመንግስት የጸደቁ ክፍያዎችን ያካትታል፡፡

ሸ. በግምታዊ ወጪው ላይ ያለው የተጠቃሚው ድርሻ (Partial Payment)

1. በተጠቃሚዎች ለኃይል አቅርቦት ጭማሪ የሚጠየቅ የመስመር እና የትራንስፎርመር ማሳደጊያ እና ማሻሻያ ወጪ በኃይል ጭነት ስርአት ክፍያ በጸደቀው መሰረት ከተጠቃሚዎች የሚሰበሰብ ይሆናል፡፡ የድርሻ ክፍያ (Partial

Payment) የሚመለከታቸው ደንበኞች ማንኛውም የ3 ፌዝ ጠያቂዎች እና ከሁለት ቆጣሪ በላይ ለሚጠይቁ ደንበኞች ይሆናል፡፡

2. ዋና ማሰራጫ መስመሮች በሌሉበት አካባቢ ለአዳዲስ ዋና ማሰራጫዎች ተከላ የሚውለው ወጪ ከመንግስት ወይም ከአካባቢው አስተዳደር ወይም ከማናቸውም ተጠቃሚዎች ስብስብ አካል የሚሰበሰብ ይሆናል፡፡ የኢ.ኤ.አ ከዚህ በተጨማሪም ትርፍ የሆነ ኃይል ካላቸው መስመሮች አዳዲስ ዋና ማሰራጫዎችን ሊዘረጋ ይችላል፡፡

3. በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ አመልካቹ ከዋና ማሰራጫ ወደ አቅርቦት ኃይል መነሻ ለመዘርጋት የሚያስፈልገውን ሙሉ ክፍያዎችን ይከፍላል፡፡ ይህ ወጪ በኢ.ኤ.አ/መንግስት በሚያጸድቀውና በሚያወጣው የክፍያ ስሌት መሰረት ይሆናል፡፡

## 4.6 የዋና ማሰራጫ መስመሮች መዘርጋት ወይም የሰብስቴሽን ኮሚሽኒንግ ወይም የኃይል ማሻሻል ሳያስፈልግ ኃይል ስለ ማገናኘት፡፡

ሀ. የኢ.ኤ.አ ኃይል አቅርቦቱ በቂ ሆኖ ካገኘው እና አዲስ ምሰሶ መተከል የማያስፈልገው ከሆነ እንዲሁም መሬት ውስጥ ኬብል የማይዘረጋ ከሆነ ድርጅቱ በ7 ቀናት ጊዜ ውስጥ በፅሁፍ አቅርቦቱን ለማግኘት የሚያስፈልጉ ክፍያዎችን ባወጣው የክፍያ ስሌት መሰረት ለአመልካቹ ያሳውቃል፡፡ በሌሎች ሁኔታዎች ውስጥ የስራው ግምት እና ሌሎች ክፍያዎች በሳይቱ ላይ ምርመራ በተደረገ በ10 ቀናት ጊዜ ውስጥ አመልካቹ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

ለ. በምርመራው ወቅት የኃይል መስመሩ በአመልካቹ ንብረት ባልሆነ ቦታ ላይ የሚያልፍ ከሆነ አመልካቹ የፍቃድ ወረቀት በ7 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

ሐ. ከደንበኛው የፈቃድ ወረቀት ካመጣ ግምቱ ተሰርቶ በ90 ቀናት ውስጥ መክፈል ይኖርበታል፡፡

መ. ኢ.ኤ.አ ከተጠቃሚው ጥያቄ ሲደርሰው የክፍያ ቀኑን ከ30 ቀናት በላይ ሊያራዝም የሚችል ሲሆን በዚህ ምክንያት ለሚፈጠሩ ችግሮች ኢ.ኤ.አ የካሳ ክፍያ አይከፍልም፡፡

ሠ. ድርጅቱ በፊደል ተራ(ረ) ላይ የተገለፁት መስፈርቶች ከተሟሉ በኋላ ቆጣሪው የሚተከልበትን ግምታዊ ቀን ያሳውቃል፡፡ ቆጣሪውም በተቻለ መጠን አመልካቹ ወይም ወኪሉ በተገኘበት በቀጠሮ ቀን የሚተከል እና የሚታሸግ ሲሆን የአሌክትሪክ ሀይሉም ወዲያውኑ የሚለቀቅ ይሆናል፡፡

ረ. አዲስ ምሰሶ የማያስፈልግ እና የአሌሌክትሪክ ኃይል አቅርቦቱን ለመልቀቅ የምድር ውስጥ ኬብል ካልተዘረጋ እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ክፍያው ገቢ በተደረገ በ7 ቀናት ውስጥ የሚከናወኑ ሲሆን ይህም ቆጣሪው መተከሉ እና ስምምነት መፈረሙ ከተረጋገጠ በኋላ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

ሰ. በሌሎች ሁኔታዎች ውስጥ አቅርቦቱ በተገለፀው ጊዜ በአንቀፅ 4.7(ረ) መሰረት ክፍያው ገቢ ከተደረገ በኋላ የሚሰጡ ይሆናል፡፡

ሸ. ኢ.ኤ.አ ከቆጣሪ ወጪ ያሉ አስፈላጊ የዲስትሪቢዩሽን እቃዎች ማቅረብ የማይችል ከሆነ ወይም ተጠቃሚው የራሱን የዲስትሪቢዩሽን እቃዎች (ከቆጣሪ በስተቀር) ግልፅ ከሆነ ገበያ በመግዛት መትከል የሚፈልግ ከሆነ አመልካቹ የእቃዎቹን ዝርዝር መግለጫ(ስፔሲፊኬሽን) በተሰጠው መሰረት በኢ.ኤ.አ ስምምነት የሚገዛ ሲሆን የተገዙት የዲስትሪቢዩሽን እቃዎች በስፔሲፊኬሽን መሰረት ትክክለኛነቱ ከተረጋገጠ በኋላ አስፈላጊውን የምርመራ ክፍያ በማስከፈል ወደ ኢ.ኤ.አ ለተጠቃሚው ለመተከል ዝግጁ እንዲሆን ገቢ ይደረጋል፡፡

## 4.7 የዋና ማሰራጫ መስመሮች መዘርጋት ወይም የሰብስቴሽን ኮሚሽኒንግ ወይም የኃይል ማሻሻል ሲያስፈልግ የሚከናወን የአዲስ ኃይል አቅርቦት፡፡

ሀ. በአንቀፅ 4.4 በተገለፀው መሰረት ማመልከቻ በአካባቢው በሚገኝ ቢሮ (የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል) ከሰነዶችጋር ያቀርባል፡፡ ነገር ግን በደንበኛው በኩል ያልተጠናቀቁ ስራዎች ካሉ የውስጥ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ መጠናቀቅ የምስክር ወረቀት ሳያቀርብ ወደፊት የኤሌክትሪክ ኃይሉን የሚፈልግበትን የጊዜ ሰሌዳ ጠቅሶ ማመልከት ይችላል፡፡

ለ. የአገልግሎት መስጫ ማእከላት እስከ 150 ኬቪኤ ዝቅተኛ መስመር የቴክኒካል አዋጭነት ጥናት እና ኮሜርሻል አዋጭነት ጥናት የሚያጠኑ ሲሆን ከጥናቱ በኋላ የጸደቀው ጭነት በዲስትሪክቱ ኔትወርክ ፕላኒንግና ዲዛይን ዳታ ቤዝ መካተት ይኖርበታል፡፡የዲስትሪክት ኔትወርክ ፕላኒንግ ዲዛይን እና ሱፐርቪዝን ቢሮ ከ150 ኬቪኤ በላይ እስከ 3000 ኬቪኤ መካከለኛ መስመር የቴክኒካል አዋጭነት ጥናት እና ኮሜርሻል አዋጭነት ጥናት የሚመረምር ሲሆን እንዲሁም የሪጅኑ ዲዛይን ኢንጂነሪንግ እና ሱፐረቪዥን ቢሮ ከ3000 ኬቪኤ በላይ እስከ 10000 ኬቪኤ የቴክኒካል አዋጭነት ጥናት እና የኮሜርሻል አዋጭነት ጥናት ያጠናሉ፡፡ ነገር ግን በጣም ከፍተኛ መስመር ማለትም ከ10000ኬቪኤ በላይ እስከ 20000 ኬቪኤ ከሆነ በኮርፖሬት ዲዛይን ኢንጂነሪንግ እና ሎካላይዜሽን የቴክኒካል አዋጭነት ጥናት እና የኮሜርሻል አዋጭነት ጥናት ያጠናል፡፡ ከዚህ በላይ ከሆነ በኢትዮጵያ ኤሌክቲክ ኃይል የሚታይ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የተገለፁት የስራ ክፍሎች ለሚጠየቀው ኃይል የቴክኒክ አዋጭነት ሁኔታውን፣ ንድፍ፣ ምህንድስናና የኔት ወርክ ዝርጋታ እና የሃይል አቅርቦት ስራን ይመረምራሉ፡፡

- ከደንበኛው የሚቀርብ የኤሌክትሪክ የመስመር ዝርጋታ ፕላን የቴክኒካል አዋጭነት ጥናት በሚያጠናው አካል ተረጋግጦ መጽደቅ ይኖርበታል፡፡

**የአዋጭነት ጥናት የቮልቴጅ መጠንን በተመለከተ፡-**

- ጥናት የሚደረግበት ማከፋፊያ ጣቢያ ላይ ያሉት ወጪ መስመሮች የቮልቴጅ መጠን 15 ኪሎ ቮልት ብቻ ከሆነ በደንበኞች የቀረበው የኃይል ጥያቄ መጠን ከማከፋፊያ ጣቢያው የመሸከም አቅም አንጻር ታይቶ እስከ 9000 ኪሎ ቮልት አምፔር ድረስ ያለው የኃይል ጥያቄ በ15 ኪሎ ቮልት ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡
- ጥናት የሚደረግበት ማከፋፊያ ጣቢያ ላይ ያሉት ወጪ መስመሮች የቮልቴጅ መጠን በሁለቱም ማለትም 15 ኪሎ ቮልት እና 33 ኪሎ ቮልት ከሆነ በደንበኞች የቀረበው የኃይል ጥያቄ መጠን ከማከፋፊያ ጣቢያው የመሸከም አቅም አንጻር ታይቶ ከ6000 ኪሎ ቮልት አምፔር በታች ያለው የኃይል ጥያቄ በ15 ኪሎ ቮልት እንዲስተናገዱ እንዲሁም 6000 ኪሎ ቮልት አምፔር ጨምሮ እስከ 20000 ኪሎ ቮልት አምፔር ድረስ ያለውን በ33 ኪሎ ቮልት ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በ33 ኪሎ ቮልት መስመር ብቻ እንዲስተናገድ ጥያቄ ከቀረበ ከ 25 ኪሎ ቮልት

አምፔር ጀምሮ እስከ 20000 ኪሎ ቮልት አምፔር ድረስ ያለውን በ33ኪሎ ቮልት ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡

- ከ20000 ኪሎ ቮልት አምፔር በላይ ያለውን የኃል ጥያቄ በ132 ኪሎ ቮልት እና ከዛም በላይ ባለው የቮልቴጅ መጠን መስተናገድ ስለሚኖርበት ጥያቄው ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ቀርቦ መስተናገድ ይኖርበታል፡፡

ሐ. የቴክኒካል እና ኮሜርሻል አዋጭነት ጥናት ውጤት ድርጅቱ በሚከተለው መልኩ ለደንበኛው ወይም ለአመልካቹ ያሳውቃል፡፡

1. ለዝቅተኛ መስመር(ዝ.መ) በ5 የስራ ቀናት ውስጥ፤
2. ለመካከለኛ መስመር(መ.መ) አቅርቦት ጥያቄ በ7 የስራ ቀናት ውስጥ፤
3. ለከፍተኛ መስመር(ከ.መ) አቅርቦት ጥያቄ በ10 የስራ ቀናት ውስጥ፤
4. ለበጣም ከፍተኛ መስመር(በከ.መ) አቅርቦት ጥያቄ በ15 የስራ ቀናት ውስጥ፤
5. አቅርቦቱ ካለው ኔትወርክ ለማቅረብ የቴክኒክ አዋጭነት ያለው ሲሆን፤
6. የኃይል ጭነቱ መጠን ከተወሰነና የሳይቱ ምርመራ ከተደረገ በኋላ ለስራው የሚያስፈልገው ግምታዊ የገንዘብ መጠን ሲታወቅ፤
7. አስፈላጊው የኃይል ጭነት እና የመስክ ምርመራ ከተደረገ በኋላ እነዚህን ስራዎች ለመስራት የሚያስፈልገው ግምታዊ የጊዜ መጠን ሲታወቅ፤
8. በመስክ ምርመራው ወቅት አመልካቾች/ህጋዊ ወኪሉ እንዲገኙ ከ3 እስከ 7 ቀን ቀደም ብሎ እንዲያውቁ ሲደረግ፤
9. ተፈፃሚ የሚሆኑ ክፍያዎች ሲከፈሉ፤
10. ቆጣሪው የሚተከልበት ቦታ ሲወሰን፤
11. በአመልካቹ ለቆጣሪ ተከላ አስፈላጊ የሆኑ የሲቪል/ሌሎች ስራዎች እንዲሁም መቅረብ ያለባቸው የኤሌክትሪክ መሳሪያዎች ሲሟሉ፤

መ. ድርጅቱ ማስታወቂያ በሰጠ በ90 ቀናት ውስጥ (የክፍያ መጠኑ ካልተከለሰ) ከላይ እንደተገለፀው አመልካቹ የተገመተለትን ገንዘብ ገቢ ማድረግ ያለበት ሲሆን ይህን የማያደርግ ከሆነ ግን አመልካቹ ማመልከቻውን እንዳነሳ ተቆጥሮ ሲያመለክት ለማስገማቻ የከፈለው ክፍያ ለድርጅቱ ገቢ ይደረጋል፡፡ በዚህ መሰረት ስራውን እንደ ገና ለመጠየቅ

አዲስ ማመልከቻ ማቅረብ እንዲሁም እንደ አዲስ የማስገመቻ ክፍያ መክፈል ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ስራው የዘገየው በኢ.ኤ.አ ችግር ከሆነ በድጋሚ ደንበኛው የማስገመቻ ክፍያ መክፈል አይኖርበትም፡፡

ሠ. አመልካቹ ካመለከተ እና ከተገመተለት በኋላ የቦታ ለውጥ፣ የይዞታ ለውጥ እና በተፈቀደው የኃይል ጭነት ላይ ለውጥ ማድረግ የማይፈቀድለት ሲሆን ይህ ሆኖ ከተገኘ ግን ቀደም ሲል የቀረበው ማመልከቻ እንደተነሳ ተቆጥሮ የተከፈለው የማስገመቻ ክፍያ ለድርጅቱ ገቢ ሆኖ ስራውን ለማሰራት አዲስ ማመልከቻ ማቅረብ እና የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ፕላን (ንድፍ) በአዲሱ የኃይል መጠን መሰረት አሰርቶ ማቅረብ ይኖርበታል ፤ እንዲሁም አዲስ የማስገመቻ ክፍያ መክፈል ይኖርበታል፡፡

ረ. ኢ.ኤ.አ የአቅርቦት አጥረትና ከአቅሙ በላይ የሆነ ችግር እስካልገጠመው ድረስ የኮንስትራክሽን ስራዎቹን በሚከተሉት ጊዜያት ውስጥ ያከናውናል፡፡

- ከ220ቮ ጋር የሚገናኙ ጭነቶችን በ30 ቀናት ጊዜ ውስጥ
- ከ380ቮ ጋር የሚገናኙ ጭነቶችን በ45 ቀናት ጊዜ ውስጥ
- ከ15 ኪ.ቮ ጋር የሚገናኙ የኃይል ጭነቶችን በ60 ቀናት ጊዜ ውስጥ
- ከ33ኪ.ቮ ጋር የሚገናኙ የኃይል ጭነቶችን በ120 ቀናት ጊዜ ውስጥ
- ከ45ኪቮ/66ኪ.ቮ የሚገናኙ የኃይል ጭነቶችን በ300 ቀናት ጊዜ ውስጥ

  132 ኪቮ እና ከዛ በላይ ጋር የሚገናኙ የኃይል ጭነቶች በኢትዮጵያ ኤሌክትክ ኃይል የሚከናወን ይሆናል፡፡ የስርጭት ስርአትን ማስተካከል የሚፈልጉ የኃይል ግንኙነቶችን በተመለከተ ድርጅቱ ለአመልካቹ ከዚህ በታች እንደቀረበው ኃይል ጭነቱ የሚለቀቅበትን ጊዜ ቢበዛ ምን ያህል እንደሆነ ያሳውቃል፡፡

- የዲስትሪቢዩሽን ትራንስፎርመር ማሻሻያ ወይም የመስመር ዝርጋታ የሚያስፈልግ ከሆነ 90 ቀናት
- አዲስ የዲስትሪቢዩሽን ትራንስፎርመር የሚያስፈልግ ከሆነ 180 ቀናት
- ነባሩ15 ኪቮ ኔትወርክ መጠናከር ካለበት ወይም ነባሩ 33/45/66 ኪቮ ግሪድ (ሰብስቴሽን) ማሻሻያ የሚያስፈልገው ከሆነ 360 ቀናት

- ድርጅቱ የኤሌክትሪክ ኃይል ያልገባላቸው ቦታዎችን እንዲገባለቸው ለማድረግ እንዲሁም የአዲስ ኃይል አቅርቦት ለመልቀቅ እንደሚከተለው ስራውን ያከናውናል፡፡
    1. ለነባር ስራዎች ማሻሻያ ማድረግ የሚያስፈልግ ከሆነ 360 ቀናት
    2. አዳዲስ ስራዎች ወይም ግሪድ (ሰብስቴሽን) መገንባት ካለበት 540 ቀናት
    3. ከግሪዱ (ሰብስቴሽን) ጋር ላልተገናኙ ደንበኞች ከሆነ 240 ቀናት

ሰ. አመልካቹ ፈቃድ ባለው የኤሌክትሪክ ተቋራጭ ስራዎቹን እራሱ እንዲያከናውን ምርጫ የሚሰጠው ሲሆን ፈቃድ ያለው መርማሪ በኢ.ኤ.አ ስር ሆኖ የሚመረምርለት ሲሆን ስራውን ኢ.ኤ.አ ፈቃድ ላለው መርማሪ ከፍሎ ሊያሰራ ይችላል፡፡

ሸ. አመልካቹ በሳይቱ ላይ የሚከናወኑትን የኤሌክትሪክ ስራዎችን አስፈላጊ ከሆነ ስራው ከመጠናቀቁ ከ2 ሳምንታት ቀደም ብሎ ምርመራ እንዲከናወንባቸው የማድረግ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ይህ የምርመራ ስራ የሚከናወነው በስራ ላይ ባሉ የኃይል አዋጆችና ደንቦች እንዲሁም መመሪያዎች አማካኝነት ሲሆን ምርመራው በኢ.ኤ.አ ሃላፊ ከተፈቀደ በኋላ የምርመራ ሪፖርቱ ለኢ.ኤ.አ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ የከፍተኛ መስመር፣ የመካከለኛ መስመር ወይም በጣም ከፍተኛ መስመር ኃይል ጠያቂዎች የኤሌክትሪክ መሳሪያዎቹን ከአምራቹ የምርመራ ሪፖርት ሰርተፊኬት ፈቃድ ከተሰጠው የኤሌክትሪክ ተቋራጭ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

የምርመራ ውጤቶችና የስራ መጠናቀቅ የምስክር ወረቀቱ በወቅቱ የማይቀርብ ከሆነ ወይም ጭራሽኑ የማይቀርብ ከሆነ ለማንኛውም አይነት መዘግየት ተጠያቂነቱ የአመልካቹ ይሆናል፡፡

ቀ. የመስመር ዝርጋታ የስራ ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀቱ፣ የምርመራ ውጤቶቹ፣ ከ10 ሜጋ ዋት በላይ ለሆነ የኃይል ጥያቄ የቆጣሪ ዋስትና ማስያዣ ወይም የተቀማጭ ባንክ ጋራንቲ እና ሌሎች ክፍያዎች በአመልካቹ በበቂ ሁኔታ መቅረባቸው ከተረጋገጠ በኋላ የኢ.ኤ.አ የኤሌክትሪክ መስመሩ ኃይል የሚያገኘው መቼ እንደሆነ ከ7 ባላነሱ ቀናት ውስጥ ያሳውቃል፡፡ አመልካቹ ወይም ህጋዊ ወኪሉ የኤሌክትሪክ መስመሩ ቆጣሪው በሚታሸግበት እና ኃይል በሚለቀቅበት ወቅት መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡

## 4.8 ከአንድ በላይ ፎቅ ያላቸው ህንፃዎች፣ የተለያዩ አዳራሾች፣ በደንበኛው በተለያየ ቦታ ለሚሰሩ የማህበር ቤቶች የሚቀርብ የኤሌክትሪክ ኃይል፤

ሀ. ለአፓርትመንት፣ ለሪል ስቴት፣ ለኮንዶሚየም፣ የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ መንደር ወዘተ የሚቀርብ የሃይል ጥያቄ የሚያስፈልግ ኤሌክትሪክ ዲስትሪቢዩሽን ኔትወርክ የመዘርጋት ስራ በአንቀጽ 4.6 የተገለጸው እንዳለ ሆኖ ኢ.ኤ.አ ከዘረጋው አቅርቦት መነሻ ጀምሮ እስከ ህንጻዎች ወይም ቤቶች አቅርቦት ድረስ ሃላፊነት የደንበኛው ሲሆን የቁጣሪ ስራው ግን በኢ.ኤ.አ ይከናወናል፡፡ ከአንድ መነሻ የሚሰጠው ኃይል (single point of supply) አቅርቦት ግንባታ የኢ.ኤ.አ ሃላፊነት ይሆናል፡፡ በተቻለ መጠን ደንበኛው የከፍተኛ ቮልቴጅ ዲስትሪቢዩሽን ሲስተም (HVDS) መጠቀም አለበት፡፡ በተጨማሪም ለትራንፎርመር፣ ስዊች የሚሆን ቦታ በአመልካቹ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

ለ. ደንበኛው በዚህ መመሪያ በተካተተው ቅፅ አማካኝነት ከላይ በተገለፀው መሰረት የኤሌክትሪክ ኃይል ጥያቄ በአቅራቢያው ባለ አገልግሎት መስጫ ማዕከል ማስገባት አለበት፡፡ ከማመልከቻውም ጋር የህንፃው/የመኖሪያ ወይም ኢንዱስትሪ መንደሩ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የኤሌክትሪካል ፕላን መቅረብ ያለበት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም በመንግስት የጸደቁና በኢ.ኤ.አ መመሪያ መሰረት ለስራው የሚያስፈልገውን ክፍያዎችን መክፈል ይኖርበታል፡፡

ሐ. ድርጅቱ የሚያስፈልገውን የኃይል ጭነት በአባሪ 4.6 በተገለጸው መመሪያ መሰረት ይወስናል፡፡

መ. ደንበኛው ለዲስትሪቢዩሽን ሲስተም የሚወጡ ወጪዎችን (የትራንፎርመር እና ወይም የሰብስቴሽን ወጪዎችን ጨምሮ) በሚፈቀደው የኃይል ጭነት መጠን መሰረት እንደ ሚከተለው ወጪውን ይሸፍናል፡፡

- እስከ 100 ኪሎዋት፡ነባሮቹየዝቅተኛመስመሮችመጠናከርይኖርባቸዋል፡፡
- ከ100 ኪሎ ዋት እስከ 400 ኪሎዋት (500ኬቪኤ) ፡

ነባሮቹ የ15 ኪቮ መጋቢ መስመሮች ማስተናገድ የሚችል የኃይል አቅም ካላቸው የሚስተናገዱ ሲሆን ይህ ካልሆነ ግን አዲስ ባለ 15 ኪቮ መጋቢ መስመር የሚዘረጋላቸው ይሆናል፡፡

- ከ400 ኪሎዋትእስከ 4000ኪሎዋት (5000 ኬቪኤ):
  ባለ 15 ኪ.ቮልት መጋቢ መስመሮች በአቅራቢያ ከሚገኘው 33 ኪ.ቮልት ወይም 132 ኪ.ቮልት ሰብስቴሽን (በ33 ኬ.ቪ. ወይም በ132 ኬ.ቪ. ሰብስቴሽኖች ላይ ባለ15 ኬ.ቪ.) የሚስተናገድ ይሆናል፡፡
- ከ4000 ኪሎ ዋት እስከ 8000 ኪሎዋት (10,000 ኬቪኤ) :
  ባለ 33 ኪቮ መጋቢ መስመር ከ33 ኪ.ቮ ወይም 132ኪ.ቮ ሰብሴቴሽን ይዘረጋል፡፡
- ከ8000 ኪሎዋት (10,000 ኬቪኤ) በላይ:
  ባለ 132 ኪቮ መጋቢ መስመር በአቅራቢያ ከሚገኘው 132 ኪቮ ወይም 230፣ 400፣500 ኪቮ ሰብስቴሽን ይዘረጋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ገደቦች አመላካች ሲሆኑ የኃይል አቅርቦቱን አይነት በተመለከተ ድርጅቱ ያለውን መሰረተ ልማት በትክክል ለመጠቀም ለእያንዳንዱ ጉዳይ በቦርድ ከፀደቀ በኋላ በተለየ ሁኔታ ሊወስን ይችላል፡፡

ሠ. ደንበኛው ከላይ ለተጠቀሱ ስራዎች ብቻ የግምት ወጪዎች ክፍያ ይከፍላል፡፡ የአዲስ ኃይል ማገናኘት ክፍያን/service connection charge/ በሲስተሙ ላይ የኃይል ጭነት ክፍያ/system loading charges/፣ development charges/፣ በኢንዱስትሪ መኖሪያ መንደሩ ባሉ እያንዳንዳቸው ነዋሪዎች የሚከፈል ይሆናል፡፡ ይህም ለእያንዳንዱ አመልካች ኤሌክትሪክ እንዲገናኝ ማመልከቻው በቀረበ ጊዜ የሚከፈል ይሆናል፡፡ ደንበኛው ከኢኤአ ከአንድ ቦታ ብቻ የኃይል አቅርቦት እንዲቀርብለት ማመልከቻ ካስገባ ለመኖሪያ ቤቶቹ፣ ለህንፃዎቹ እያንዳንዱ ወለል እና ክፍል የሚቀርበው የቤት ውስጥ ኢንስታሌሽን ስራ በራሱ የሚሸፈን ይሆናል፡፡ ለእያንዳንዱ ባለቤት የሚሸጠው ኃይል፣ በደንበኛው የሚከናወነው የባለቤትነት ዝውውር አሰራርና ደንብ በዚህ አንቀጽ 4.45 ቀጥሎ እንደተመለከተው “በተጠቃሚው የሚቀርብ የኃይል ሽያጭ” በሚለው ዝርዝር መሰረት የሚከናወን ይሆናል፡፡

ረ. ኢ.ኤ.አ ጊዜያዊ ኤሌክትሪክ አቅርቦት ግንባታ የሚጀምረው ለኮንስትራክሽን የተገመተው ሒሳብ ሙሉ በሙሉ (100%) ከተከፈለ በኋላ ነው፡፡

ሰ.ነገር ግን ደንበኛው መስመሮቹን እራሱ መገንባት የሚፈልግ ከሆነ ይህንኑ ማድረግ የሚችለው በአንቀጽ 4.5(መ) መሰረት ለኢ.ኤ.አ 18% የቁጥጥር (supervision) ክፍያ ገቢ ካደረገ በኋላ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ደንበኛው ዋናው መስመር እስኪዘረጋለት ድረስ ጊዜያዊ የኃይል ጥያቄ ካቀረበ እና ይህንኑ ጊዜያዊ ኃይል በራሱ ማሰራት ከፈለገ ከላይ የተጠቀሰውን የክትትል (ሱፐርቪዥን) ክፍያ እንደተጠበቀ ሆኖ ከጠቅላላ የቁጥጥር ክፍያ 50% ተጨማሪ ገቢ ሲያደርግ ነው፡፡

### 4.9 ለጊዜያዊ /Temporary/ የኃይል አቅርቦት የሚቀርብ ማመልከቻ

ሀ. ኢ.ኤ.አ ለህንፃ ግንባታ ከ2 ዓመታት ላልበለጠ ጊዜ ለሌሎች ስራዎች ደግሞ ከ3 ወር ባልበለጠ ጊዜ ጊዜያዊ ኤሌክትሪክ ኃይልን ሊያቀርብ የሚችል ሲሆን መደቡም በንግድ ታሪፍ (ታሪፍ 20) ይሆናል፡፡

ለ. ለጊዜያዊ የኤሌክትሪክ አቅርቦት የሚቀርብ ማመልከቻ በአባሪ 4.5 ላይ በተጠቀሰው ፎርማት ተሞልቶ በአካባቢው ለሚገኝ አገልግሎት መስጫ ማዕከል ይቀርባል፡፡ ይህም አዳዲስ ምሰሶዎችን መትከል ወይም የመስመር ዝርጋታ የማያስፈልግ ከሆነ የኃይል አቅርቦት ከሚፈለግበት ጊዜ ቢያንስ ከ15 ቀናት፤ አዳዲስ ምሰሶዎች መተከል ካለባቸው ከ30 ቀናት ቀደም ብሎ ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር መቅረብ አለበት፡፡

1. የኃይል አቅርቦቱ የተጠየቀበት ቦታ በአካባቢው የመንግስት አካል ወይም በሌላ ባለቤት የተያዘ ከሆነ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታው ላይ ተቃውሞ እንደሌለ የሚገልፅ ማስረጃ፤
2. አመልካቹ የድርጅቱ ደንበኛ ካልሆነ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማቅረብ ሲኖርበት ነባር ደንበኛ ከሆነ የመጨረሻ ክፍያ ቢል ኮፒ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሐ. ድርጅቱ የቴክኒክ አዋጪነቱን (technical feasiblity) ካረጋገጠ በኋላ የተፈለገውን አገልግሎት ለመስጠት የሚችል ከሆነ የግምት ወጪ እና ሌሎች ክፍያዎችን ማመልከቻው በደረሰው በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለአመልካቹ ያሳውቃል፡፡

መ. የኤሌክትሪክ አገልግሎቱ ለተጠየቀው ጊዜ የሚከፈለውን የፍጆታ ክፍያ በኢ.ኤ.አ/መንግስት በየጊዜው በሚያጸድቃቸው የክፍያ ተመኖች መሰረት ያሳውቃል፡፡

ሠ. ከላይ በተገለጸው መሰረት የተገመተው ቅድሚያ ክፍያ ሒሳብ ገቢ ከተደረገ በኋላ የኃይል ጭነቱ እስከ 100 ኪሎ ዋት የሆነ የትራንስፎርመር እና የመስመር ዝርጋታ ስራ የሚፈልግ ከሆነ በ15 ቀናት ውስጥ እንዲገባለት የሚደረግ ሲሆን ስራው ቆጣሪ ብቻ የሚፈልግ ከሆነ በ5 ቀናት ውስጥ የሚስተናገድ ይሆናል፡፡ ከ100 ኪሎ ዋት በላይ ከሆነ ደግሞ በ30 ቀናት ውስጥ ኃይል ይገናኝለታል፡፡ ነገር ግን 100 ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ጊዚያዊ የኃይል ጠያቂ በሚሆኑበት ጊዜ የኃይል ጭነቱ የሚፈቀደው ከሚመለከተው የመንግስት አካል የጽሁፍ ማረጋገጫ ሲገኝ ይሆናል፡፡

ረ. ጊዜያዊ የኃይል አቅርቦቱ የሚቆይበት ጊዜ ሊራዘም የሚችል ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ከ90 ቀናት ላልበለጠ ጊዜ መራዘም የሚችል ሲሆን ደንበኛው የቀን ማራዘሚያ ጥያቄውን ውሉ ከሚጠናቀቅበት ቀን ቢያንስ 3 ቀናት ቀደም ብሎ ማመልከት ይኖርበታል፡፡ ዝርዝር መመሪያው በኢንስፔክሽን ማንዋል መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ሰ. የኤሌክትሪክ ሀይሉ ከተገናኘ በኋላ በሚመለከተው አካል የተሰጠ ፈቃድ (የስራ ፈቃድ፣ ያለመቃወምን የሚገልጽ ደብዳቤ) ከተነሳ የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲቋረጥ ተደርጎ ፈቃዱ ከተገኘ በኋላ መልሶ ይገናኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ኢ.ኤ.አ ለማናቸውም ጉዳቶች ሃላፊነቱን የማይወስድ ሲሆን በዚህ ረገድ የክፍያ ቅናሽ ወይም ተመላሽ ገንዘብ አይኖርም፡፡

ሸ. ጊዜያዊ የኃይል አቅርቦት ለሁለተኛ ጊዜ እንዲራዘም የሚፈለግ ከሆነ ተጠቃሚው የጊዜያዊ የኃይል አቅርቦቱ ከማለቁ ቢያንስ ከ1 ሳምንት በፊት ለኢ.ኤ.አ ይህንኑ ማሳወቅ አለበት፡፡ የኢ.ኤ.አ በአንቀፅ 4.10 (ሀ) በቀረበው ዝርዝር መሰረት እና ተጠቃሚው ተፈላጊውን ጊዜ የማራዘሚያ ቅድመ ክፍያ ከተከፈለ በኋላ ጊዜውን ሊያራዝም ይችላል፡፡ ይህም የማራዘሚያ ቅድመ ክፍያ በሌሎች መመሪያዎች የሚወሰን ይሆናል፡፡

ቀ. ይህ የጊዜያዊ አቅርቦት ወደ ቋሚ አቅርቦት ሲለወጥና ቋሚ አቅርቦቱ ከ10 ሜጋ ዋት በላይ ሲሆን ጊዜያዊ ተቀማጭ ደንበኛው ከፍሎ ከነበረ ለቋሚ አቅርቦቱ ለሚያስፈልገው

የዋስትና ተቀማጭ መጠን ግምት ውስጥ ገብቶ ይስተካከላል፡፡ በተጨማሪም ለቋሚ አቅርቦቱ የማያስፈልግ ትራንስፎርመር ካለ ያገለገለበት ዋጋ (Depericiation Cost) ተቀንሶ ለቋሚ ሃይል በሚጠየቀው የግምት ዋጋ ታሳቢ የሚደረግ ሆኖ ትራንስፎርመሩ ወደ ኢ.ኤ.አ ተመላሽ ይሆናል፤ የ(Depericiation Cost)ስሌት የሚወሰደው ትራንስፎርመሩ በሚነሳበት ወቅት ባለው ወቅታዊ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋጋ ዝርዝር መሰረት ይሆናል፡፡

### 4.10 ለጊዜያዊ ኤሌክትሪክ አቅርቦት የሚዘጋጅ አስቸኳይ የአቅርቦት እቅድ

ኢ.ኤ.አ በ24 ሰዓት ቅድሚያ ማስታወቂያ መሰረት በሚከተሉት ሁኔታዎች የጊዜያዊ ኃይል አቅርቦት ሊሰጥ ይችላል፡፡

1. ጥያቄው በቴክኒክ ረገድ አዋጭ እንደሆነ ከታወቀ
2. በኢ.ኤ.አ የሚጠየቀው ተጨማሪ ክፍያ ሲከፈል ሲሆን ይህም ክፍያ በሌሎች መመሪያዎች የሚወሰን ይሆናል፡፡

**4.11 የተገናኘ ወይም ውል የተደረገበት የኃይል ጭነት** ለማወቅ የሚረዱ አጠቃላይ ሁኔታዎች የተገናኘውን ጭነት ለማወቅ ጥቅም ላይ የሚውሉ ዘዴዎች በአባሪ 4.6 ቀርበዋል፡፡

### 4.12 ውል የተደረገበት (የተፈቀደ) ኃይል ጭነት መጠን፤

ሀ. የከፍተኛ ኃይል ጭነት አጠቃቀም ጠቋሚ maximum Demand Indicator(MDI) የሌላቸው የዝቅተኛ መስመር ኃይል ተጠቃሚዎች፡-

ከመኖሪያ እና ከንግድ ታሪፍ መደብ ተጠቃሚዎች ውጪ የተፈቀደው የኃይል ጭነት መጠን ከተገናኘው የኃይል ጭነት ጋር እኩል ይሆናል፡፡

ድርጅቱ የሚፈቅደው የኃይል ጭነት መጠን ከተገናኘው የኃይል ጭነት መጠን በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊያንስ ይችላል፡፡

- የመኖሪያ ቤት ታሪፍ ሲሆን ከተፈቀደው 30% ያላነሰ ይሆናል፡፡
- የንግድ ታሪፍ ሲሆን ከተፈቀደው ከ75% ያላነሰ ይሆናል፡፡

ከላይ የተገለፀው የጭነት መጠን ማወቂያ አሰራር ይህ የደንበኞች አገልግሎት ፖሊሲ እና ፕሮሲጀር ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ውል ለሚፈጽሙ የአዲስ ኃይል ጠያቂዎች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በነባሮቹ ተጠቃሚዎች ላይ ያለው ትርፍ ኤሌክትሪክ ኃይል ጭነት በዚህ ፖሊሲ መመሪያ 6.9 መሰረት ይሆናል፡፡

ለ. Maximum Demand Indicator(MDI) ያላቸው የዝቅተኛ መስመር እና ሁሉም መካከለኛ መስመር፣ ከፍተኛ መስመር እና በከፍተኛ መስመር የኃይል ጭነት ተጠቃሚዎች፡-

- ውል የሚደረግበት የኃይል ጭነት በድርጅቱ እና በተጠቃሚው/በአመልካቹ መካከል በሚደረግ ስምምነት ሆኖ ነገር ግን ከላይ በንዑስ አንቀፅ (ሀ) ላይ ከተገለጸው በታች መሆን የለበትም፡፡

ሐ. ለኢንዳክሽንና ለአርክ ፈርነስ የሚሰጠው የኃይል አቅርቦት የተፈቀደው ጭነት ከሚፈልጉት የቶን መጠን ጋር ተመጣጣኝ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ዝቅተኛው የአንድ ቶን ፈርነስ ጭነት ከ600 ኬቪኤ በታች መሆን የለበትም፡፡ ሁሉም ጭነቶች በዚህ መሰረት የሚወሰኑ ይሆናሉ፡፡ ማንኛውም አቅርቦት ከዚህ ጭነት በታች ከሆነ አይፈቀድም፡፡

### 4.13 የውል ስምምነት

ሀ. ለሁሉም አዲስ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ጠያቂዎች በደንበኛው በሚቀርብ የቀረጥ ቴምብር ተያይዞ የውል ስምምነት በአመልካቹ እና ኢ.ኤ.አ መፈረም ይኖርበታል፡፡

ለ. የውል ስምምነት ቅጂ ለኃይል አቅርቦቱ ከከፈለ በኋላ ለደንበኛው ይሰጣል፡፡ ይህ የውል ስምምነት የሚያገለግለው ደንበኛው የኤሌክትሪክ አገልገሎት ተጠቃሚ መሆኑን እና የሚጠበቅበትን መብትና ግዴታ የሚገልጽ ሲሆን ለቦታ ይዞታ እንደ ግብዓት ወይም ማረጋገጫነት አያገለግልም፡፡

ሐ. ስምምነቱ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦቱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በየ5 ዓመቱ መታደስ የሚኖርበት ሲሆን ከሁለቱ ወገኖች በአንዱ ውሉ እስካልተቋረጠ ድረስ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

መ. በዚህ መመሪያ አማካኝነት የቀረበው መደበኛ (ስታንዳርድ) የስምምነት ፎርማት ለኢ.ኢ.ባ ቀርቦ መፅደቅ ያለበት ሲሆን በስምምነቱ ላይ የተካተቱ ዝርዝሮች ሊሻሻሉ

ይችላሉ፡፡ እነዚህ ፎርማቶች ተፈፃሚ ለሚሆኑባቸው መደቦች በኢ.ኤ.አ ድረ ገፅ የሚለቀቁ ይሆናል፡፡

ሠ. የኃይል አቅርቦቱ በቋሚነት የሚቋረጥ ከሆነ የውል ስምምነቱ ይቋረጣል፡፡

ረ. ተጠቃሚው በአባሪ 4.7 በቀረበው ቅጽ ካሳወቀ በኋላ ስምምነቱን ሊያቋርጥ ይችላል፡፡ የማስታወቂያ ጊዜው ለሁሉም ተጠቃሚዎች 30 ቀናት ሲሆን ይህ ማስታወቂያ ከተሰጠ በኋላ ድርጅቱ በቀጣዮቹ 30 ቀናት ውስጥ የሚከፈሉ ክፍያዎችን ለማይከፍል ደንበኛ "ምንም አይነት ቀሪ ክፍያ የለባቸውም" የሚል ማረጋገጫ የማይሰጠው ሲሆን በሁለቱም ሁኔታ የውል ስምምነቱ በቋሚነት ይቋረጣል፡፡ ክፍያውን ያልፈጸመ ደንበኛ ግን በህግ አግባብ ጉዳዩ እንዲጠየቅ ይደረጋል፡

ሰ. ነገር ግን ደንበኛው የውል ስምምነቱን 2 ዓመት ሳይሆነው የሚያቋረጥ ከሆነ፡-

1. ሁለት ዓመት ሳይሞላቸው ውል ለሚያቋርጡ ደንበኞች የ6 ወራት አማካይ የፍጆታ ክፍያ ተሰልቶ ሁለት አመት ለመሙላት ለቀሩት ወራት ከተባዛ በኋላ ደንበኛው እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሌሎች አስገዳች ሁኔታዎችን አያካትትም፡፡

2. ለበከ.መ፣ ለከ.መ፣ ለመ.መ፣ ለውሃ መሳቢያ ተጠቃሚዎች ሁለት ዓመት ሳይሆናቸው ውል የሚያቋርጡ ከሆነ ኤሌክትሪክ መስመሩን ለማንሳት አስፈላጊ የሆኑ ክፍያዎችን ደንበኛው መክፈል አለበት፡፡

ሸ. ስምምነቱ ሲቋረጥ ኢ.ኤአ የአገልግሎት መስመሩን አንስቶ ቀሪ ክፍያዎችን በማስከፈል ወይም ተገቢውን የእዳ ማካካስ ስራ ያከናውናል፡፡

ቀ. ስምምነቱ ሲቋረጥ ኢ.ኤአ በአባሪ 4.8 በቀረበው ፎርማት መሰረት ለተጠቃሚው የፅሁፍ ማስታወቂያ ይሰጣል፡፡

### 4.14 የአቅርቦት መነሻ ቦታ

ሀ. የአቅርቦቱ አገልግሎት መስጫ የኤሌክትሪክ ወጪ መስመር ተርሚናል በቅጥር ግቢው በአንድ ቦታ ላይ የሚቀርብ ይሆናል፡፡ ድርጅቱ አቅርቦቱ የሚሰጥበትን ቦታ ቆጣሪዎችንና ሌሎች መሳሪያዎች የሚተከሉበት ቦታ የምርመራ ሂደቱን እንቅፋት በማይፈጥርና በቀላሉ ሊደረስበት በሚችል ቦታ እንዲሆን ይወስናል፡፡

ለ. ሁሉም የ(በከመ) ፣(ከመ) እና (መመ) ተጠቃሚዎች፣ አመልካቾች ወደ ቆጣሪው የሚያመሩ ራሳቸውን የቻሉ ማስተላለፊያ መስመር እንዲኖሩ ማድረግ ያለባቸው ሲሆን መስመሮቹም ለተፈቀደላቸው የኢኤአ ሰራተኞች ለምርመራ በማንኛውም ጊዜ ክፍት መሆን አለባቸው፡፡

ሐ. ነገር ግን ልዩ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ድርጅቱ ከአንድ አቅርቦት በላይ በሆኑ ቦታዎች የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦቱን የተጠቃሚው ወይም የአመልካቹን ኤሌክትሪካል ኢንስታሌሽን ፕላን ፍላጎት መሰረት በማድረግ አቅርቦቱን ሊያከናውን ይችላል፡፡ ይህ አሰራር ራሳቸውን የቻሉ ቆጣሪዎች የሚተከሉበትና ለሁሉም በተተከሉ ቆጣሪዎች ላይ ያሉ ንባቦችን የሚመዘገብበትና እንደየ ታሪፍ አይነቱ የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

### 4.15 በኃይል አቅርቦት ቦታ ላይ የሚከናወን የኤሌክትሪክ መሳሪያዎች ተከላ

ሀ. የኃይል አቅርቦቱ መቅረብ ሲጀምር ተጠቃሚው ወይም አመልካቹ ከወጪ ተርሚናል ወይም ከቆጠሪ በኋላ Main switch/circuit breaker ያቀርባል፡፡

ለ. በተጨማሪም የከመ፣ የበከመ፣ የመመ ኃይል ተጠቃሚዎች (አመልካቾች) ተፈፃሚ በሚሆኑ ደንቦች መሰረት አስፈላጊውን ተስማሚ የኤሌክትሪክ ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎች በድርጅቱ ስፔሲፊኬሽን መሠረት ያቀርባሉ፡፡ እነዚህ መሳሪያዎች የኃይል አቅርቦት ከመሰጠቱ በፊት በድርጅቱ ስፔሲፊኬሽን መሰረት ትክክለኛነታቸው መጽደቅ ይኖርበታል፡፡

ሐ. የመመ፣ የከመ፣ የበከመ ተጠቃሚ/አመልካች ከሆኑ ቆጣሪ፣ circuit breaker እና ሌሎች ተያያዥ እቃዎች በኢ.ኤ.አ የኃይል አቅርቦት ቦታ (point of power supply) ላይ የሚተከል ይሆናል፡፡

መ. የመ.መ/የከመ/ የበከ.መ ተጠቃሚ/አመልካቾች በቬክተር ግሩፕ የሆኑና የዴልታ ዋይንዲንግ ስሪት ያላቸው በከ.መ በኩል እንዲሁም ስታር ዋይንዲንግ በዝ.መ በኩል ሆኖ ኒውትራሉ የተዘጋጀና የተቀበረ ስቴፕዳውን ትራንስፎርመር መትከል ይኖርባቸዋል፡፡

### 4.16 በተጠቃሚው ይዞታ ውስጥ የሚገኙ እቃዎች ላይ ስለሚደርስ ጉዳት፡-

ሀ. ቆጣሪ፣ የቆጣሪ ቦርዶች፣ የኃይል አቅርቦት ዋና መስመሮች፣ ኤም.ሲ.ቢ/ሲቢ፣ የኃይል ጭነት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች ወዘተ በማንኛውም መልኩ ባልተፈቀደለት ኢ.ኤ.አ ሰራተኛ/ተወካይ መነካካት፣ መዛወርና መነሳት የለባቸውም፡፡ ከተፈቀደላቸው ኤ.ኤ.አ ሰራተኞች  በስተቀር በቆጣሪ (በቆጣሪ አካሎች) ላይ እንዲሁም በኢ.ኤ.አ እቃዎች ላይ የተለጠፉ ወይም የታሰሩ ማሸጊያዎች በማንኛውም መልኩ መነካካት መሰበርና መቀየር የለባቸውም፡፡ በተጠቃሚው ይዞታ ውስጥ የሚገኙ የኢ.ኤ.አ ኤሌክትሪክ ኃይል መሳሪያዎችና በቆጣሪዎች ወይም በቆጣሪ አካሎች ላይ ያሉ እሽጎችን ተጠቃሚው በአግባቡ የመያዝና የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፡፡

ለ. በኢ.ኤ.አ መሳሪዎችና እቃዎች ላይ በቸልተኝነት ወይም በተጠቃሚው ወይም በተጠቃሚው ሰራተኞች ስህተት ጉዳት የሚደርስ ከሆነ ኢ.ኤ.አ የሚያቀርበው የጉዳት ወጪ በተጠቃሚው ይከፈላል፡፡ ደንበኛው እንዲከፍል የተጠየቀውን ክፍያ የማይፈጽም ከሆነ የውል ስምምነቱን እንደጣሰ ተቆጥሮ ኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦቱ ይቋረጣል፣ ክፍያውን እንዲከፈል በህግ አግባብ ይጠየቃል፡፡

## 4.17 የኤሌክትሪክ ኃይል ጠያቂ ተጠባባቂ ደንበኞች ዝርዝር

ሀ. ኢ.ኤ.አ ምዝገባቸውን መሰረት ያደረገ ለእያንዳንዱ ተጠቃሚ ልዩ የሆነ ቁጥር ይሰጣል፡፡ አመልካቾች ቀድሞ የመጣ ቀድሞ ይስተናገዳል በሚል መርህ ይስተናገዳሉ፡፡ ሆኖም በኢ.ኤ.አ ከሚሰጡት አገልግሎት አንጻር ቅድሚያ እንዲሰጣቸው የተፈቀደላቸው አመልካቾች ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

ለ. አካባቢን መሰረት ያደረገ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠባባቂ ደንበኞች ዝርዝር ወቅታዊ ሁኔታቸውን፣ የምዝገባ ቁጥር፣ በሁሉም የደንበኞች መስተንግዶ ቢሮዎችና በማዕከላዊ ጥሪ ሊያዝ የሚችል ሲሆን ይህ መረጃ በኢ.ኤ.አ በሚገኝ የማስታወቂያ ሰሌዳ የሚለጠፍና በየጊዜው ወቅታዊ እንዲሆን የሚደረግ ይሆናል፡፡

## 4.18 የሚደነገጉ ክፍያዎች

ሀ. ለኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት፣ መልሶ ለማገናኘት እና ግንኙነቱን ለማቋረጥ፣ አቅርቦት ለማሳደግ ወይም ለመቀነስ ወዘተ የሚከፈሉ የማመልከቻ እና የምዝገባ ክፍያዎች በኢ.ኤ.አ የሚወሰኑ ሆኖ ኢ.ኢ.ባ/መንግስት በሚያጸድቀው መሰረት ይሆናል፡፡

ለ. ደንበኛው የምዝገባ (Processing Fee)፣ የማስገመቻ፣ የማስቀጠያ የማቋረጫ እና ቅጣት ክፍያ ይከፍላል፡፡

ሐ. ለ(ሀ) እና (ለ) የሚቀርቡ የማመልከቻና የመመዝገቢያ ክፍያዎች በኢ.ኤ.አ የቀረቡ እና በኢ.ኢ.ባ ወይም በመንግስት የጸደቁ የማይመለሱ ክፍያዎች ሲሆኑ የመመዝገቢያ ክፍያ(Processing Fee) ተመላሽ የማይደረገው መስመሩ ፊዚብል ሳይሆን ሲቀርና ደንበኛው የጠየቀውን የኃይል ጥያቄ ሲያቋርጥ ብቻ ፡፡

## 4.19 የዋስትና ተቀማጭ ገንዘብ

ሀ. ከቅድመ ክፍያ ቆጣሪ ተጠቃሚዎች በስተቀር በድህረ ክፍያ ቆጣሪ ሁሉም የሶስት ፌዝ ተጠቃሚዎች፣ ሁሉም የንግድ ተቋማት፣ የባንክ ሽፋን በደረሰባቸው አካባቢዎች የሚገኙ የነጠላ ፌዝ የመኖሪያ ቤት ደንበኞች ስታፍን ጨምሮ የባንክ አካውንት በማምጣት በባንክ ለመክፈል ፈቃደኛ ስለመሆናቸው ስምምነት ይፈርማሉ፡፡

ለ. ከ10 ሜጋ ዋት በላይ ለሚጠይቁ ደንበኞች የተገመተው የኃይል ፍጆታ እና የዋስትና ገንዘብ መጠን አዲስ ደንበኞች እና ነባር ደንበኞች ተቀማጫቸውን እንዲያስተካክሉ ኢኤአ በሚያጸድቀው መመሪያ መሰረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

ሐ. ከ10 ሜጋ ዋት በላይ እየተጠቀሙ ያሉ የኤሌክትሪክ ኃይል ጭነትን ለማሻሻል ጥያቄ ሲቀርቡ ጥያቄ ለቀረበበት ተጨማሪ ኃይል ብቻ የሚሰላ የዋስትና ገንዘብ ገቢ ይደረጋል፡፡

መ. የዋስትና ገንዘብ መጠኑ ተፈፃሚ በሚሆነው የተመን ስሌት መሰረት የሚከለስ ይሆናል፡፡

ሠ. ከ10 ሜጋ ዋት በላይ ተጠቃሚ ደንበኛ የሚከተሉት ሁኔታዎች ካሉ ተጨማሪ ዋስትና ገቢ እንዲያደርጉ ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡

1. ለአዲስ ደንበኛ ቀድሞ ከከፈለው ተቀማጭ ተጨማሪ ማስከፈል ሲያስፈልግ ጭማሪው ተፈጻሚ የሚሆነው አንድ የበጀት አመት ካበቃ በኋላ መሆን አለበት፡፡

2. መከፈል የሚገባው ተጨማሪው የዋስትና ገንዘብ ቀደም ብሎ ገቢ ከተደረገው የዋስትና ገንዘብ 10% የሚበልጥ ከሆነ ተጨማሪ ዋስትና ገንዘብ ገቢ እንዲደረግ ይጠየቃል፡፡

3. የዋስትና ገንዘቡ ቀሪ ክፍያዎች ወይም እዳ ካለ ውል በሚቋረጥበት ጊዜ እንዲቀናነስ ይደረጋል፡፡

4. ገቢ የተደረገው የዋስትና ገንዘብ በማናቸውም ምክንያት ሲሰረዝ ወይም በቂ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር፤

ለ. ቀደም ሲል የዋስትና ገንዘብ የከፈሉ ደንበኞች እዳ ካለባቸው ውል በሚቋረጥበት ጊዜ እንዲቀናነስ ይደረጋል፡፡

ረ. ከ10 ሜጋ ዋት በላይ ተጠቃሚ የሆነ ደንበኛ ተፈላጊውን ተጨማሪ የዋስትና ገንዘብ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ገቢ ያደርጋል ወይም የባንክ ጋራንቲ ያስይዛል፡፡ ይህ ገንዘብ ገቢ የማይሆን ከሆነ ወይም የባንክ ጋራንቲ የማይቀርብ ከሆነ ክፍያው እስከሚከፈል ድረስ ኢ.ኤ.አ የኤሌክትሪክ አቅርቦቱን ያቋርጣል፡፡

ሐ. ቀደም ሲል ገቢ የተደረገው የዋስትና ተቀማጭ ከሚፈለገው ዋስትና መጠን 20% በላይ ትርፍ ሆኖ ከተገኘ ትርፍ የሆነው ገንዘብ ለሃይል ፍጆታ ክፍያ ሊከፈልለት ወይም ደግሞ ተመላሽ ሊደረግለት ይችላል፡፡

መ. የዋስትና ገንዘብ ለደንበኛው ተመላሽ የሚሆነው ስምምነቱ ሲቋረጥና በቋሚነት የኃይል አቅርቦቱ ሲቋረጥ እንዲሁም ቀሪ ክፍያዎች ከተስተካከሉ በኋላ በ30 ቀናት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ነገር ግን በኢ.ኤ.አ ምክንያት ክፍያው ከ90 ቀናት በላይ ከዘገየ በወቅቱ ባለው የባንክ ወለድ መሰረት ለተጠቃሚው የሚከፈል ሲሆን በደንበኛው ምክንያት ከዘገየ ወለድ ሳይኖረው ዋናው ተቀማጭ ብቻ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

ቀ. ከ10 ሜጋ ዋት በላይ ደረጃ በደረጃ ለሚቀርብ የኃይል ጥያቄ ገቢ የሚደረገው የዋስትና መጠን እንደ አቅርቦቱ ተከፋፍሎ ስምምነት ላይ በተደረሰበት ፍላጎት መሰረት ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ ከዚህ ተከትሎ አስፈላጊ የሆነው ተጨማሪ የዋስትና መጠን ተጨማሪ የኃይል ጭነት ከመለቀቁ ከ30 ቀናት በፊት ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡

በ. ከ10 ሜጋ ዋት በላይ ለሆነ የኃይል ጥያቄ ድርጅቱ በተጠቃሚው/አመልካቹ የዋስትና ገንዘብ ገቢ እስኪደረግ ወይም የባንክ ጋራቲ እስኪቀርብ ድረስ ሀይሉን አይለቅም፡፡

### 4.20 የአዲስ ኃይል የማገናኘት እና የኃይል ማሻሻያ የአገልግሎት ዋጋ

ሀ. ተጠቃሚው የኤሌክትሪክ ኃይል የአገልግሎት መስመሮችን ወዘተ እንዲሁም የኤሌክትሪክ ጭነት ክፍያዎችን፣ የዝርጋታ ክፍያዎችን (development cost) እንዲሁም ለአዲስ ኃይል ማገናኘት፣ ማሻሻያ ክፍያዎችን ለኢ.ኤ.አ ይከፍላል፡፡ ክፍያውም ቀድሞ በተቀመጠ የክፍያ ስርዓት፣በኢ.ኤ.አ ወይም በመንግስት የጸደቀ የዋጋ ተመን ወይም (አንቀጽ4.6) እንደተገለጸው ትክክለኛው የስራ ወጪ በኢ.ኤ.አ ይዘጋጃል፡፡

ለ. ከአንድ ፌዝ ወደ ሶስት ፌዝ (ዝመ) ወይም ከሶስት ፌዝ ወደ አንድ ፌዝ ለመቀያየር እና (ከዝ.መ) ወደ (ከ.መ) እንዲሁም (ከከ.መ) ወደ (ዝ.መ) ለመቀያየር በአንቀፅ 3 የቀረቡት አሰራሮች ሊተገበሩ ይገባል፡፡

### 4.21 የክፍያ ዘዴ

ሀ. ሁሉም ክፍያዎች እስከ 4000 ብር ድረስ በጥሬ ገንዘብ መክፈል የሚቻል ሲሆን ከ4000 ብር በላይ ለሆኑ ክፍያዎች በባንክ ቼክ፣ ሲ.ፒ.ኦ እና ድራፍት ሰነድ ይከፈላሉ፡፡ የክፍያ ቼኮችና ሲፒኦዎች ወይም ድራፍቶች በማናቸውም ለድርጅቱ አቅራቢያ በሚገኝ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ሊመነዘሩ የሚችል መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ለ. በቼክ/በሲፒኦ የቀረበ ክፍያ ቼኩ/ሲፒኦው በኢ.ኤ.አ ቢሮ በደረሰበት ቀን እንደተከፈለ የሚታሰብ ሲሆን ይህም ቼኩ/ሲፒኦው በባንኩ በቀረበ በ7 ቀናት ውስጥ ባንኩ ክፍያ የሚፈፅም ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ቼኩ/ሲፒኦ ለባንክ ከቀረቡ በ7 ቀናት ጊዜ ውስጥ ተቀባይነት ካላገኙ አመልካቹ የቼኩን/ሲፒኦ መጠን በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ ድራፍት ቼኩ/ሲፒኦ ያልተመነዘረበትን ቅጣት ብር 100 ወይም 3 ፐርሰንት ከሁለቱ ከፍተኛውን ጨምሮ ወይም ኢ.ኤ.አ በሚወስነው መሰረት የሚከፍል ሲሆን ተጠቃሚው ተፈፃሚ በሚሆኑ ህግጋት መሰረት ሌሎች እርምጃዎች ሊወሰዱበት ይችላል፡፡

ሐ. ከ10 ሜጋ ዋት በላይ ለሆኑ አዲስ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ጥያቄዎች ደንበኛው ለዋስትና ተቀማጭ ለአምስት አመት የሚያገለግልና በአቅራቢያው ከሚገኝ ንግድ ባንክ በሚቀርብ የባንክ ዋስትና (bank guarantee) የመክፈል አማራጭ ይኖረዋል፡፡ ዋስትናውን ለተጨማሪ 5 ዓመታት የተያዘለት የዋስትና ዘመኑ ከማለቁ 3 ወራት በፊት የማሳደስ ሀላፊነት የተጠቃሚው ይሆናል፡፡

መ. ይህ ፕሮሲጀር ከመሻሻሉ በፊት የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ የሆኑ ደንበኞች ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር በመፈራረም የተጠቀሙበትን ወርሃዊ ፍጆታ ከባንክ አካውንታቸው ተቀናሽ በማድረግ እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

ሠ. የቅድመ ክፍያ ቆጣሪ አክሰስ ባልደረሰባቸው አካባቢዎች የድህረ ክፍያ ቆጣሪ የሚገናኝላቸው ሁሉም የሶስት ፌዝ ተጠቃሚ ደንበኞች፣ ሁሉም የንግድ ተቋማት፣ የባንክ ሽፋን በደረሰባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ የነጠላ ፌዝ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚዎች ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር የደንበኝነት ውል ሲያስሩ የተጠቀሙበትን ወርሃዊ ፍጆታ ከባንክ አካውንታቸው ተቀናሽ በማድረግ ለመክፈል መፈረም ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 4.22 በተጠቃሚው ቅጥር ግቢ የሚከናወን የኤሌክትሪክ ሽቦ ዝርጋታ

ሀ. በተጠቃሚው ቅጥር ግቢ የሚከናወን የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ፍቃድ ባለው ኤሌክትሪክ ተቋራጭ በኢትዮጵያ በተቀመጠ የጥራት ደረጃዎች የተሰራ መሆን የሚገባው ሲሆን ለኤሌክትሪክ ዝርጋታ የሚውሉ እቃዎችም በዚሁ የጥራት ደረጃ የሚገኝ መሆን አለበት፡፡ የጥራት ደረጃዎችም እንደ አስፈላጊነቱ ለደንበኞች በመገናኛ ዘዴዎች እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

ለ. ሁሉም ከፍታ ያላቸው ህንጻዎች ማለትም ከመሬት 15 ሜትር በላይ ከፍታ ያላቸው ህንፃዎች በኢትዮጵያ ኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 እንዲሁም በአዋጁ መሰረት የወጡ መመሪያዎችንና ደንቦችን ማክበር ይኖርባቸዋል፡፡

## 4.23 የAC ሞተሮች ተከላ

ሞተሩ እና የሞተር ተከላው የመነሻ ከረንታቸው ከዚህ በታች በተጠቀሰው መሰረት መጥነው የሚለቁ መሳሪያዎች እስከ ሚገጠሙ ድረስ ማንኛውም የAC ሞተሮች ከዩቲሊቲው ዝቅተኛ ወይም መካከለኛ የቮልቴጅ ሲስተም ጋር መገናኘት አይችሉም፡፡

ሀ. በሶስት ፈረስ ጉልበት ወይም ከዚያ በላይ ያላቸው የኢንዳክሽን ሞተሮች ወይም 1Kva ወይም ከዛ በላይ ያላቸው የመበየጃ ትራንስፎርመሮች በተጠቃሚው ተገቢው ደረጃ ያላቸው ካፓሲተሮች እስካልተተከሉ ድረስ ከዝቅተኛ ወይም መካለኛ ቮልቴጅ ሲስተም ጋር መገናኘት አይችሉም፡፡ ተጠቃሚው ይህን ማድረግ የሚፈልግ ከሆነ በነዚህ ሞተሮች እና የመበየጃ ትራንስፎርመሮች ላይ በዚህ መመሪያ በተጠቀሰው መሰረት አማካይ ወርሃዊ የፓወር ፋክተርን ለማግኘት ተገቢው ደረጃ ያላቸው ካፓሲተሮችን መትከል ይኖርበታል፡፡

ለ. ዝቅተኛ ወይም መካከለኛ ቮልቴጅ የሚጠቀሙ ሞተሮች ከመቆጣጠሪያ መሳሪያ ጋር የሚቀርቡና በበቂ ሁኔታ የደንበኛውን ከፍተኛ የከረንት ጭነት ለመቆጣጠር ሲሆን ይህም ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ የተዘረዘረውን ገደብ እንዳያልፉ ቁጥጥር ለማድረግ ነው፡፡

| የአቅርቦት አይነት | የተከላ መጠን | ከፍተኛው የከረንት ጭነት |
|---|---|---|
| ነጠላ ፌዝ ወይም 3 ፌዝ | ሀ. እስከ 1 የፈረስ ጉልበት | -ከሙሉ ጭነት ከረንት 6 እጥፍ፡፡ |
| | ለ. ከአንድ የፈረስ ጉልበት በላይ እስከ 10 የፈረስ ጉልበት | -ሶስት እጥፍ ከሙሉ ከረንት ጭነት |
| | ሐ. ከ10 የፈረስ ጉልበት በላይ እስከ 15 የፈረስ | -ሁለት እጥፍ ከሙሉ ከረንት ጭነት |

| | | |
|---|---|---|
| | ጉልበት<br>መ. ከ15 የፈረስ ጉልበት በላይ | -አንድ ተኩል ከሙሉ ከረንት ጭነት |

ከላይ የተጠቀሱትን ቅድመ ሁኔታዎች ያላሟላ ተጠቃሚ ኤሌክትሪክ ኃይል እንዲቆረጥበት ይደርጋል፡፡ ኢ.ኤ.አ በቦታው እና በስራው ባህሪ መሰረት የመነሻ ከረንቱን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

ሐ. ኖ-ቮልት የተገጠመለት ባለ 3 ፖል የተያያዘ ስዊች ሞተር ሰርኪውቱን እና የሶስት ፌዝ ፊዊዝን (ከአቅም በላይ ጭነት) ይቆጣጠራል፡፡ ይህ መቆጣጠሪያ በጥሩ ሁኔታ የሚሰራ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ለሞተሮች የሚደረገው የዝርጋታ ስራ በሁሉም 3ፌዝ ሽቦዎች በብረት ኮንዲውት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡ የሽቦ ዝርጋታው ግራውንዱ ከሞተሩ ፍሬም ጋር በሁለት ራሳቸውን በቻሉ ግራውንድ ሽቦዎች መገናኘት ይኖርበታል፡፡ አነስተኛው የተፈቀደው ወደ መሬት የሚቀበረው የሽቦ መጠን 14SWG (standard wire gage) ነው፡፡

መ. ጠቅላላው የሀርሞኒክ ቮልቴጅ መለዋወጥ ከዚህ በታች ከተገለጸው መጠን መብለጥ የለበትም፡፡

(በከ.መ)= 4%

(ከ.መ) = 5%

(መ.መ)=7%

(ዝ.መ) = 10%

ለሁሉም ከ15 ኪዋት በላይ ለሚጠቀሙ የንግድ ተጠቃሚዎች የሚተከሉ የሀርሞኒክ ፊልተሮች ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ1 ዓመት ጊዜ ውስጥ እንዲተከሉ ጊዜ እንዳለቸው ኢ.ኤ.አ በማስታወቂያ መንገር ይኖርበታል፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ግን በእንደነዚህ አይነት ተጠቃሚዎች ላይ ተከላውን ማከናወን እንደ ግዴታ ይቀመጣል፡፡

ሠ. ከዚህ በተጨማሪም wattless ከረንትን የሚቆጣጠር ከsyncroneous ሞተር ጋር አብሮ የሚገጠም መሳሪያ ሊገጠምላቸው ይገባል፡፡

## 4.24 የመስኖ/የእርሻ ፓምፕ ገጠማ

ሁሉም አዳዲስ የፓምፖች ማገናኘት አቅርቦት/መልሶ ማገናኘት በተቻለ መጠን አነስተኛ ብክነት እንዲኖር ማድረግ ያለባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ከኃይል አቅርቦት ውጤታማነት ቅድመ ሁኔታዎች ጋር አብረው የሚሄዱና የሚከተሉትን ክፍሎች ያካተቱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ሀ. ሰበቃን የሚቀንሱ የግርጌ ቫልቮች፣

ለ. የHDPE ቱቦ መሳቢያ እና ማቅረቢያ፣

ሐ. የጥራት ደረጃ ምልክት (ሰርተፍኬት) የተደረገባቸው የኃይል ቆጣቢ አጠቃቀም ባለ 1 ብሎክ pumpset

መ. ተመጣጣኝ የሆነ ደረጃ ያለው የፓምፕ ካፓሲተር ኢ.ኤ.አ ከተገቢው/ከሚመለከተው ባለስልጣን/ኤጀንሲ የውሃ መጠን የሚገልጽ መረጃ ይሰበስባል፡፡ የተሰበሰበው መረጃ የኃይል ጭነት መጨመር ካሳየ ተጠቃሚው ተጨማሪ የተገኘውን የኃይል ጭነት ማሻሻል ይጠበቅበታል፡፡

## 4.25 ከኢ.ኤ.አ የኃይል አቅርቦት ጋር በ Parallel የሚከናወን ስራ

ሀ. ደንበኞች ከሚቀርብላቸው የኃይል ግሪድ ጋር Parallel ጀኔሬተር መጠቀም የሚፈልጉ ከሆነ ተጠቃሚዎቹ የጀኔሬተሩን ተከላ ከኢ.ኤ.አ ሲስተም ጋር በማይፃረር መልኩ ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

ለ. ኢ.ኤ.አ በParallel በሚከናወነው ስራ ምክንያት በተጠቃሚው የማመንጫ መሳሪያ፣ ማሽን ወይም እቃዎች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ወይም ለተከሰተ ተያያዥ ችግር ተጠያቂ አይሆንም፡፡

ሐ. ከግሪድ ጋር Parallel ለሚሰራ ስራ ተጠቃሚው በፖሊሲና ፕሮሲጀር የኤሌክትሪክ ግሪድ ቅድመ ሁኔታዎችንና ሌሎች ደንቦችን ማክበር እንዲሁም በኢ.ኤ.አ የፀደቁ ተያያዥ ክፍያዎችን መክፈል ይኖርበታል፡፡

መ. Parallel የኦፐሬሽን ስራውን ከብሄራዊ የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ LDC (load dispatch center) ጋር በቅንጅት መስራት አለበት::

ሠ. ነባር የኢ.ኤ.አ ስምምነቶች ካሉ ስምምነቱ እስኪቋረጥ ድረስ የParallel ስራ ክፍያዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## 4.26 ከለላ የሚደረግለት የኃይል ጭነት

ኢ.ኤ.አ ልዩ ሁኔታዎች ከለላ የሚደረግለት ኤሌክትሪክ ጭነትን ሊፈቅድ የሚችል ሲሆን ይህ ሁኔታ በተጠቃሚዎች ስምምነቶች ውስጥ መካተት ይኖርበታል፡፡ እነዚህ ተጠቃሚዎች በሚከተሉት ዝርዝር ሁኔታዎች መሰረት የ24 ሰዓት ኃይል አጠቃቀምን የሚመርጡ ናቸው፡፡

ሀ. በወቅቱ ተፈጻሚ በሚሆነው የታሪፍ ሰንጠረዥ መሰረት በየወሩ በመደበኛው ክፍያ ደረሰኝ አማካኝነት ተጨማሪ ክፍያ ይከፈላል፡፡

ለ. ከለላ የተደረገለት ጭነት ለድንገተኛ ጊዜ ሁኔታዎች የተጋለጠ ሊሆን ይችላል፡፡

ሐ. ከለላ የተደረገለት ጭነት በተጨማሪም ለመብራት፣ ለአየር ሁኔታ ማስተካከያ እና ለመጠጥ ውሃ አገልግሎት ይውላል፡፡

መ. ለከለላ ጭነት (ፕሮቴክቲቭ ሎድ) ሁኔታዎችን የሚመቻቹለት ተጠቃሚ በፕሮግራም በመንግስትም ሆነ በኢ.ኤ.አ የሚጣሉ የኃይል መቋረጥ ሁኔታዎች ተፈፃሚ አይሆኑበትም፡፡ ኃይል በሚቋረጥበት ጊዜ የከለላ የኤሌክትሪክ ኃይል ጭነቱ ከቀረበውና ከተወሰነው የከለላ ጭነት በላይ አይሆንም፡፡

ሠ. የከለላ የኤሌክትሪክ ኃይል ጭነቱ ራሱን በቻለ ባለ 15 ኪ.ቮ እና ከዚያ በላይ መጋቢ መስመር ከግሪድ ሰብስቴሽን ኃይል ለሚቀርብላቸው ተጠቃሚዎች ብቻ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

ረ. ከለላ የተደረገለት የኃይል ጭነት በኢ.ኤ.አ ላይ ቀሪ ክፍያ ላለበት ተጠቃሚ አይለቀቅም ወይም አገልግሎቱ አይቀጥልም፡፡ በፍርድ ቤት የተያዙና ውሳኔ የሚጠብቁ ክፍያዎች እንደቀሪ ክፍያ አይወሰዱም፡፡

ሸ. ኢ.ኤ.አ በLDC/ አንድ ተጠቃሚ ባልተፈቀደለት ጊዜ ኃይል እየተጠቀመ መሆኑን፣ ከተቀመጠው እና ከተወሰነው የከለላ ኃይል ጭነት በላይ እየተጠቀመ መሆኑን መረጃ ከደረሰው ለተጠቃሚው ኃይል የሚሰጡት መጋቢ መስመሮች ተከፍተው ሀይሉ እንዲቋረጥ ይደረጋል፡፡

## 4.27 የአገልግሎት መስመር እና መሳሪያዎችን በተመለከተ አጠቃላይ ሁኔታዎች

ሀ. ተጠቃሚው ሀይሉ እስከሚቀርብበት ቦታ ድረስ ለመስመር ዝርጋታ ትራንስፎርመር ለመትከልና ቆጣሪ ለማስቀመጥ በሁለቱም ስምምነት በራሱ ይዞታ ላይ አመች የሆነ ቦታ ያዘጋጃል፤ ሆኖም በትራንስፎርመርና ተዛማጅ እቃዎች ላይ ለሚደርስ ጉዳት በተመለከተ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

- በደንበኛው ምክንያት ትራንስፎርመርና ተዛማጅ እቃዎች ቢቃጠሉ ወይም ጉዳት ቢደርስባቸው ደንበኛው ሙሉ ወጭውን ይሸፍናል፡፡ በደንበኛው በራሱ ለሚቀርቡ ትራንስፎርመርና ተዛማች እቃዎች በዋስትና ጊዜ ውስጥ የጥራት ችግር ካጋጠመ እና ደንበኛው ኃይል ከተቋረጠበት የእቃ አቅራቢው ድርጅት ወይም የደንበኛው ሃላፊነት ይሆናል፡፡
- በሶስተኛ ወገን በማንኛውም የኤሌክትሪክ አውታሮች ላይ የሚደርሱ ጉዳዮች በህግ አግባብ የሚፈጸም ይሆናል፡፡
- ትራንስፎርመርና ተዛማጅ እቃዎች የቀረበው በኢ.ኤ.አ ወይም በደንበኛው ሆኖ (ከዋስትና ጊዜ ውጭ) በማንኛውም ጊዜ ጉዳት ቢደርስባቸው በግምት ሂሳብ ክፍያ ወቅት የጥገና ወጭ ክፍያ የጠቅላላውን የእቃ ዋጋ 25% ቀደም ሲል የከፈሉ ከሆነ ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ያለምንም ተጨማሪ ክፍያ ጉዳት የደረሰበት እቃ ይተካለታል፡፡
- ነገር ግን ከላይ የተጠቀሰውን 25% የጥገና ወጭ ያልከፈለ ደንበኛ ትራንስፎርመርና ተዛማጅ እቃዎች ቢቃጠልበት ወይም ጉዳት ቢደርስበት

የቀረበው በግለሰቡ በራሱ ከሆነ እና ከዋስትና ጊዜ ውጭ ለሚደርስ ጉዳት የእቃውን ሙሉ ዋጋ ደንበኛው ከሸፈነ በኋላ ተጨማሪ ለቀጣዩ ጥገና 25% የትራንስፎርመርና ተዛማጅ እቃዎች ከፍሎ ጥገና ይከናወንለታል፡፡

- ጉዳት የደረሰበት እቃ በተለይ ትራንስፎርመር በተመሳሳይ ለመተካት የማይቻል /እቃው ባለመኖሩ ምክንያት ወደ ቀጣዩ ሬቲንግ የሚቀየር ከሆነ የእቃ ዋጋ ልዩነት መከፈል ይኖርበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሁለቱ እቃዎች የዋጋ ልዩነት የጥገና ወጭ (25%) ልዩነት መከፈል ይኖርበታል፡፡

<u>ማሳሰቢያ</u>

የእቃዎች የዋጋ ልዩነት እና የጥገና ወጪ (25%) ልዩነት ግምት ውስጥ የሚገባው የእቃዎቹ ዋጋ ግምት በሚከፈሉበት ወቅት የሚኖረው ወቅታዊ ዋጋ ይሆናል፡፡

ለ. ከአንድ በላይ ፎቅ ባላቸው ህንጻዎች ላይ የቱንም ያህል ወለል በህንጻዎቹ ላይ ቢኖር ከመሬት በላይ በሚዘረጉም ሆነ በመሬት ስር በሚቀበሩ ኬብሎች አማካኝነት የሚከናወኑ ዝርጋታዎች ከመጀመሪያው ወለል የሚሳቡ ይሆናል፡፡ በደንበኛው ጥያቄ መሰረት መስመሮቹ የሚገናኙበት በህንጻው መሰረት ባለው ወለል ላይ ሆኖ ቆጣሪዎች ማብሪያ ማጥፊያዎች ከህንፃው ውጪ ራሱን የቻለ መግቢያ ያለውና በቂ ቦታ ያለው አየር ማስገባት የሚችል የእሳት አደጋ መከለያ ያለው የውሃ ፍሳሽና እርጥበት የማያስገባ መሆን አለበት፡፡

ሐ. ከአንድ በላይ ፎቅ ያላቸው ህንፃዎች ተስማሚ በሆነ ቦታ ከክፍያ ነፃ ለኢ.ኤ.አ ትራንስፎርመሮች፣ ስዊች ጊር ወዘተ መትከያ መዘጋጀት አለበት፡፡

መ. ከአንድ በላይ ወለል ባላቸው ህንፃዎች እና ጠቅላላ የወለል ስፋታቸው 900 ካ.ሜና ከዛ በላይ ለሆኑ ህንፃዎች ከወለል በላይ ሶስት ፎቆች (G+3) ለዝቅተኛ መስመር የኃይል አቅርቦት፡-

I. በኮንክሪት የተሰራ ጣሪያ የተገጠመለት እና 6 ሜትር በ4 ሜትር የሆነ ስፋት ያለው ክፍት ቦታ፤ መቆለፍ የሚችል፣ ንፋስ ማውጫ ያለው፣ በቂ የሆነ ኬብል ማስተላለፊያ ቱቦ

ያለው፣ መሬት ላይ የሚቀመጥለት ማሰራጫ ትራንስፎርመር እና ከዚህ ጋር የተያያዘ የስዊች ጊር እቃዎች ከህንፃው አጠገብ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

II. ከቤት ውጪ ስፋቱ 10 ሜትር በ4 ሜትር ወይም 5 ሜትር በ5 ሜትር የሆነ ጣሪያ የሌለው ከተቻለ በዋናው መግቢያ አጠገብ ለትራንስፎርመርና ስዊችጊር መትከያ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

III. በሰብስቴሽን/ስዊች ስቴሽን በንግድ ቦታዎች ማለትም ጠቅላላ የሚቀርበው ኃይል ከ15/33 ኬ.ቪ. ሰብስቴሽን ግንባታ የሚያስፈልግ ከሆነ ለዚሁ በኢ.ኤ.አ በሚገለፀው መሰረት ቦታ መዘጋጀት አለበት፡፡

ሠ. የክሊራንስ ዝርዝር፤ ከመሬት በላይ የተዘረጉ መስመሮችን ስታንዳርድና በመካከል ያለውን ርቀት እንዲሁም የአቅርቦት ጥራትን በተመለከተ በኢ.ኢ.ባ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ይፈጸማል፡፡

ረ. ትራንስፎርመር ስዊችንግ ስቴሽንና ሰብስቴሽን ለመገንባት፣ ስፋቱ ከ3 ሜትር የማያንስ ከዋናው መንገድ ወደ ኤሌክትሪክ ክፍል እንዲሁም ትራንስፎርመር ወደ ሚተከልበት መግቢያ መንገድ መኖር አለበት፣ ለኤሌክትሪክ ክፍል/ክፍት ቦታ ለትራንፎርመር፣ ተያያዥ ስዊች ጊር እና ሰብስቴሽን/ስዊች ስቴሽን መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

### 4.28 ኢ.ኤ.አ የተጠቃሚዎችን የኃይል መስመር ስለ ሚጠቀምበት ሁኔታ

ሀ. ኢ.ኤ.አ የኤሌክትሪክ ኃይል መስመሩንና ሌሎች መሳሪያዎችን ይህን የኤሌክትሪክ መስመርና መሳሪያ ለመጠቀም ክፍያ የፈፀመው ተጠቃሚ በአገልግሎት አጠቃቀሙ ላይ ችግር እስካልፈጠረበት ድረስ መስመሮቹንና መሳሪያዎቹን ለሌሎች ተጠቃሚዎች ኃይል አቅርቦት ሊጠቀምበት ይችላል፡፡

ለ. ከዚህ በተጨማሪም በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት የኤሌክትሪክ ኃይል መስመሩን ለመጠቀም ክፍያ የፈፀመው ተጠቃሚ የኤሌክትሪክ ኃይሉ ቢቋረጥበት ኢ.ኤ.አ የኤሌክትሪክ ኃይሉንና ሌሎች መሳሪያዎችን የመጠቀም መብት አለው፡፡ ኢ.ኤ.አ በዚህ ሁኔታ ለሌሎች ተጠቃሚዎች መስመሩን እና የኤሌክትሪክ መሳሪያዎች ኤሌክትሪክ ኃይል

ለማቅረብ ቢጠቀምም ለመስመሮቹ እና ለመሳሪያዎቹ ጥቅም ቀድሞ ክፍያ ለፈፀመው ተጠቃሚ የመክፈል ግዴታ የለበትም፡፡

ሐ. ነገር ግን በተቻለ መጠን ኢ.ኤ.አ የተለየ ማስተካከያ እስከሚደረግ ድረስ ሌላ አማራጭ ለመጠቀም ጥረት ማድረግ እንዳለበት በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ለዚህም ሲባል ኢ.ኤ.አ ከደንበኛው ጋር የሁለትዮሽ ስምምነት በማድረግ በነባሩ ኤሌክትሪክ መስመር ላይ ተከላውን እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡

መ. ከማከፋፈያ ጣብያ የራሳቸው የሆነ መስመሮች (Dedicative Lines) የተዘረጋላቸውን ደንበኞች አስመልክቶ ግን ጉዳያቸው የሚታየው በዚህ ፕሮሲጀር አንቀጽ 3.3 መሰረት ይሆናል፡፡

### 4.29 ወደ ተጠቃሚው ቅጥር ግቢ ስለ መግባት

ኢ.ኤ.አ ወይም በኢኤአ የተፈቀደለት ሰራተኛ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሰራተኛ መሆኑን የሚገልጽ መታወቂያ ወይም ማስረጃ በማሳየት እና የመጣበትን ዓላማ በግልጽ በማስረዳት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይችላል፡-

I. የኢ.ኤ.አ ንብረት የሆኑ የኤሌክትሪክ ኃይል መስመሮች፣ ቆጣሪዎች፣ መገጣጠሚያዎች፣ መሳሪያዎች እና ቁሳቁሶችን ለመመርመር ወይም ለመፈተሽ፣ ለመለወጥ፣ ለመጠገን እንዲሁም ለማስተካከል፤

II. በኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት መስመሩ ላይ ያለውን የኃይል መጠን ለማረጋገጥ፣ የቆጣሪ ፍጆታ ለማንበብ እና ባልተከፈለ ሂሳብ ምክንያት የኃይል አቅርቦት ማቋረጥ፤

III. የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦቱ በማይፈለግበት ጊዜ የኃይል አቅርቦቱን ለማንሳት ወይም ኢ.ኤ.አ ስልጣን ባለው አካል እንዲያነሳ ሲታዘዝ የኃይል መስመሮችን፣ ቆጣሪዎችን፣ መገጣጠሚያዎችን እና ሌሎች የድርጅቱ መሳሪያዎችን ለማንሳት ወደ ደንበኛው ቅጥር ግቢ መግባት ይችላል፡፡

**4.30 የተለየ የደህንነት ጥበቃ ለሚደረግላቸው ድርጅቶች ወይም ተጠቃሚዎች** ከላይ በአንቀጽ 4.29 ስር የተዘረዘሩት ተግባራት እንዳሉ ሆነው ኢ.ኤ.አ ለባለ ይዞታው ወይም

ድርጅቱ ከ24 ሰዓት ያላነሰ የቅድሚያ ማስታወቂያ በመስጠት አስፈላጊውን ከኤሌክትሪክ ስራዎች ጋር የተያያዥ ስራዎችን ሊሰራ ይችላል፡፡

4.31 **በኢ.ኤ.አ የተፈቀደለት ሰራተኛ** ከላይ በ4.29 ለተጠቀሱት ስራዎች ደንበኛው ወደ ቅጥር ግቢው እንዳይገባ የሚከለክል ከሆነ ወይም ሰራተኛው ወደ ቅጥር ግቢ እንዲገባ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን የማያመቻች ከሆነ ኢ.ኤ.አ ማስታወቂያውን ከሰጠ ከ24 ሰዓት በኋላ ይህ የተጠቃሚው እንቢተኝነት እስከቀጠለ ድረስ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦቱን ሊያቋርጥ ይችላል፡፡ ነገር ግን ሃይል ተቋርጦም እንዲገባ የማይፈቀድለት ከሆነ ከሚመለከታቸው ህግ አስከባሪዎች ጋር በመሆን ሊያስገድድ ይችላል፡፡

4.32 **ማንኛውም በኢ.ኤ.አ ውክልና የተሰጠው ሰራተኛ**

ሀ. የኤሌክትሪክ ኃይል ያላግባብ ጥቅም ላይ መዋሉን ካመነበት ወደ ይዞታው በመግባት ይዞታውን በሙሉ መፈተሽ እና መመርመር ይችላል፡፡

ለ. ያልተፈቀደ የኤሌክትሪክ ኃይል አጠቃቀም ማስቆምና ጥቅም ላይ የዋሉ ማናቸውንም መሳሪያዎች፣ ቁሳቁሶች ወይም ሌሎች እቃዎችን መያዝ ወይም መንቀል ይችላል፡፡

ሐ. ከላይ በፊደል ተራ (ሀ) የተጠቀሱትን ጥፋቶች በማስረጃነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን መዛግብትና ሰነዶች መያዝና እነዚህን ሰነዶች የሚይዘው ግለሰብ በተገኘበት ቅጂዎችን መውሰድ ይችላል፡፡ ምርመራ እና ፍለጋ የሚደረግበት ባለ ይዞታ ወይም የባለይዞታ ወኪል በፍተሻና በምርመራው ወቅት መገኘት የሚኖርበት ሲሆን በዚህ የምርመራና ፍተሻ ተግባር የተገኙ ማናቸውንም ግኝቶች በዝርዝር በመያዝ ለባለ ይዞታው ወይም ወኪሉ በማስፈረም መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ይህ ዓይነቱ የፍተሻ ጊዜ ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12፡00 ሰዓት በመኖሪያ ቤቶች መከናወን አይችልም፡፡

4.33 **የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን የማቋረጥ ፕሮሲጀር**

የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦቱ በጊዜአዊነት ወይም በቋሚነት ከዚህ በታች በቀረቡት ፕሮሲጀሮች መሰረት ሊቋረጥ ይችላል፡፡

I. ኢ.ኤ.አ በቋሚነት የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦቱን ካቋረጠ በኋላ አገልግሎት መስመሮችን፣ ቆጣሪዎችን ወዘተ ሊያነሳ ወይም ሊነቅል ይችላል፡፡

II. ነገር ግን በጊዜአዊነት ለሚቋረጡ የኤሌክትሪክ ኃይል መስመሮችና ቆጣሪዎች አይነሱም፡፡

III. ኢ.ኤ.አ ያልተፈቀደ የኃይል አጠቃቀም ለመኖሩ በቂ መረጃ ካገኘ የኤሌክትሪክ ኃይል መስመር/ኬብል የሚያነሳ ሲሆን ነገር ግን በዚህ ጊዜ የኤሌክትሪክ ቆጣሪ አይነሳም፡፡

### 4.34 በጊዜአዊነት የኤሌክትሪክ ኃይል መቋረጥ

ኢ.ኤ.አ በመደበኛ የመክፈያ ፕሮግራሞች ያልተከፈሉ የፍጆታ ሂሳቦች ሲኖሩ፣ በስርቆት እና ያለአግባብ ኤሌክትሪክን ከመጠቀም ጋር በተያያዘ ሃይል በጊዜያዊነት ያለቅድመ ማስታወቂያ የሚያቋርጥ ሲሆን ቅድመ ማስታወቂያ በሚያስፈልጋቸው አንዳንድ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በሚከተለው መንገድ ሃይል በጊዜያዊነት ሊያቋርጥ ይችላል፡-

ሀ. በምርመራ ወቅት የኋላ ቀሪ ሂሳብ በአማካይ ተሰልቶ እንዲከፍሉ የተጠየቁ ደንበኞች ከ7 ቀን ያላነሰ ከ15 ቀናት ያልበለጠ ቅድመ ማስታወቂያ በመስጠት ሊቋረጥ ይችላል፡፡

ለ. አንድ ንግድ/ኢንዱስትሪ፣ ተገቢውን ፈቃድ በማጣቱ ወይም ፈቃዱን በሚሰጠው አካል ይህ ፈቃድ ከተነሳ እና መረጃው ለኢ.ኤ.አ ከደረሰ ቢያንስ ከ7 ቀናት በኋላ፤

ሐ. የቤት ውስጥ ኃይል አቅርቦት እስከ 10 ኪሎ ዋት እንዲሁም ለንግድ እስከ 5 ኪሎ ዋት የሚጠቀሙትን ደንበኞች ሳይጨምር እንዲሁም በኢ.ኤ.አ ምክንያት ከሚፈጠሩት ችግሮች በስተቀር በማንኛውም የክፍያ ወቅት የፓወር ፋክተር መጠናቸው ከ0.75 ያነሰ ከሆነ በታሪፍ መደቡ እስካልተገለጸ ድረስ የ7 ቀናት ቅድመ ማስታወቂያ በመስጠት ኃይል በጊዜያዊነት ሊቋረጥ ይችላል፡፡

መ. በ48 ሰዓታት ውስጥ ስለሚቋረጥ ኃይል

- በተጠቃሚው ይዞታ የተዘረጉ ሽቦዎችና የተተከሉ መሳሪያዎች የተበላሹ መሆኑ ከታወቀ
- የኤሌክትሪክ ኃይል ማፍሰስ ሁኔታ (leakage) ካለ
- ተጠቃሚው የቆጣሪውን ወይም ተዛማጅ እቃዎችን ካዛወረ
- ተጠቃሚው የኤሌክትሪክ ኃይል መስመሩን አደጋ ላይ በሚጥል ሁኔታ ማናቸውንም መገልገያ ቁሳቁሶች የሚጠቀም ከሆነ

- ተፈላጊው ከፍተኛ የከረንት መጠን በአንቀፅ 4.23 በተጠቀሰው ሰንጠረዥ ላይ ከተገለጸው መጠን በላይ ከሆነ
- ተጠቃሚው በሌሎች ተጠቃሚዎች ላይ ጣልቃ የሚገባ እና የሚረብሽ አጠቃቀም እየተጠቀመ መሆኑ ከተረጋገጠ
- በማንኛውም ሁኔታ በጊዜያዊነት ኤሌክትሪክ ተቋርጦበት እንደገና በራሱ ፈቃድ አገናኝቶ ከተጠቀመ

ሠ.ደንበኛው ሕገ ወጥ የኃይል አጠቃቀም ሲጠቀም የተገኘ መሆኑ በአንቀፅ 6.8 (ሀ) መሰረት ሲረጋገጥ፤

ረ. ረ. ተጠቃሚው ከተፈቀደለት የሃይል ጭነት በላይ እየተጠቀመ ሲገኝ ቢያንስ በ30 ቀናት ውስጥ ገቢ ካላደረገ፤

ሰ. ተጠቃሚው ኢ.ኤ.አ ወይም በኢ.ኤ.አ የተፈቀደለትን ሰራተኛ ከአንቀፅ 4.29 እስከ 4.34 የተጠቀሱትን ተግባራት ለማከናወን እንዳይገባ ከከለከለ ቢያንስ ከ24 ሠዓት በኋላ፤

ሸ. በተጠቃሚው የተሰጠው ቼክ/ሲፒኦ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ሲገኝ ቢያንስ ከ7 ቀናት በኋላ፤

ቀ. ደንበኛው በራሱ ፍላጎት ከ6 ወራት ላልበለጠ ጊዜ ለግንባታ እና ለመሳሰሉት ሁኔታዎች እንዲቋረጥለት ሲያመለክት የማቋረጫ እና የማስቀጠያ በማስከፈል ይስተናገዳል፡፡

በ. በአባሪ 4.9 በተገለጸው ፎርማት መሰረት ተጠቃሚው የኤሌክትሪክ ኃይል በጊዜያዊነት እንዲቋረጥ ምክንያት የሆነውን ሁኔታ እንዲያነሳ ማስታወቂያ የሚሰጥ ሲሆን ነገር ግን ይህ ካልሆነ ከ6 ወራት በኋላ በቋሚነት የኃይል አቅርቦቱ ያለምንም ተጨማሪ ማስጠንቀቂያ ይቋረጣል፡፡ እንደዚህ አይነት ኃይል መስመሮች መጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ እንደተዘጉ የሚቆጠር ሲሆን ቢል የሚቆምና የመጨረሻው ውሳኔ የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

ተ.ኢ.ኤ.አ ያቋረጠውን መስመር ሳይፈቀድ የተገናኘ መሆኑን ካወቀ በዚህ መመሪያ 4.34(መ) እና ሌሎች የምርመራ ማንዋሎች በተቀመጡት መሰረት እርምጃ ይወስዳል፡፡

### 4.35 የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን በቋሚነት ማቋረጥ

የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት በሚከተሉት ምክንያቶች በቋሚነት ይቋረጣል፡፡

ሀ. የውል ስምምነቱ ሲቋረጥ

ለ. በጊዜአዊነት እንዲቋረጥ ምክንያት የሆነው ጥፋት በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ ካልተስተካከለ

ሐ. ተጠቃሚው የሚፈለግበትን ክፍያ ከፍሎ የኤሌክትሪክ ሀይሉ እንዲነሳ በፅሁፍ ሲጠይቅ እና የሚፈለግበትን ክፍያ ሲያጠናቅቅ

መ. በሌሎች አስገዳጅ ሁኔታዎች ለምሳሌ በመልሶ ማልማት ምክንያት ለሚነሱ አካባቢዎች አስፈላጊው መረጃ በመያዝ ቆጣሪው እንዲነሳ ተደርጎ ክፍያውን በተመለከተ ለሚመለከተው አካል ደብዳቤ በመጻፍ ክፍያውን ማስከፈል ይኖርበታል፡፡

## 4.36 የኤሌክትሪክ ኃይል መልሶ የመቀጠል ፕሮሲጀር

ሀ.በቋሚነት የተቋረጠ የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት በድጋሚ የማይገናኝ ሲሆን ተጠቃሚው ለአዲስ መስመር ማመልከት ይኖርበታል፡፡

ለ.በጊዜአዊነት የተቋረጠው መስመር ለዚሁ ምክንያት የሆነው ጥፋት ሲስተካከል ተመልሶ የሚገናኝ ይሆናል፡፡

ሐ.አገልግሎቱ የተቋረጠው ክፍያ ባለመክፈል ከሆነ ይህ መስመር በድጋሚ የሚገናኘው ተጠቃሚው ክፍያውን ሲከፍል እና ማመልከቻውን ከተሰጠው ማስታወቂያ የደረሰኝ ኮፒ ጋር ሲቀርብ ነው፡፡ የኃይል አቅርቦቱ ማመልከቻው በቀረበ በ24 ሰዓት ውስጥ በድጋሚ ይገናኛል፡፡

መ. ክፍያው የተፈጸመው በቼክ/ሰፒኦ ከሆነ ቼኩ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ መልሶ የሚገናኝ ይሆናል፡፡

ሠ.በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲታዘዝ

ረ.ደንበኛው በራሱ ፍላጎት ለተቋረጠው ሃይል በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲቀጠልለት ሲያመለክት

## 4.37 በጊዚያዊነት የተቋረጠውን ኤሌክትሪክ ስለ መቀጠል

በሌሎች ሁኔታዎች ውስጥ አመልካቾቹ በጊዜአዊነት የኤሌክትሪክ ሀይሉ እንዲቋረጥ ምክንያት የሆነውን ሁኔታ ሲያስተካክል እና የመልሶ የማስቀጠያ ክፍያ ፈፅሞ

የሚከተሉትን ሰነዶችን ሲያቀርብ ኤሌክትሪክ ሀይሉ በ24 ሰዓት ውስጥ መልሶ እንዲገናኝ ይደረጋል፡፡

ሀ. የማስቀጠያ ክፍያ ሲፈፀም

ለ. መስመሩ የተቋረጠው በአንቀፅ 4.34 (መ) እና (ሠ) ከሆነ በኢ.ኤ.አ የተፈቀደለት ሰራተኛ/ፈቃድ ያለው የኤሌክትሪክ ተቋራጭ ስለ መስተካከሉ የምርመራ ሪፖርት ሲያቀርብ፤

ሐ. መስመሩ የተቋረጠው በአንቀፅ 4.34 (ለ) በተገለፀው መሰረት ከሆነ መስመሩ እንዲቋረጥ ምክንያት የሆነው የፈቃድ ስረዛ እንደገና ስለመፈቀዱ የሚረያረጋግጥ መረጃ ሲቀርብ

መ. በአንቀፅ 4.34 (ሠ) ለተጠቀሱት ጉዳዮች ቃል የተገባበት የተፈጸመለት ማስረጃ ሲቀርብ

ሠ. ከተፈቀደው ኃይል በላይ ለቀረበ የኃይል ጭነት (ተጨማሪ ተቀማጭ) እና ሌሎች ማስተካከያ ክፍያ በአንቀፅ 4.34 (ረ) ላይ ለተጠቀሱት ተስተካክሎ ሲቀርብ፡፡

ኢ.ኤ.አ በ48 ሰዓታት ውስጥ ይዞታውን የሚመረምር ሲሆን ለኃይል መቋረጡ ምክንያት የሆነው ሁኔታ ችግር ከተስተካከለ በ24 ሰዓት ውስጥ የኃይል አቅርቦቱ መልሶ እንዲቀጠል ያደርጋል፡፡

## 4.38 የተሰጠ የኃይል ጭነት ቅነሳ

ሀ. የኃይል ጭነት ቅነሳ እንዲደርግ የሚቀርብ እያንዳንዱ ማመልከቻ በአባሪ 4.10 ላይ በተገለፀው ቅጽ ተሞልቶ እና አስፈላጊው ክፍያ ተከፍሎ ለሚመለከተው ሃላፊ ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ይቀርባል፡፡

I. ከተፈቀደለት የኤሌክትሪክ ተቋረጭ የስራ ማጠናቀቂያና የምርመራ ምስክር ወረቀት ሲቀርብ፤

II. ቆጣሪው ከፍተኛ የኃይል ጭነት (maximum demand) የሚያነብ ከሆነ ላለፉት 2 የክፍያ ወራቶች የተመዘገበው ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ንባብ፣

III. የቅርብ ጊዜ የኤሌክትሪክ ኃይል ፍጆታ ደረሰኝ መቅረብ አለበት ነገር ግን ጉዳዩን በፍ/ቤት እየታየ የሚገኝ ከሆነ በአንቀፅ 4.46 ላይ የተገለጸው አሰራር ተፈፃሚ መሆን አለበት፡፡

ለ. የሚመለከተው የኢ.ኤ.አ ሃላፊ ለተጠቃሚው ማመልከቻውን በተመለከተ የተወሰነውን ውሳኔ በ30 ቀናት ውስጥ ያሳውቃል፡፡

ሐ.ለመስመር ዝርጋታ እና ለሰብስቴሽን ገቢ የተደረገው ገንዘብ አይመለስም፡፡ ነገር ግን ከዚህ ቀደም ብሎ ገቢ የተደረገው የዋስትና ተቀማጭ ገንዘብ ከሚፈለገው ኃይል ጭነት ቅነሳ ክፍያ በላይ ከሆነ ትርፍ የመጣው ገንዘብ እንዳመችነቱ ወደ ፊት በሚከፈሉ የፍጆታ ክፍያዎች መሰረት ይወራረዳል ወይም በገንዘብ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

መ. የኃይል ጭነት ቅነሳው የሚተገበረው ማመልከቻው በኢ.ኤ.አ በፀደቀ በሚቀጥለው ወር ይሆናል፡፡

ሠ. የኃይል ጭነት ቅነሳው በሚከተሉት ሁኔታዎች ተቀባይነት አያገኝም፡፡

1. አርክ/ኢንዳክሽን ፈርነስ፣ አነስተኛ የብረታ ብረት ፋብሪካዎች ማሽኖቹ አጠቃላይ ከሚፈልጉት የኃይል ጭነት በታች መቀነስ አይቻልም፡፡ ነገር ግን በፓራላል የተገጠመ አጋዥ ጄኔሬተር ካለ ይህ ሊፈቀድ ይችላል፡፡
2. በትናንሽና በመካከለኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም በግል የውሃ ጉድጓድ ተጠቃሚዎች ቆጣሪዎቹ MDI (maximum demand indicator) ከሌላቸው የሚቀርበው የኃይል ጭነት ቅነሳ በጠቅላላ የተተከሉት ማሽኖች ከሚያስፈልጋቸው የኃይል ጭነት በታች ማነስ የለበትም፡፡
3. አዲስ ሃይል በተገናኘ በ24 ወራት ውስጥ የሚቀርብ የሃይል ቅነሳ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
4. ምክንያቱ በፅሁፍ ሳይገለፅ እና ውሳኔው ለአመልካቹ ሳይሰጥ ማናቸውም የኃይል ቅነሳ ማመልከቻ ውድቅ አይደረግም፡፡
5. ላለፉት 2 የፍጆታ ክፍያዎች የቆጠረው ከፍተኛ የኃይል አጠቃቀም እንዲቀንስ ከተጠየቀው ጭነት በላይ ከሆነ ተቀባይነት አያገኝም፡፡
6. ቆጣሪዎች ከፍተኛውን የጭነት መጠን መመዝገብ በማይችሉበት ጊዜ ኢ.ኤ.አ የሚቀርበው ከፍተኛ ኃይል ቦታው ላይ በመርማሪ ወይም በኢነርጂ ቢል በሚደረግ ፍተሻ እንዲታወቅ

ያደርጋል፡፡ ነገር ግን ኢ.ኤ.አ ተጠቃሚው እንደዚህ አይነት ከፍተኛ የኃይል ጭነት እንደሚጠቀም በምርመራው የሚያረጋግጥ ከሆነ ይህ አሰራር አይተገበርም፡፡

### 4.39 የመንገድ መብራት የኃይል አገልግሎት ማሻሻያ ፕሮሲጀር

በህዝብ መገልገያ ቦታዎች፣ መዘጋጃ ቤቶች፣ ቤቶች ልማት ወዘተ አካባቢዎች ተጨማሪ የህዝብ መገልገያ አምፖሎች እና ተያያዥ እቃዎች በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊሻሻሉ ይችላሉ፡፡

ሀ. ተጠቃሚው በሚመለከተው ኢ.ኤ.አ ፅ/ቤት ማመልከቻ ሲያስገባ እና አስፈላጊውን ክፍያ ሲፈፅም፤

ለ. ኢ.ኤ.አ በ15 ቀናት ውስጥ የኃይል አቅርቦትን ሲያሳውቅ፤

ሐ. ሐ. አመልካቹ የሚቀርበውን ኃይል የግምት ሂሳብ ይህ ማስታወቂያ በደረሰው በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ገቢ ሲያደርግ፤

መ. አመልካቹ በሚሰጠው ቅፅ መሰረት የውል ስምምነት ሲፈፅም፤

ሠ. ኢ.ኤ.አ የግምት ገንዘቡ ገቢ በተደረገ በ15 ቀናት ውስጥ የተሻሻለውን ኃይል ያቀርባል፡፡

ረ. ተስማሚ የሆነ ውሃ የማያስገባ የብረት ሳጥን በመንገድ ላይ ለሚገኝ ቆጣሪ እና መቆጣጠሪያ ሳጥን ደንበኛው ሲያቀርብ፤

### 4.40 ከመንገድ መገልገያ መብራት ውጪ የሚቀርብ የኃይል ጭነት ማሻሻያዎች፡፡

ሀ. የኃይል ጭነት ማሻሻያ ጥያቄ የሚያቀርቡ አመልካቾች ማመልከቻቸውን በኢ.ኤ.አ የሚመለከተው ኃላፊ (በአባሪ 4.10) በተገለፀው ቅፅ አማካኝነት መሰረት ከሚከተሉት ማስረጃዎች ጋር ማቅረብ ይኖርበቸዋል፡፡

1. የምዝገባና የማስገመቻ ክፍያ ጋር በድርጅቱ የፀደቀው የማስገመቻ ክፍያ ሲከፈል፤

2. ፈቃድ ካለው የኤሌክትሪክ የስራ ተቋራጭ የውስጥ ኤሌክትሪካል መስመር ዝርጋታ ፕላን (electrical installation plan) እና ስራው ስለመጠናቀቁ የሚያሳይ የምስክር ወረቀትና የፍተሻ ሪፖርት ሲቀርብ፤
3. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከኢ.ኤ.አ መርማሪ የማረጋገጫ ደብዳቤ ሲቀርብ፤
4. የመጨረሻ የተከፈለውን የፍጆታ ክፍያ ደረሰኝ ሲቀርብ (ዕዳ የሌለበት ሲሆን)፤
5. ከክፍያዎች ጋር በተያያዘ ጉዳዩ በፍ/ቤት የሚታይ ከሆነ አንቀፅ 4.46 መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ለ. ለ. የኤሌክትሪክ ሲስተሙና የአቅርቦት ቮልቴጅ ሲስተም በተጠየቀው ማሻሻያ ምክንያት የማይለወጥ ከሆነ፡-

1. ቆጣሪውና ተዛማጅ እቃዎች የማይቀየሩ ሲሆን የኃይል ማሻሻያው ተጠቃሚው ተጨማሪ የሲስተም ጭነት ክፍያ (partial payment) መክፈል ለሚጠበቅባቸው ገቢ ካደረገበት እለት ጀምሮ ይሆናል፡፡

2. ቆጣሪውና ተዛማጅ እቃዎቹ መለወጥ ካለባቸው የኃይል ጭነት የክፍያ ግምት በ7 ቀናት ውስጥ የሚያሳውቅ ሲሆን ተጠቃሚውም ተጨማሪ የሲስተም ጭነት ክፍያ (የሚኖር ከሆነ) መክፈል ይኖርበታል፡፡ ወይም ለአዲስ ቆጣሪና ተዛማጅ እቃዎች አቅርቦት ክፍያ ገቢ ማድረግ ወይም ገዝቶ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

የሚተላለፈው ተጠቃሚው በሞት ሲለይ ወይም የይዞታው ባለቤትነት ወደ ሌላ ሰው/ድርጅት ሲተላለፍ፤ የኢ.ኤ.አ ሠራተኛ የተፈቀደለትን ነጻ ኤሌክትሪክ አገልግሎት

ሐ. በኤሌክትሪክ ሲስተም ውስጥ የቮልቴጅ መጠን ለውጥ የሚደረግ ከሆነ የሚፈቀደው የኃይል ማሻሻያ ጭነት በዚህ ምዕራፍ በተጠቀሰው ለአዲስ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት መመሪያ መሰረት የሚከናወን ይሆናል፡፡

መ. አዲስ የኃይል ጭማሪ ማሻሻያ የውል ስምምነት ቢያንስ ለ2 ዓመታት ተፈፃሚ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሠ. የኃይል ማሻሻያ ማመልከቻ ተጠቃሚው ለኢ.ኤ.አ ያልከፈላቸው ቀሪ ክፍያዎች ካሉበት እና ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ ውድቅ ይደረጋል፡፡

4.41 ስም ማዘዋወርና ታሪፍ መቀየር

ሀ. አንድ ኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ወደ ሌላ ሰው/ድርጅት ስም ለማግኘት ሲያመለክት ይህን ተከትሎ በሚቀርበው ማመልከቻ መሰረት ይሆናል፡፡

ለ. የስም ማዛወሪያ ማመልከቻ በአባሪ 4.1 በተገለጸው ፎርማት ካስፈላጊው ክፍያ ጋር በአመልካቹ ተከፍሎ ማመልከቻ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሐ. ማመልከቻው ህጋዊ ወራሽነትን የሚገልፅ ማስረጃ፣ ተያያዥ ክፍያዎች፣ እንዲሁም ከእዳ ነፃ ስለመሆኑ የሚገልፅ ማስረጃ ጋር መቅረብ ይኖርበታል፡፡

መ. ኢ.ኤ.አ ይህን የቀረበውን የስም ማዛወሪያ እንዲተላለፍ ማመልከቻ በ3 ቀናት ጊዜ ውስጥ በመመልከት ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡ ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ አመልካቹ ጉዳዩን የተመለከቱ ዝርዝሮች ጨምሮ እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡

ሠ. ነገር ግን የስም ማዛወሪያ ማመልከቻው በተለያዩ ምክንያቶች ውድቅ ከተደረገ (ተቀባይነት ካላገኘ) አመልካቹ በቀድሞ ስም የኃይል አቅርቦቱ ሳይቋረጥበት እንዲቀጥል የሚደረግ ይሆናል ፡፡

ረ. ቆጣሪው የሚተላለፍለት ወይም እንዲገናኝለት ያመለከተው ህጋዊ ወራሽ የሚጠበቅበትን ማስረጃ አሟልቶ ከቀረበ በ3 ቀናት ውስጥ አዲስ የውል ስምምነት ፈርሞ የስምምነቱን ቅጅ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

ሰ. ኢ..ኤ.አ በልዩ ሁኔታ ያስቀመጣቸው ደንበኞችን በተመለከተ ከሚመለከተው የመንግስት አካል መረጃ ከተገኘ በኋላ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

ሸ. በህጋዊ ውርስ እና ሽያጭ ለሚደረግ የይዞታ ስም ዝውውር በመጀመሪያው ተጠቃሚ እና አሁን ስም እንዲዛወርለት በጠየቀው ተጠቃሚ መካከል ስም ሳያዛውሩ የቆዩ ተጠቃሚዎች ካሉ የመጨረሻው ተጠቃሚ ያቀረበው ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ እና ውርስ ወይም ሽያጭ የተደረገበት ህጋዊ ውል/ማስረጃ ከቀረበ መስተናገድ ይችላል፡፡ነገር ግን የይዞታ ማረጋገጫ በባንክ ወይም በሌላ ሁኔታ ከተያዘ ወይም የእዳ እገዳ ካለበት

ካርታውን ከያዘው አካል ማስረጃ ሲያቀርብ መስተናገድ ይችላል፡፡ በተጨማሪም የውርስ እና ሽያጭ ማስረጃዎች መቅረብ በማይችሉበት ሁኔታ በህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ መስተናገድ ይችላል፡፡ የይዞታ ማስረጃ ላይ ለሚዘገይ የስም ማዛወር ከሚመለከተው አካል የዘገየበትን ማስረጃ ሲቀርብ በሽያጭ ውሉ እና በህጋዊ የውርስ ማስረጃ ሊስተናገድ ይችላል፡፡

ቀ. የታሪፍ ለውጥ የሚደረገው በቦታው ላይ የኤሌክትሪክ ኃይል አጠቃቀሙን በተመለከተ የቆጣሪ አንባቢ ወይም የሚመለከተው የቴክኒክ መርማሪ የምርመራ ማረጋገጫ ሪፖርት ሲያቀርብ ነው፡፡ በተጨማሪም ደንበኛው የአጠቃቀም ለውጥ እንደሚያደርግ ሪፖርት ካደረገ በኃላ በሚመለከተው መርማሪ ሲረጋገጥ የታሪፍ ለውጥ ይደረጋል፡፡

በ. ከመኖሪያ ቤት ጋር ተያይዘው ለሚሰሩ ሱቆች ለመኖሪያ ቤት የገባውን ኤሌክትሪክ ቆጣሪ ከመብራት ወይም ብርሃን አገልግሎት ውጭ ለማምረቻነት እስካልተጠቀመበት ድረስ በንግድ ታሪፍ አይታሰብበትም፡፡ ነገር ግን ለብርሃን አገልግሎት ከአንድ አምፑል በላይ የሚጠቀሙ ከሆነ በንግድ ታሪፍ ይታሰብባቸዋል፡፡ ይህ ፖሊሲ እና ፕሮሲጀር ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ከላይ ካለው ሁኔታ ውጭ ያለአግባብ በንግድ ታሪፍ ተቀይሮባቸው የቆዩ ደንበኞች ይህ ፖሊሲ እና ፕሮሲጀር ተግባራዊ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ በቆጣሪ አንባቢ፣ መርማሪ ወይም በደንበኛው በሚቀርብ ጥያቄ ወደ ትክክለኛው ታሪፍ እንዲቀየርላቸው ይደረጋል፡፡

## 4.42 በደንበኞች ይዞታ ውስጥ የመስመር፣ ቆጣሪ እና ተዛማጅ እቃዎች ማዛወሪያ ፕሮሲጀር

ሀ. ተጠቃሚው በይዞታው የሚከናወኑ የኤሌክትሪክ መስመርና ተዛማጅ ስራዎች ፈቃድ በተሰጠው የኤሌክትሪክ ተቋራጭ ክትትል ስር በመሆን ራሱ ከሽቦዎች ዝርጋታ ጋር የተያያዙ ስራዎችን ያከናውናል፡፡ ከዚህ በኋላ የስራ ማጠናቀቂያ ምስክር ወረቀት እንዲሁም በኃይል አዋጁ ቁጥር 810/2006 መሰረት የምርመራ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

ለ. የዝቅተኛ መስመር ማዛወሪያው ቆጣሪው ከቦታው እንዲነሳ የማያደርግ ከሆነ ፈቃድ የተሰጠው የኤሌክትሪክ ባለሙያ ምርመራ ሪፖርት አያስፈልግም፡፡ ነገር ግን ወደ ፊት በኢ.ኤ.አ ሲጠየቅ ተጠቃሚው የምርመራ ሪፖርቱን ያቀርባል፡፡

ሐ. በሌሎች ሁኔታዎች ውስጥ ተጠቃሚው በቅጥር ግቢ የሚገኘውን የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ወይም ቆጣሪ እና ተያያዥ እቃዎች ቦታ መለወጥ የሚፈልግ ከሆነ ይህንኑ ከተስተካከለው የመስመር ዝርጋታ ፕላን (ካስፈለገ) ጋር ለኢ.ኤ.አ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ኢ.ኤ.አ ጥያቄው በቀረበ በ7 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለጥያቄው ምላሽ ይሰጣል፡፡

መ. ከመስመር ዝርጋታው ጋር የተገናኙ የውስጥ ስራዎች ፈቃድ ባለው የኤሌክትሪክ ተቋራጭ አማካኝነት በተጠቃሚው የሚከናወን ሲሆን ከዚህ በኋላ የምርመራ ውጤቱ እና የስራ ማጠናቀቂያ ምስክር ወረቀቱ ለኢ.ኤ.አ ይቀርባል፡፡ ኢ.ኤ.አ ተፈፃሚ በሚሆኑት አዋጁ ዝርዝሮች መሰረት ጥያቄውን ያጸድቃል፡፡

ሠ. ከደንበኛው ይዞታ ውስጥ ወደ ውጭ እንዲሁም ግቢው ውስጥ ከቦታ ቦታ እንዲንቀሳቀስ ለሚጠየቅ የኤሌክትሪክ ምሰሶ ማዛወሪያ ደንበኛው የይዞታ ማረጋጫ ሲያቀርብ የሚስተናገድ ሲሆን ለቆጣሪ ማዛወሪያ ጥያቄ የመጨረሻ የፍጆታ ክፍያ ቢል እና መታወቂያ ሲያቀርብ የሚስተናገድ ይሆናል፡፡ በባንክ ወይም በሌላ አካል የተያዘ የይዞታ ማረጋገጫ እንደ አዲስ ሃይል አቅርቦት ሁሉ በሚጻፍ ማስረጃ ይስተናገዳል፡፡

ረ. የቆጣሪ ማዛወሪያ ከአንድ ይዞታ ወደ ሌላ ይዞታ መዛወር የማይችል ሲሆን ለመስኖ እርሻ ፣ ለውሃ መሳቢያ ፣ ለመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት የገቡ ቆጣሪዎች ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ መዛወር ከፈለጉ እና ሙሉ ወጭያቸው በደንበኛው የሚሸፈን ከሆነ ሊዛወር ይችላል፡፡ የትራንስፎርመር ማዛወሪያ ጥያቄ ደንበኛው ሙሉውን ወጭ መሸፈን ከቻለ ከአንድ ይዞታ ወደ ሌላ ይዞታ እንዲሁም ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ በአንቀጽ 4.43(ሐ) የተዘረዘሩት መስፈርቶች ሲሚሉ ማዛወር ይችላል፡፡

ሰ. አመልካቹ የመስመር ማዛወሪያ ጥያቄ ጠይቆ ህጋዊ ማስረጃ ማቅረብ የማይችል ከሆነ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 4.43 የኃይል አቅርቦት ቦታን የማዛወር ፕሮሲጀር

ሀ. የመስመር ማዛወሪያው የኃይል አቅርቦት ቦታን፣ ቆጣሪ እና ተዛማጅ እቃዎች ለውጥ ስራ በተጠቃሚ ወጪ በኢ.ኤ.አ ይከናወናል፡፡ የስራው ሁኔታ ከፀደቀው የስራ ዝርዝር ጋር በደንበኛው ክፍያ ገቢ ከተደረገ በ15 ቀናት ውስጥ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡ በፍ/ቤት የፍርድ ሂደት ካለ የማዛወሪያ ስራው አይከናወንም፡፡

ለ. የቆጣሪ ማዛወሪያ ከአንድ ይዞታ ወደ ሌላ ይዞታ መዛወር የማይችል ሲሆን ለመስኖ እርሻ እና ለውሃ መሳቢያ የገቡ ቆጣሪዎች ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ መዛወር ከፈለጉ እና ሙሉ ወጭያቸው በደንበኛው የሚሸፈን ከሆነ ሊዛወር ይችላል፡፡

ሐ. የትራንስፎርመር ማዛወሪያ ጥያቄ የሚከተሉት ዝርዝር ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ሊዛወር ይችላል፡

- ትራንስፎርመሩ በደንበኛው ተገዝቶ የቀረበ ወይም ሙሉ ወጭው ለኢ.ኤ.አ የተከፈለ ሲሆን
- ትራንስፎርመሩ የሚዛወርበት አዲሱ ይዞታ የደንበኛው መሆኑ ሲረጋገጥ
- ትራንስፎርመሩ ከ25 ዓመት በላይ አለማገልገሉ ሲረጋገጥ
- ደንበኛው ነባሩን መስመር ለማንሳት እና አዲሱ ቦታ ላይ ለመትከል የሚያስፈልጉ ማንኛውም ወጭዎችን ሙሉ በሙሉ ሲሸፍን
- ደንበኛው ባቀረበው የትራንስፎርመር ማዛወሪያ ጥያቄ ተጨማሪ የሃይል ጭነት ጥያቄ ከሌለ የተጨማሪ ሃይል ጭነት የድርሻ ክፍያ(partial payment) አይጠየቅም
- ትራንስፎርመሩ የሚዛወርበት ቦታ በሚመለከተው የኢ.ኤ.አ የስራ ክፍል የአዋጭነት ጥናት መሰረት ሲረጋገጥ እና ሲፈቀድ
- ደንበኛው ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች በደንበኞች አገልግሎት ፖሊሲ እና ፕሮሲጀር መሰረት መሆኑ ሲረጋገጥ
- የትራንስፎርመሩ የአገልግሎት እድሜ የሚሰላው በመጀመሪያው የውል ስምምነት ዘመን መሰረት ነው
- አስገዳጅ ሁኔታዎች ለምሳሌ የተፈጥሮ አደጋዎች፣ቦታው ለልማት ሲፈለግ ወዘተ እንደ ህጋዊ መስፈርት ተወስደው ትራንስፎርመር ያለ ቅድመ ሁኔታ ሊዛወር ይችላል፡፡

### 4.44 በደንበኛው የሚከናወን የኃይል ሽያጭ

ሀ. በኢ.ኤ.አ ሳይፈቀድለት ማንኛውም ደንበኛ ለማንኛውም አካል ኃይል መሸጥ አይችልም፡፡

ለ. የንግድ/የቢሮ ወይም የመኖሪያ መንደር በሚሆንበት ጊዜ በመጀመሪያ የኤሌክትሪክ ሀይሉ የገባው በአልሚው/ገንቢው ስም ከሆነና ባለቤትነቱን ለባለ ይዞታዎች ያስተላለፈ ከሆነ የኃይል አቅርቦቱ በሚከተሉት ሁኔታዎች ይቀጥላሉ፡፡

I. የህንጻው ገንቢ ወይም አልሚ ለባለ ይዞታዎች ወይም ለተከራዮች ንዑስ ቆጣሪዎችን በመትከል ያለትርፍ የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲያቀርብ ሲፈቀድለት፤ ይህ ሁኔታ እንደ ህገ ወጥ የኃይል አጠቃቀም አይወሰድም፡፡

II. ገምቢው ወይም አልሚው የህንፃውን ግንባታ ስራ ከጨረሰ በኋላ በንብረቱ ላይ ምንም አይነት ድርሻ እንዳይኖረው የሚፈልግ ከሆነ የኃይል አቅርቦት መስመሩ ወደ ተቋቋሙ ማህበራት ወይም ነዋሪዎች ስም ተዛውሮ በስሩ ላሉት ባለ ይዞታዎች የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦቱ ይቀጥላል፡፡

## 1.45. በፍራንቻይዝ (በውክልና) አማካኝነት የኤሌክትሪክ ኃይል ስርጭት አገልግሎት

ኢ.ኤ.አ የተወሰኑ ቦታዎች በሌላ አካል አማካኝነት ማለትም የንግድ ድርጅት፣ ማህበር ወይም ግለሰብ አማካኝነት ኃይል ሊያሰራጭ ይችላል፡፡ ይህ አካል በተፈቀደለት ቦታ የኤሌክትሪክ ኃይል የማቅረብ መብት አለው፡፡ ነገር ግን ኢ.ኤ.አ በአካባቢው የሚቀርበውን ኤሌክትሪክ ኃይል የማቅረብ ሃላፊነት አለበት፡፡

## 1.46. የፍርድ ቤት የዕዳ ክስ ሂደትና ሌሎች ጉዳዮች ባሉበት ሁኔታ የኤሌክትሪክ ኃይል ማገናኘት

በምንም አይነት ሁኔታ ጉዳዩ በፍ/ቤት፣ በግልግል ጉባኤ ወይም በኢ.ኤ.አ ክፍያን አስመልክቶ ክርክር ላይ ከሆነ በዚህ ጊዜ

I. ተጠቃሚው ቅጥር ግቢውን ከሸጠ እና በገዢው አዲስ አቅርቦት ማመልከቻ ከቀረበ ወይም

II. በተጠቃሚው የኤሌክትሪክ ኃይል ጭነት ማሻሻያና ቅነሳ ጥያቄ ከቀረበ፤ ኢ.ኤ.አ አዲሱን አቅርቦት ለተጠቃሚው ይለቃል እንዲሁም የኃይል ጭነት ቅነሳ ወይም ማሻሻያ ጭማሪን ይፈቅዳል፡፡

ይህ የሚፈቀደው በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው፡፡

- የባንክ ዋስትና፣ ቦንድ ወይም ሌሎች ሰነዶች ኢ.ኤ.አ በቂ ነው ብሎ በሚያምንበት ሁኔታ ሲቀርብ
- ከኢ.ኤ.አ ጋር የማራዘሚያ/የዋስትና ስምምነት ሲደረግ
- በቀሪ ክፍያዎች ላይ የሚጣሉ ተጨማሪ ክፍያዎች ሲኖሩ

ከዚህ በተጨማሪ የተጠቃሚው ማመልከቻዎች በኢ.ኤ.አ ለረዥም ጊዜ መጓተት የለባቸውም፡፡

## 5. የቆጣሪዎች አቅርቦት መመሪያ

### 5.1 የኢ.ኤ.አ የቆጣሪዎች አቅርቦት ግዴታ፡- የቆጣሪዎች ቅድመ ሁኔታ

ሀ. ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ያለ ቆጣሪ ወይም ተመጣጣኝ ሰርኪውት ብሬከር ምንም አይነት የኃይል አቅርቦት አይሰጥም፡፡

ለ.ሁሉም ቆጣሪ የሌላቸው የኃይል አቅርቦቶች ማለትም የውሃ ፓምፖች የመንገድ መብራትን ጨምሮ በኢ.ኤ.አ ቆጣሪ እንዲገጠምላቸው ይደረጋል፡፡ ይህም የሚሆነው እንደየ ሁኔታው ኢ.ኤ.አ ቀድሞ በሚሰጠው ማስታወቂያ መሰረት ነው፡፡

- ማንኛውም አካል በመመሪያ 5.1 (ሀ) እና (ለ) ላይ የተገለፁን ዝርዝሮች የማያከብር ከሆነ ኢ.ኤ.አ ይህን አካል በጥፋተኝነት መጠየቅ ይችላል፡፡

### 5.2 የቆጣሪዎች ዓይነት

ለአዳዲስ/ማሻሻያ የኃይል አቅርቦቶች የሚተከሉ ቆጣሪዎች አለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ እና ኢ.ኤ.አ በሚሰጠው ወይም የተሻለ ስፔሲፊኬሽን መሰረት አለም አቀፍ እውቅና ባለው ላብራቶሪ ተመርምረው ደረጃቸውን የጠበቁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ቆጣሪዎቹ የሚከተሉት ገፅታዎች ያሉአቸው መሆን ይገባቸዋል፡፡

ሀ. ለሁሉም በገጠር ለሚቀርቡ የመኖሪያ ቤትና የንግድ ኃይል አቅርቦቶች ስታቲክ ቆጣሪ ካልተገኘ ኤሌክትሮ መካኒካል ቆጣሪ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

ለ. ለሁሉም በከተማ ለሚቀርቡ የኃይል ጭነቶች ለቅድመ ክፍያም ሆነ ለድህረ ክፍያ ስታቲክስ ስማርት ቆጣሪዎች ይተከላሉ፡፡

ሐ. ለደንበኞች የሚቀርቡ ቆጣሪዎች በተቻለ መጠን በገመድ እና ገመድ አልባ ቴክኖሎጂ የሚሰሩ መሆን አለባቸው፡፡

መ. ኢ.ኤ.አ የቅድመ ክፍያ ቆጣሪዎችን ለባለ 1ፌዝ ቆጣሪ እና ባለ 3ፌዝ ቆጣሪ ደረጃ በደረጃ እንዳስፈላጊነቱ መሰረተ ልማቱን መትከል ይኖርበታል፡፡

ሠ. የቆጣሪ ማሸጊያ ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ባለው ፖሊ ካርቦኔት ፕላስቲክ ማቴሪያል መሰራት ያለበት ሲሆን በላዩ ላይም በሌዘር ብርሃን የተቀረጸ መለያ ቁጥር ሊኖረው ይገባል፡፡ ማሸጊያው የተለያዩ አካባቢ ለውጦችን የማስተናገድ አቅም ያለው መሆን ያለበት ሲሆን እሽጉ በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ መከናወን ይኖርበታል፡፡

- የከረንት ትራንስፎርመር ተጨማሪ ሁለተኛ ሳጥን (መቆለፍ የሚችል)
- የፖቴንሻል ትራንስፎርመር ተጨማሪ ሁለተኛ ሳጥን (መቆለፍ የሚችል)
- የቆጣሪ ካቢኔት
- የቆጣሪ መፈተሻ
- የቆጣሪ ተርሚናል መሸፈኛ
- የቆጣሪ መሸፈኛ
- የከረንት ትራንስፎርመር እና የፖቴንሻል ትራንስፎርመር 2ኛ ሰርኪውቶች አስፈላጊ ከሆነ ለመቋረጥና ለብሬኪንግ የተጋለጡ ሲሆን
- የፖቴንሻል ትራንስፎርመር መምረጫ ሪሌይ ሳጥን፤ አውቶማቲክ ለውጥ ሲያስፈልግ
- የከረንት ትራንስፎርመር ዋነኛ ማገናኛና የላይ ሽፋን
- ከፍተኛ ፍላጎት (MD) ሪሴት መጫኛ ቁልፎች
- የቆጣሪ መረጃ ከርቀት ለማገናኘት ጥቅም ላይ የሚውሉ ሳጥኖች/ካቢኔቶች

ረ. ለሁሉም ለ15 ኪቮ እና 33 ኪቮ ተጠቃሚዎች እና ከዛ በላይ ተጠቃሚዎች የርቀት ቆጣሪ ማንበቢያ ጂ.ኤስ.ኤም ዘዴ እንዲሁም ለማሰራጫ ትራንስፎርመሮች የርቀት ቆጣሪ ማንበቢያ እና መረጃ ማውጫ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ሰ. ዝቅተኛ ፣ መካከለኛ፣ ከፍተኛ እና በጣም ከፍተኛ መስመር የከረንት ቆጣሪዎች የትክክለኛነት ደረጃ ለከፍተኛ እና በጣም ከፍተኛ ቮልቴጅ 0.2 ወይም ከዚያ በላይ የተሻለ ወይም ለዝቅተኛ እና መካከለኛ ቮልቴጅ 0.5 ወይም የተሻለ መሆን ያለባቸው ሲሆን ይህ ሁኔታ በኢ.ኤ.አ በቆጣሪ ተከላ ፖሊሲ ላይ ይካተታል፡፡

## 5.3 የቆጣሪዎች፣ ሚኒአቸር ሰርኪውት ብሬከር /ሰርኪውት ብሬከር (MCB/CB) አቅርቦትና ተከላ

ሀ. ቆጣሪዎቹ በኢ.ኤ.አ የቆጣሪ ተከላ ፖሊሲ የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ ማሟላት አለባቸው፡፡

ለ. ለዝ.መ የኃይል ጭነት MCB እና መ.መ፣ ከ.መ፣ በ.ከ.መ ጭነቶች ተገቢው ደረጃ ያላቸው CB መሳሪያዎች ኢ.ኤ.አ በሚያፀድቀው መሰረት በተጠቃሚ ወጪ ከቆጣሪዎች ጋር ይተከላሉ፡፡

ሐ. እስከ 250 ኪሎ.ዋት የኃይል ጭነት የሚቀርብላቸው የመካከለኛ እና ከፍተኛ ኃይል ነባር ተጠቃሚዎች ቆጣሪያቸው ዝቅተኛ መስመር ላይ የተገናኘ/የታሰረ ከሆነ በታሪፍ ሰንጠረዡ ውስጥ እስካልተጠቀሰ ድረስ የሚወሰድላቸው የቆጣሪ ንባብ የዝቅተኛ መስመር ከፍተኛ ጉልበት ንባብ (maximum demand) 2% እንዲሁም የኪሎዋት ሰዓት ንባብን 3% በመጨመር በማስላት ክፍያው ይወሰናል፡፡

መ. ለመ.መ፣ ለከ.መ፣ በከመ ተጠቃሚ የሚቀርበው ኃይል ራሱን በቻለ መጋቢ መስመር ለተጠቃሚው ብቻ የሚቀርብ ከሆነ የቆጣሪው አተካከል በተጠቃሚው ቅጥር ግቢ ሆኖ በሁለትዮሽ ስምምነት በኢ.ኤ.አ ሰብስቴሽን በሚገኘው ቆጣሪ አማካኝነት የኃይል ፍጆታው ሊሰላ ይችላል፡፡

ሠ. ኢ.ኤ.አ ለሁሉም ወጪና ገቢ መጋቢዎች የሚውሉ ቆጣሪዎችን በሰብስቴሽኖች የሰብስቴሽን ትራንስፎርመርን ጨምሮ (ዝ.ቮ እና ከ.ቮ) ራሳቸውን ከቻሉ መጋቢዎች በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ ለኃይል ቆጠራ እና ምርመራ እንዲሁም ለአንድ አካባቢ፣ ኢንዱስትሪ ወይም ተቋም የሚሰጠውን የኃይል ብክነት ለመገምገም ይጠቀምበታል፡፡

ረ. ከ.መ/በከ.መ ተጠቃሚዎች በሰብስቴሽኖች ላይ በተቻለ መጠን የኃይል ፍጆታን እና ብክነቱን ለመቆጣጠር ቆጣሪዎችን ሊተክሉ የሚችሉ ሲሆን ነገር ግን የነዚህ ቆጣሪዎች ንባብ በኢ.ኤ.አ ለተጠቃሚው የተገጠመው ቆጣሪ ካልተበላሸ/ካልጠፋ በስተቀር ለክፍያ ስሌት አይውልም፡፡

ሰ. ኢ.ኤ.አ ከፍተኛ የኃይል ብክነት ላላቸው በመጋቢ መስመሩ አቅጣጫ የዝ.ቮ ማሰራጫ ትራንስፎርመሮች ቆጣሪ በመትከል የሚቀርበውን ኃይል መጠን ለማወቅ፣ ለመመርመር እና ብክነቱን ለማየት ጥቅም ላይ ያውላል፡፡ ለማሰራጫ ትራንስፎርመሮች የሚተከለው ቆጣሪ ኮምፖዛይት ስታንዳሎን ቆጣሪ ሲሆን ስታቲክ ቆጣሪዎች ከርቀት መነበብ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ቆጣሪዎቹ በትራንስፎርመሩ ከፍታ ቅርበት የሚተከሉ ሲሆኑ ነው፡፡

ሸ. ኢ.ኤ.አ ለመንገድ መብራት ቆጣሪዎች ከማብሪያ እና ማጥፊያ ጋር ይተክላል፡፡

## 5.4 የቆጣሪዎች ባለቤትነት እና አጠቃቀም

ሀ. የኢ.ኤ.አ ቆጣሪዎችን እና ሲቲ/ፒቲ የማቅረብ ሃላፊነት አለበት፡፡

ለ. ቆጣሪው ኃይል በሚቀርብበት ቦታ የሚተከለው ምን ግዜም ኢ.ኤ.አ ቆጣሪዎቹን ለማንበብ በሚያመቸው መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከአንድ በላይ ወለል ባለበት ህንፃ ቆጣሪው በመጀመሪያው ወለል (ግራውንድ ፍሎር) ይተከላል፡፡ ኮንዶሚኒየም እና የመንግስት ኪራይ ቤቶች እንደ አስፈላጊው በየቤቶቹ ላይ ሊደረግ ይችላል፡፡

ሐ. አዲስ ቆጣሪ ሲተከል (ቆጣሪ ሲለወጥ ሆነ ለአዲስ ኃይል አቅርቦት) ተጠቃሚው በተገኘበት መታሸግ እና በ2 ቅጂዎች የቆጣሪው መረጃ መመዝገቢያ ካርድ ታሪክ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ኢ.ኤ.አ የመጀመሪያውን ኮፒ የሚወስድ ሲሆን ሁለተኛው ቅጂ ደግሞ በቆጣሪው ላይ ይታሰራል፡፡ በመቀጠል የቆጣሪው ብልሽት፣ የጥገና ሁኔታ ወዘተ በዚህ ካርድ ላይ በኢ.ኤ.አ ሰራተኛ ይመዘገባል፡፡ በቆጣሪው ላይ የሚሰፍረው መረጃ እና የሚከናወነው እሽግ፣ ስሙን የያዘው ሰሌዳ፣ መለያ ቁጥር ወይም ምልክት በማንኛውም መልኩ በተጠቃሚው መነሳት፣ መሰረዝ ወይም መቀየር የለበትም፡፡

መ. ተጠቃሚው በኢ.ኤ.አ ይዞታ ውስጥ ከተተከሉት ቆጣሪዎች ፣MCB/CB መሳሪያዎች ወዘተ በስተቀር በራሱ ይዞታ ውስጥ ያሉ ቆጣሪዎቹን፣ MCB/CB መሳሪያ ወዘተ በአግባቡ የመያዝ ኃላፊነት አለበት፡፡

ሠ. ተጠቃሚው የራሱን የማረጋገጫ ቆጣሪ ሊተክል ይችላል፡፡ የተተከለውን ቆጣሪ በደንበኞች አገልግሎት መመሪያ መሰረት የተገለፀውን ዝርዝር (ስፔሲፊኬሽን) የሚያሟላ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ይህን የማረጋገጥ ቅደም ተከተል ለኢ.ኤ.አ በሚከፈል ክፍያ ድርጅቱ ቆጣሪዎቹ ሲበላሹ በደንበኛ ወጪ በኢ.ኤ.አ ሊጠገኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በቆጣሪዎቹ የሚደረገው ንባብ ኢ.ኤ.አ ለክፍያ አላማ ጥቅም ላይ አይውልም፡፡

## 5.5 ቆጣሪዎችን መፈተሽ

ሀ. ኢ.ኤ.አ የቆጣሪዎችን ትክክለኝነት ከመተከሉ በፊት የማረጋገጥ ሀላፊነት አለበት፡፡

ለ. ኢ.ኤ.አ በሚከተለው አሰራር መርሃ ግብር መሰረት የመደበኛ የቆጣሪ ምርመራ ያከናውናል፡፡

1. እስከ 7.5 ኪ.ዋ ባለ ነጠላ እና ሦስት ፌዝ ቆጣሪዎች- በ5 ዓመት አንድ ጊዜ
2. ከ7.5 ኪ.ዋ እስከ 150 ኬ.ቪ.ኤ እስከ በ3 ዓመት አንድ ጊዜ
3. 150 ኬ.ቪ.ኤ በላይ እስከ 3000 ኬ.ቪ.ኤ በ2 ዓመት አንድ ጊዜ
4. 3000 ኬ.ቪ.ኤ በላይ እስከ 10000 ኬ.ቪ.ኤ በ1 ዓመት አንድ ጊዜ
5. 10000 ኬ.ቪ.ኤ በላይ በ6 ወራት አንድ ጊዜ

ለCT እና PT ተያያዥ መስመሮች አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ከቆጣሪዎቹ ጋር አብሮ ምርመራ ይደረግበታል፡፡ የንፅፅር ምርመራዎች እና ስህተት ማካካሻዎች (Ratio Test and Error compensation) ተግባራዊ የሚሆኑ ከሆነ ይህንኑ ተግባራዊ ሊደረግ ይችላል፡፡

ሐ. ኢ.ኤ.አ ከዚህ በተጨማሪ ፍተሻዎቹ ደረጃቸውን በጠበቁ (በድርጅቱ ውስጥ መመርመሪያ ከሌለ) በኢ.ኢ.ባ በተፈቀደላቸው 3ኛ ወገን ላብራቶሪዎች እንዲከናወን ሊያደርግ ይችላል፡፡

መ. የፍተሻ ውጤቶቹን በተመለከተ በደንበኞ አገልግሎት ፖሊሲና ፕሮሲጀር መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

### 5.6 የተበላሹ ቆጣሪዎች

ሀ. ኢ.ኤ.አ በቆጣሪዎቹ ላይ አጠራጣሪ ሁኔታ እንዳለ ተጨባጭ የሆነ ጥርጣሬ ካለው ምርመራ ማከናወን የሚችል ሲሆን ተጠቃሚው አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ያም ሆኖ ተጠቃሚው የምርመራ ሂደቱን እንዲከታተል ይፈቀድለታል፡፡

ለ. ተጠቃሚው የተተከሉት ቆጣሪዎች ላይ ጥርጣሬ ካለው በአባሪ 5.1 በተመለከተው ፎርማት አማካኝነት ተገቢውን ክፍያ በመፈፀም ኢ.ኤ.አ ምርመራ እንዲያደርግ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ኢ.ኤ.አ ቆጣሪዎቹን እንደሚከተለው ይፈትሻል፡፡

- ማመልከቻው በደረሰው በ10 ቀናት ውስጥ በተጠቃሚው ቅጥር ግቢ በመገኘት ወይም
- በኢ.ኤ.አ ላብራቶሪ ወይም ሌሎች በተፈቀደላቸው ላብራቶሪዎች
- እንደ መጨረሻ አማራጭ ኢ.ኤ.አ የፍተሻ ቆጣሪ ቢበዛ ለተከታታይ 7 ቀናት በseries በመትከል ማመልከቻው በቀረበ በ10 ቀናት ውስጥ ምርመራውን ሊያከናውን ይችላል፡፡

ሐ. ምርመራው በተጠቃሚው ቅጥር ግቢ በሚከናወንበት ጊዜ ቆጣሪው ምርመራው ቢያንስ ለአንድ ኪ.ዋ.ሰ መከናወን ይኖርበታል፡፡ የኢ.ኤ.አ ፈታሽ ቡድን ምርመራውን ለማከናወን በቂ የኃይል ጭነት መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡ የኤሌክትሪክ ምት/ዙረት በአኳቼክ አማካኝነት የ(ዝ.መ) ቆጣሪዎችን ምርመራ ለማከናወን የኦፕቲካል ስካነር እና USB port መሳሪያ መጠቀም ይችላል፡፡ የአኳቼክ መሳሪያው ፍተሻ በአመት አንድ ጊዜ በብሄራዊ ደረጃ እውቅና በተሰጠው ላብራቶሪ ይከናወናል፡፡

- ቆጣሪው ደህና መሆኑ ከተረጋገጠ ተጨማሪ እርምጃ አይወሰድም፡፡
- ቆጣሪው ከሚገባው ፍጥነት እጅግ የፈጠነ ወይም የዘገየ ከሆነ ቆጣሪው በሌላ አዲስ ቆጣሪ በ15 ቀናት ውስጥ የሚቀየር ሲሆን የፍጆታ ክፍያውን በተመለከተ ለከፍተኛ እና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ክርክር የተነሳባቸው የመጨረሻዎቹ 3 ወራት ያለው ክፍያ አዲሱ ቆጣሪ ከተተከለ በኃላ ባሉት ቀጣይ 3 ተከታታይ ወራት በሚኖረው አማካይ ፍጆታ እና ቆጣሪው ከመበላሸቱ በፊት የነበሩትን 3 ወራት በድምሩ የ6 ወራት አማካይ ፍጆታ መሰረት በማድረግ የሚስተካከል ይሆናል፡፡ ለዝቅተኛ መስመር የመኖሪያ እና የንግድ ተጠቃሚዎች ደግሞ ቆጣሪው ከመበላሸቱ (ትክክለኛ አቆጣጠር ስህተት ከመፈጠሩ በፊት ያሉት 3 ወራት) አማካይ ፍጆታ ስሌት በቂ ሊሆን ይችላል፡፡ ቆጣሪው እጅግ ዘገምተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ በደንበኛው ጥያቄ መሰረት የፍጆታ ክፍያው ለሶስት ወራት አማካይ ክፍያ ተሰልቶ ከ3 ጊዜ ክፍያ ባልበለጠ ሁኔታ በሚከፈል ክፍያ የሚስተካከል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ተጠቃሚው ደንበኝነቱን የማይቀጥል እና ቆጣሪ የማይቀየር ከሆነ አማካይ ክፍያ የሚሰላው ቆጣሪው ያልተገባ አቆጣጠር ጀምሮበታል ተብሎ ሊታሰብ ከሚችለው ጊዜ ከ 3 እስከ 6 ወራት ቀደም ብለው ያሉትን ጊዜ በመውሰድ ይሆናል፡፡
- ምንም ዓይነት ታሪክ ለሌላቸው ቆጣሪዎች የአማካይ ፍጆታ የሚሰላው በቦታው ጥቅም ላይ የዋለ ጭነት ተቆጥሮ ሲሆን ይህ ከሌለ ደግሞ በውሉ ወቅት ያስፈቀደውን ጭነት 75% በመውሰድ የተጠቀመበትን ሰዓት በተመለከተ በየጊዜው እየተሻሻለ በሚወጣው የኢንስፔክሽን ፖሊሲና ፕሮሲጀር መሰረት ይሆናል፡፡
- ተጠቃሚው የምርመራ ውጤቱ ላይ ተቃውሞ የሚኖረው ከሆነ ወይም በተጠቃሚው ቅጥር ግቢ ምርመራውን ማከናወን አስቸጋሪ ከሆነ ጉድለት የተገኘበት ቆጣሪ በኢ.ኤ.አ አዲስ ቆጣሪ የሚተካ ሲሆን የተበላሸው ቆጣሪ ተጠቃሚው ባለበት ከታሸገ በኋላ ደንበኛው

በሚስማማበት የኢ.ኤ.አ ላብራቶሪ/ራሱን የቻለ ሌላ ላብራቶሪ ምርመራ ይደረግበታል፡፡ ተጠቃሚው አንደኛውን አማራጭ ከመረጠ በኋላ በምንም አይነት መልኩ ይህን አማራጭ መለወጥ አይችልም፡፡ በዚህ መሰረት የሚወሰነው የምርመራ ውጤት የመጨረሻው ይሆናል፡፡

መ. ቆጣሪዎች በኢ.ኤ.አ/ራሱን በቻለ የምርመራ ላብራቶሪ ስለሚደረግባቸው ምርመራዎች

- ተጠቃሚው ቆጣሪው ሲለወጥለት ምርመራው የሚደረግበትን ቀን ከ7 ቀናት ቀደም ብሎ እንዲያውቀው የሚደረግ ሲሆን ይህም ተጠቃሚው/ህጋዊ ወኪሉ በምርመራው ወቅት እንዲገኙ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ነው፡፡
- በምርመራ ውጤት ቅፁ ላይ የተጠቃሚ ወይም ህጋዊ ወኪሉ ፊርማ መስፈር ይኖርበታል፡፡
- የምርመራ፣ የኃይል ፍጆታ ቆጠራ ውጤት ላይ ተጠቃሚው ተቃውሞ የሚኖረው ከሆነ ሁኔታው ከላይ በ5.6 (ሐ) መሰረት ይታያል፡፡

**ማስታወሻ**፡ ኢ.ኤ.አ አስተማማኝ የሆኑ እውቅናና ፍቃድ ያላቸው የፍተሻ ላብራቶሪዎችን ዝርዝር ከሚያስከፍሉት ክፍያዎች ጋር ለኢ.ኢ.ባ አቅርቦ ሊያጸድቅ ይችላል፡፡

ሠ. የመፈተሻ ቆጣሪ ከተተከለ እና ከ7-15 ቀናት ውስጥ ነባሩ ቆጣሪ ፍጥነቱ ከፍተኛ ወይም ዘገምተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ እንዲሁም በዚህ ምርመራ ውጤት ተጠቃሚው ተቃውሞ ከሌለው ነባሩ ቆጣሪ ተነስቶ ለምርመራ የተተከለ ቆጣሪ በቋሚነት እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ክፍያውን በተመለከተ ከላይ በ5.6 (ሐ) መሰረት ይሆናል፡፡

## 5.7 የቆሙ ቆጣሪዎች MDI ያላቸውን ጨምሮ

ሀ. ተጠቃሚው ቆጣሪዎቹ የማይመዘግቡ መሆኑን ካስተዋለ ወዲያው ለኢ.ኤ.አ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

ለ. በየጊዜው በሚደረጉ እና ሌሎች ምርመራዎች ኢ.ኤ.አ ቆጣሪው የማይመዘግብ መሆኑን ካወቀ ወይም ተጠቃሚው ይህንን በተመለከተ ቅሬታ ካቀረበ ኢ.ኤ.አ ቆጣሪውን በ10 ቀናት ጊዜ ውስጥ ይፈትሻል፡፡

ሐ. በምርመራው ቆጣሪው የማይመዘግብ መሆኑ ከተረጋገጠ ፍተሻው በተከናወነ በ15 ቀናት ውስጥ ቆጣሪው ይቀየራል፡፡

መ. ክርክር የተነሳበት ክፍያ በተመለከተ በአንቀጽ 5.6 (ሐ) መሰረት ይሆናል፡፡ በጊዜአዊነት የተሰጡ የክፍያ ደረሰኞች ካሉ በዚሁ መሰረት ይወራረዳሉ፡፡

ሠ.ነገር ግን በትንሹ ከ3 ወራት ያነሰ ጊዜ ሳይቆጥሩ ላቆሙ ቆጣሪዎች አዲስ የተተከለውን ቆጣሪ 3-6 ወራት ያለውን አማካይ ፍጆታ በመውሰድ እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

ረ. አማካኝ ፍጆታው በሚሰላበት ወቅት ጭነታቸው በወቅት የሚለያይ ደንበኞችን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት በተመሳሳይ ጊዜ የነበረ ያለፈው ዓመት ፍጆታ ከግምት ውስጥ ይገባል፡፡

## 5.8 የተቃጠሉ ቆጣሪዎች

ሀ. ቆጣሪው ተጠቃሚው ባቀረበው የቅሬታ ማመልከቻም ሆነ በኢ.ኤ.አ ምርመራ መቃጠሉ ከተረጋገጠ፤

- ቆጣሪ የተቃጠለበትን ትክክለኛ ምክንያት ይመረምራል፡፡ ከተፈቀደ ጭነት በላይ በሆነ ምክንያት የተቃጠለ ከሆነ በአንቀጽ 6.9 መሰረት እንዲከፍል ተደርጎ አዲስ ቆጣሪ በ3 ቀናት ጊዜ ውስጥ ይተከላል፡፡

ለ. የሚቻል ከሆነ ኢ.ኤ.አ የተቃጠለውን ቆጣሪ ይፈትሻል፡፡ በአንቀፅ 5.6 (መ) መሰረት ቆጣሪውን መፈተሽ የማይቻል ከሆነ ተጠቃሚው ከአንቀፅ 5.7 (መ) እስከ 5.7 (ረ) ድረስ ባለው ሁኔታ መሰረት የኃይል ፍጆታውን እንዲከፍል ያደርጋል፡፡

## 5.9 የተበላሹ/የተቃጠሉ ቆጣሪዎች መተኪያ ወጪ

ሀ. የቆጣሪ ወጭ በኢ.ኤ.አ የሚሸፈንባቸው ሁኔታዎች

- በቮልቴጅ መዋዠቅ፣
- በቆጣሪ ተከላ፣ በቆረጣ ቅጠላ እና በጥገና ወቅት በኢ.ኤ.አ ሰራተኛ የተፈጠረ ስህተት ከሆነ

ለ. የቆጣሪው ወጪ በተጠቃሚው የሚሸፈንባቸው ሁኔታዎች

- ከኢ.ኤ.አ ውጭ ተከላውን ባጸደቀው የኤሌክትሪክ ተቋራጭ ጉድለት ምክንያት ከሆነ
- ከተፈቀደ ጭነት በላይ ተጠቅሞ ከሆነ
- ከኢ.ኤ.አ ፈቃድ ውጭ በመነካካት እና ሃይል ስርቆት ተግባሮች ምክንያት ከሆነ

## 5.10 የጠፉ ቆጣሪዎች (አድራሻቸው ያልተገኙ)

ሀ. የጠፉ ቆጣሪዎችን በተመለከተ የሚቀርቡ የቅሬታ ማመልከቻዎች በኢ.ኤ.አ የሚስተናገዱት ከማመልቻው ጋር ተጠቃሚው ለፖሊስ ጣቢያ ማመልከቱን የሚያሳይ ማስረጃ ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የኢ.ኤ.አ ኃላፊ ማጣራት እንዲደረግ መጠየቅ ይኖርበታል፡፡

ለ. ይህ በሚሆንበት ጊዜ የኤሌክትሪክ ኃይሉ በድጋሚ እንዲመለስ የሚደረገው አዲስ ቆጣሪ ከተተከለ እና ቆጣሪው ባልነበረበት ወቅት ለነበረው ኃይል ፍጆታ ክፍያ እንዲሁም ሌሎች ክፍያዎች ከተፈፀሙ በኋላ ነው፡፡

ሐ. ቆጣሪው ላልነበረበት ጊዜ የሚሰላው ኤሌክትሪክ ኃይል ፍጆታ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

1. የኤሌክትሪክ ኃይል ስርቆት የሚጣራበት አካሄድ በኢ.ኤ.አ ማጣራት መሰረት ቆጣሪው የጠፋው ሆን ተብሎ በተደረገ ድርጊት ወይም ቸልተኝነት ከሆነ በኤሌክትሪክ ስርቆት ይታሰባል፡፡

2. በሌሎች ምክንያቶች ከሆነ በአንቀፅ 5.7 (መ) እስከ 5.7 (ረ) የዚህ መመሪያ ዝርዝሮች መሰረት ይታያል፡፡ ለሁሉም የጠፉ ቆጣሪዎች መተኪያ ወጪ በደንበኛው የሚሸፈን ይሆናል፡፡

# 6. የኃይል ፍጆታ ስሌት

## 6.1 አጠቃላይ ዝርዝር ሁኔታዎች

ሀ. ለተለያዩ ተጠቃሚዎች መደብ የክፍያ ጊዜ በአባሪ 3.1 ተጠቅሷል፡፡ ኢ.ኤ.አ በዚህ መመሪያ መሰረት ተጠቃሚዎች የሚከፍሉበትን የክፍያ ጊዜ ያሳውቃል፡፡ እንደዚህ አይነት ማስታወቂያ በኢ.ኤ.አ በየአመቱ ወይም ማናቸውም የክፍያ አሰራር የሚገልፅ ለውጦች ተግባራዊ ከመደረጋቸው ከ1 ወር በፊት ለተጠቃሚዎች የሚገለፅ ይሆናል፡፡

ለ. ኢ.ኤ.አ ለመኖሪያ ቤት፣ ለንግድ እና ለኢንዱስትሪ ተጠቃሚዎች በደንበኛው በራሱ በሚመጣ ንባብ፣ በቦታው የሚወሰድ ንባብ፣ ቆጣሪው በሚገኝበት ቦታ የሚደረግ ኃይል ፍጆታ ክፍያ፣ ከቆጣሪው በሚወሰዱ ዳታ ቤዝ መሰረት በማድረግ የፍጆታ ክፍያዎችን በተለያየ ዲስትሪቢዩሽን አካባቢ ሊሰበስብ ይችላል፡፡

ሐ. ተጠቃሚው በራስ በሚደረግ ንባብ ስርአት በሚተገበርበት ወቅት ተጠቃሚው የቆጣሪውን ንባብ በመጨረሻው የክፍያ ደረሰኝ ላይ ከተጠቀሰው ቀን 1 ሳምንት ቀደም ብሎ ትክክለኛውን መረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡ ነገር ግን ኢ.ኤ.አ ንባቡ ትክክለኛ መሆኑን በራሱ አሰራር ማረጋገጥ ይችላል፡፡ በቦታው የሚደረግ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ንባብ በየፌዙ ከታች በፊደል ተራ (መ) በተጠቀሰው መሰረት የሚተገበር ይሆናል፡፡

መ. የተቀናጀ የቆጣሪ ስራ፣ የኃይል ፍጆታ ስሌት እና የገቢ አሰባሰብ ስርአት በሁሉም አካባቢዎች ሊተገብር ይችላል፡፡ ኢ.ኤ.አ ክፍያዎችን በእጅ ከሚያዙ የኮምፒውተር መሳሪያዎች፤ የቆጣሪውን ፎቶግራፍ ማንሳት የሚችሉ መሳሪያዎችን በመጠቀም መረጃ መሰብሰብ ይችላሉ፡፡ ኢኤአ ለተጠቃሚው መረጃዎቹ በነዚህ የኮምፒውተር መሳሪያዎች ሲደርሱት ለተጠቃሚው እንዲያረጋግጠው የሚያሳይ እና ተጠቃሚው ወዲያውኑ መክፈል የሚፈልግ ከሆነ ሊያሳየው ይችላል፡፡ ኢ.ኤ.አ በሶስተኛ ወገን በእጅ ከሚያዙ የኮምፒውተር መሳሪያዎች ለሚነበቡ መሳሪያዎች በቂ የማንበቢያ መሳሪያ መሰራጨቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ቀድሞ ከተቀመጠው የገንዘብ ስብሰባ ገቢ ያነሰ ለሚሰበስቡ የገንዘብ ስብሰባ ኤጀንሲዎች (ሶስተኛ ወገን) ቅጣት የሚጣልበት አሰራር ይዘረጋል፡፡

ሠ. በMRI የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ አማካኝነት የሚሰበሰብ ቆጣሪ ንባብ መረጃ በ7 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለተጠቃሚው መድረስ ይኖርበታል፡፡ በንዑስ አንቀጽ (ለ) ከተጠቀሱት ሁኔታዎች ውጪ ቆጣሪው በኢ.ኤ.አ ወኪል በክፍያ ወቅቱ አንድ ጊዜ መነበብ

ይኖርበታል፡፡ ቢሎች ከቆጣሪ ዳታ ቤዝ በተወሰደ መረጃ መሰረት ሲዘጋጁ በ5.1 ከተገለፀ ውጪ ኢ.ኤ.አ በ7 ቀናት ውስጥ መሸጥ አለበት፡፡ ኢ.ኤ.አ ለቆጣሪ አንባቢዎቹ ፎቶ ግራፍ የተለጠፈበት መታወቂያ መስጠት አለበት፡፡ ቆጣሪ አንባቢዎቹ በተጠቃሚው ቅጥር ግቢ የሚገኘውን ቆጣሪ ያነባሉ በደንበኛው ግቢ ውስጥ በሚገኘው ካርድ ላይ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡ ኢ.ኤ.አ ይህን ተግባር ለማከናወን ኢ.ኢ.ባ/መንግስት በሚፈቅደው መሰረት ሌላ አማራጭ ሊጠቀም ይችላል፡፡

ረ. የኢ.ኤ.አ ሰራተኛ የቆጣሪዎቹን ሁኔታ እሽግ LCD/LED የማንበብና ማሳያ ሁኔታዎችን ሪፖርት የማድረግ ሀላፊነት አለበት፡፡ በቆጣሪዎቹ ላይ የሚታይ ያልተለመደ ሁኔታ ካለ ይህንኑ ለሚመለከተው ሃላፊ በማሳወቅ በድርጅቱ እና በሃገሪቱ ባለው ህግ መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ አለበት፡፡ በኤሌክትሮኒክ ቆጣሪዎች ላይ EL ወይም LED ማሳያ ከተገጠመ እና የበራ ከሆነ ይህ ሁኔታ ለሚመለከተው ከፍተኛ ኃላፊ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ እሽጉ የተበጠሰ ከሆነ፣ የተሰበረ መስታዎት ካለው፣ እና ቆጣሪው ከተበሳ ህጋዊ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

ሰ. ኢ.ኤ.አ ቢሉን ክፍያው ከሚከፈልበት ቀን 7 ቀናት ቀደም ብሎ ሊያሳውቅ ይችላል፡፡ ቢሉ የኃይል ፍጆታ መጠን፣ ልዩ ልዩ የክፍያዎች፣ ክፍያው መከፈል ያለበትን ቀን፣ የኃይል አቅርቦቱ የሚቋረጥበትን ቀን፣ ቀሪ ክፍያዎች፣ የዋስትና ገንዘቦች፣ የደንበኛውን መብቶች፣ የክፍያ አይነትና ቦታ ወዘተ የያዘ መረጃ ይኖረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የደንበኛ ማዕከል አድርሻ ደንበኞች ቅሬታ የሚቀርቡበት ቦታ ወዘተ በዚህ የክፍያ መረጃ ውስጥ ይካተታል፡፡ ክፍያው የሚፈፀመው በባንክ ሂሳብ ወይም በቼክ/ ሲፒኦ ከሆነ የሚዘጋጅበትን የኢ.ኤ.አ ስምና አድራሻ በሰነዶቹ ላይ በግልፅ መስፈር ይኖርበታል፡፡

ሸ. የእያንዳንዱ ተጠቃሚ የክፍያ ዝርዝር የሚከፈለውን ክፍያ በተናጠል መያዝና ውዝፍ ክፍያ ተጠቃሚዎች በወቅቱ ክፍያውን የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡

ቀ. ተጠቃሚው በአንቀፅ 6.1 የተጠቀሰው የክፍያ ዝርዝር በኢ.ኤአ በወቅቱ ካልደረሰው ከሚመለከተው የኢ.ኤአ ቢሮ በመቅረብ የዚህን ክፍያ ቢል ኮፒ መውሰድ ይኖርበታል፡፡ ተጠቃሚዎቹ የዚህን ክፍያ ዝርዝር በየወቅቱ ከኢ.ኤ.አ ድረ ገፅ ማግኘት እንዲችሉ ይደረጋል፡፡

በ. ኢ.ኤ.አ በግልጽ በተቀመጠ ጊዜ ገደብ የንግድ፣ የህዝብ እና የግል ተቋማት እንዲሁም የኢንዱስትሪ ተቋማት ክፍያቸውን ሂሳባቸው ከሚገኝበት ባንክ ቀጥታ ለኢ.ኤ.አ ባንክ ሂሳብ ገቢ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ፡፡

ተ. ኢ.ኤ.አ በየደረጃው ሁሉንም የገንዘብ ስብሰባ ቢሮዎቹን በመረጃ መረብ (ኔትወርክ) ያገናኛል፡፡

## 6.2 የግምታዊ የቆጣሪ ፍጆታ ሂሳብ (estimation) የቢል ዝግጅት

ሀ. በቆጣሪ ንባብ አማካኝነት የሚዘጋጅ የፍጆታ መረጃ ከሌለ እና ኢ.ኤ.አ የኤሌክትሪክ ቆጣሪዎችን ማንበብ ካልቻለ ያለፉት 3 ወራት የፍጆታ ሂሳቦችን አማካኝ በመውሰድ ክፍያ ይዘጋጃል፡፡ ነገር ግን ኢ.ኤ.አ እንደዚህ አይነት ግምታዊ የክፍያ ዝርዝሮች ከ2 ተከታታይ የክፍያ ጊዜ በላይ እንዲዘጋጁ መፍቀድ የለበትም፡፡ ጊዜአዊ የግምት ክፍያዎቹ በኋላ ላይ በሚኖረው ቆጣሪ ንባብ መሰረት የሚስተካከሉ ይሆናሉ፡፡

ለ. የቆጣሪ ንባቡ ለ2 ተከታታይ ጊዜአት ከሌለ ላለፉት 3 የክፍያ ጊዜአት የነበረ አማካኝ ፍጆታ ተወስዶ ክፍያው የሚሰላ ሲሆን ተጠቃሚውም ማስታወቂያ ከተሰጠው በኋላ በሚኖሩት 7 ቀናት ውስጥ ቆጣሪውን ለንባብ ዝግጁ እንዲያደርግ ይነገረዋል፡፡

ሐ. ቆጣሪው በሚነበብበት ቀን ለአንባቢው ክፍት ካልሆነ ይህንኑ በተመለከተ ለደንበኛው ማስታወቂያ የሚሰጥ ሲሆን ወይም ደግሞ ይህ ማስታወቂያ በቅጥር ግቢው ዋና መግቢያ ላይ ይለጠፋል፡፡ በኢ.ኤ.አ የተጣለው ቅጣት በ7 ቀናት ውስጥ ይከፈላል፤ ይህ ካልሆነ ኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦቱ ይቋረጣል፡፡

መ. በአንቀፅ (ለ) እና (ሐ) ላይ የተገለፁት ዝርዝሮች ቀደም ብለው ለኢ.ኤ.አ ለተወሰነ ጊዜ ወደ ሌላ ቦታ በመሄዳቸው ምክንያት ቆጣሪአቸው ለመነበብ አመቺ እንዳልሆነ ማስታወቂያ ለሰጡ እና ለዚህ ማካካሻ የተወሰነ ግምት መጠን ለተወሰነ ጊዜ ለከፈሉ ተጠቃሚዎች ተፈፃሚ አይሆንም፡፡ እንደዚህ አይነት ግምታዊ ክፍያዎች ቆጣሪው ከተነበበ በኋላ በሚመጣው የክፍያ ተመን መሰረት ተስተካክለው የሚከፈሉ ይሆናሉ፡፡

## 6.3 የቦታ ይዞታ ለውጥ (ባለ ይዞታው ለቆ ሲሄድ) በቆጣሪዎች ላይ የሚከናወን ልዩ ንባብ፡፡

ሀ. ተጠቃሚው ቅጥር ግቢውን ለቆ የሚሄድ ከሆነ/የሚሸጥ ከሆነ ይህንኑ ለኢ.ኤ.አ የማስታወቅ እና የኤሌክትሪክ ሀይሉ እንዲቋረጥ የማድረግ ሀላፊነት አለበት፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ለሚቀጥለው የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ክፍያ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ለ. ተጠቃሚው የኃይል አቅርቦቱ እንዲቋረጥ የሚሰጠው ማስታወቂያ ቅጥር ግቢውን ለቆ ከመውጣቱ ቢያንስ ከ7 ቀናት በፊት መሰጠት ይኖርበታል፡፡ ኢ.ኤ.አ ለተጠቃሚው ካስታወቀ በኋላ የቆጣሪው ልዩ ንባብ ሊያከናውን ይችላል፡፡ ይህ ልዩ የቆጣሪ ንባብ እና የክፍያ ሰነድ ቆጣሪው ከተነበበት ቀን ጀምሮ እስከ መጨረሻው የኤሌክትሪክ ኃይል መቋረጥ አቅርቦት ድረስ ያለውን ክፍያ ያካትታል፡፡

ሐ. ደንበኛው ከቅጥር ግቢው ከመውጣቱ በፊት የሚጠበቅበትን ክፍያ ከከፈለ በኃላ ከእዳ ነጻ መሆኑን ማረጋገጫ ይሰጠዋል ፡፡

## 6.4 ቅድሚያ የሚከፈል የኤሌክትሪክ ፍጆታ ሂሳብ

ሀ. አንድ ተጠቃሚ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ሂሳቡን ቀድሞ ሊከፍል ይችላል፡፡

ለ. ይህ ጥያቄ በአባሪ 6.1 ላይ በተጠቀሰው ቅጽ መሰረት ሲቀርብ የሚመለከተው ሃላፊ ተጠቃሚው ላለፈው አንድ አመት የተጠቀመውን ክፍያ አማካኝ በመውሰድ እንዲከፍል ያደርጋል፡፡ አንድ ዓመት ላልሞላቸው ደንበኞች የ6 ወር አማካይ ክፍያ በመውሰድ ሊከፍሉ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ከ6 ወር በታች የደንበኝነት ጊዜ ላላቸው ተጠቃሚዎች ቅድሚያ የሚከፈል የፍጆታ ክፍያ አማካይ መውሰድ ስለሚያስቸግር ደንበኞች በፍላጎታቸው የሚከፍሉት ክፍያ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

ሐ. ኢ.ኤ.አ ቅድሚያ ለሚከፈል የክፍያ መጠን ላይ ወለድ አይጠየቅም፡፡

መ. ቅድመ ክፍያው ወደፊት በሚኖሩት የፍጆታ ክፍያዎች ላይ የሚታሰብ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት ቀሪ ክፍያ የሚኖርበት ከሆነ ደንበኛው በተለመደው የክፍያ ስርዓት ካላስተካከለ ባለመክፈሉ ምክንያት እርምጃ ይወሰዳል፡፡

## 6.5 ክርክር የሚነሳባቸው ቢሎችና ውዝፍ ሂሳቦች

ሀ. በክፍያ ሰነዱ ላይ የተሳሳተ ስም፣ አድራሻ ወዘተ የሚኖር ከሆነ ይህን በተመለከተ በሚመለከተው ቅሬታ ሰሚ ክፍል ምዝገባ ይደረጋል፡፡ አስፈላጊዎቹ ማስተካከያዎችም

በዚህ መሰረት ተደርገው ተጠቃሚው በቀጣዩ የክፍያ ቢል ላይ የሚፈለግበትን ክፍያ ይከፍላል፡፡

ለ. ደንበኛው በቢሉ ትክክለኛነት ላይ ቅሬታ ካለው በሚከተለው ሁኔታ ክፍያ ይፈፅማል፡፡

➢ የተጠየቀውን ድምር ሂሳብ፣

➢ ባለፉት 6 ወራት የተጠቀመው አማካይ ፍጆታ ተሰልቶ ከሁለቱ ያነሰውን፣

➢ ደንበኛው ከላይ በተጠቀሱት ሁለት አማራጮች ላይ በክፍያ ሰነዶች ላይ ተቃውሞ ካለው ይህን በተመለከተ በሚመለከተው ክፍል የቅሬታ ፋይል ይከፈታል፡፡ ፋይሉ መከፈት ያለበት ክፍያ ከሚከፈልበት ከመጨረሻ ቀን በፊት ነው፡፡ ቅሬታውም በ7 ቀን ውስጥ ውሳኔ አግኝቶ ደንበኛው እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

➢ ቅሬታው ትክክለኛ ሆኖ ከተገኘ የሚመለከተው ክፍል ትክክለኛውን ቢል አዘጋጅቶ በቀጣዩ የክፍያ ወቅት ወይም በወቅቱ በተደረሰበት የአሰራር ስርዓት በተቻለ ፍጥነት ለደንበኛው ማሳወቅ አለበት፡፡ ደንበኛው ክፍያውን እንዲፈፅም 7 ቀናት ይሰጠዋል፡፡ ተጠቃሚው በዚህ ምክንያት ለዘገየ ክፍያ ምንም አይነት ቅጣት የማይጣልበት ይሆናል፡፡ ክፍያው ቀደም ብሎ የተከፈለ ከሆነ ትርፉ ክፍያ በሚቀጥለው ቢል ላይ ታሳቢ ይደረጋል፡፡

➢ ቅሬታው ስህተት ሆኖ ከተገኘ ተጠቃሚው ይህንኑ እንዲያውቀው ተደርጎ ክፍያ እንዲፈፅም የሚደረግ ሲሆን በዚህ ጊዜ ክፍያውን በማዘግየቱ ደንበኛው የሚቀጣ ይሆናል፡፡

ሐ. ተጠቃሚው በቢል ላይ የቀረበለት እዳ በወቅቱ ካጠናቀቀ እና የተወሰነው ትርፍ ክፍያ ልዩነት የሚያሳይ ከሆነ ተጠቃሚው ይህንኑ ለኢ.ኤ.አ ቅሬታ ያቀርባል፡፡

መ. ኢ.ኤ.አ የኤሌክትሪክ ኃይሉ በጊዜአዊነት ከተቋረጠ ከ6 ወራት በኋላ በቋሚነት ለተቋረጡ ቆጣሪዎች ቢል እንዲወጣ የሚያደርግ ከሆነ ተጠቃሚው ይህንኑ ለሚመለከተው ክፍል በማሳወቅ በ15 ቀናት ውስጥ መልስ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

## 6.6 በደንበኛ የሚዘጋጅ የክፍያ ቢል

ተጠቃሚው የክፍያ ቢል ካልደረሰው በኢ.ኤ.አ በሚቀርበው ህጋዊ ደረሰኝ መሰረት የክፍያ ስሌቱን በአንቀጽ 6.4 (ለ) መሰረት ይከፍላል፡፡ በዚህ መሰረት ለሚዘገይ ክፍያ ኢ.ኤ.አ ቅጣት አያስከፍልም፡፡

## 6.7 የዘገዩ ክፍያዎች ቅጣት

ኢ.ኤ.አ ክፍያቸውን በጊዜው ያልፈጸሙ ደንበኞች ሃይል ካቋረጠ በኋላ በጸደቀው መመሪያ መሰረት ቅጣት ይጥላል፡፡ ደንበኛው ግዴታውን ከተወጣ ወይም ክፍያውን ከፈጸመ በኋላ ኤሌክትሪክ ወዲያውኑ እንዲቀጠል ይደረጋል፡፡ ክፍያውን ካልከፈለ ግን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን መረጃ በማደራጀት ለህግ ክፍል ክስ እንዲመሰረትበት ይተላለፋል፡፡

## 6.8 ያልተፈቀደ ኤሌክትሪክ ስለ መጠቀም

ሀ. ያልተፈቀደ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚጠቀሙ ደንበኞች የመመርመር ፕሮሲጀር

1. የኢ.ኤ.አ መርማሪ ቡድን ለተጠቃሚው መታወቂያውን ያሳያል፡፡
2. ይህን የሚመረምረው ባለሙያ ያልተፈቀደ የኤሌክትሪክ ኃይልን የሚጠቀም ደንበኛ ወይም ሌላ ግለሰብን በይዞታው ውስጥ በመግባት በመመርመር ማጣራት ይችላል፡፡ ምርመራውን በአግባቡ ካከናወነ በኋላ ኤሌክትሪክ ኃይል መሳሪያ፣ ቆጣሪ ወዘተ ላይ የተገኙ ግኝቶችን ይመዘግባል፡፡ ያልተፈቀደ ኃይል አጠቃቀም መኖሩን ሪፖርት ያቀርባል፡፡
3. የምርመራ ባለሙያው አግባብ ያልሆኑ ልዩነቶች ማለትም የተገናኘውን ኃይል ጭነት መጠን፣ የእሽጎች ሁኔታ፣ የቆጣሪውን ሁኔታ በማየት የታዘባቸውን ልዩነቶች በኤሌክትሪክ ኃይል አላግባብ አጠቃቀም መመዝገቢያ ቅፅ አባሪ 6.4 ላይ ይመዘግባል፡፡
4. ሪፖርቱ አላግባብ የሆነ የኤሌክትሪክ ኃይል አጠቃቀም መገኘት አለመገኘቱን በግልፅ ሁኔታ ማሳየት አለበት፡፡ እንዲሁም ዝርዝር ሁኔታዎቹ በሪፖርት ላይ መካተት ይኖርባቸዋል፡፡
5. ሪፖርቱ የምርመራ ሂደቱን ስሌት እና በደአፖፕ ወይም ታሪፍ ሰንጠረዥ መሰረት መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ሪፖርቱ በምርመራ ባለሙያ እና በእያንዳንዱ የምርመራ ቡድኑ አባላት ተፈርሞ ለተጠቃሚው ወይም ለወኪሉ ወዲያውኑ ይሰጣል፡፡ ተጠቃሚው ለመቀበል እምቢተኝነት የሚያሳይ ከሆነ የምርመራ ሪፖርቱ ቅጂ በቅጥር ግቢው ላይ የሚለጠፍ እና ፎቶ ግራፍ የሚነሳ ሲሆን በተመሳሳይም ሪፖርቱ ለተጠቃሚው በፖስታ፣ ኢሜይል ወይም በአጭር የሞባይል መልዕክት ይላክለታል፡፡

6. ኢ.ኤ.አ ምርመራ በተደረገ በ3 ቀናት ጊዜ ውስጥ አላግባብ የሆነ የኤሌክትሪክ ኃይል አጠቃቀም መኖሩ ለምን እንዳልተመዘገበ በ7 ቀናት ውስጥ ምክንያት እንዲቀርብለት ለደንበኛው ያሳውቃል፡፡ ማስታወቂያውም ቅሬታ ካለው የሚቀርብበት ሁኔታ ማለትም ለማን፣ መቼ እና የት ማቅረብ እንዳለበት በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡ የምርመራ ኦፊሰሩ ቅሬታውን ለመስማት አስፈላጊውን በቂ ጊዜ ከሰጠ በኃላ በተጠቃሚው መከፈል ያለበትን የኤሌክትሪክ ሃይል ፍጆታ ይወስናል፡፡

ለ. የደንበኛው ምላሽ አቀራረብ

I. የደንበኛው ምላሽ በ7 የስራ ቀናት ከቀረበ በኋላ ኢ.ኤ.አ ሁሉንም ሰነዶች በጥንቃቄ መርምሮ ያልተፈቀደ የኃይል አጠቃቀም የሌለ መሆኑ ከተረጋገጠ ይህን በተመለከተ የተከፈተው ፋይል ተዘግቶ ውሳኔው ወዲያውኑ ለተጠቃሚው በ7 ቀናት ጊዜ ውስጥ ይላካል፡፡

II. ያልተፈቀደ የኃይል አጠቃቀም መኖሩ ከተረጋገጠ ኢ.ኤ.አ ይህ ውሳኔ በተላለፈ በ15 ቀናት ውስጥ የደንበኛውን አቤቱታ ለመስማት ቀጠሮ ይይዛል፡፡

ሐ. የተጠቃሚውን አቤቱታ ስለ መስማት፡፡

I. የተጠቃሚው ምላሽ በ7 ቀናት ጊዜ ውስጥ ከቀረበ የምርመራ ኦፊሰር የተጠቃሚውን አቤቱታ የሚሰማበት ቀን ያመቻቻል፤

II. የተጠቃሚው አቤቱታ በሚሰማበት ወቅት የምርመራ ኦፊሰሩ በተጠቃሚው የቀረቡ እውነታዎችን ከግምት በማስገባት በ7 ቀናት ጊዜ ውስጥ ያልተፈቀደ የኃይል አጠቃቀም መኖር አለመኖሩን ይወስናል፡፡ አቤቱታ በሚቀርብበት ወቅት የፍተሻ ሪፖርቱ እና በተጠቃሚው የቀረበው የፅሁፍ ምላሽ መካተት ይኖርባቸዋል፡፡

III. ያልተፈቀደ የኃይል አጠቃቀም አለመኖሩ ከተረጋገጠ ሌላ ተጨማሪ ሂደት ሳይኖር ኃይል አቅርቦቱ እንዲቀጠል ይደረጋል፡፡

IV. የምርመራ ኦፊሰሩ ያልተፈቀደ የኃይል አጠቃቀሙ ሰርቆት መሆኑን ካረጋገጠ ይህ ያልተፈቀደ የኤሌክትሪክ ኃይል አጠቃቀም ለመኖሪያና ለእርሻ አገልግሎት ከሆነ በ3 ወራት ጊዜ ውስጥ እንደቀጠለ ወይም እንደተጠቀመ ተቆጥሮ የሌሎች አገልግሎቶች መደብ ከሆነ ስድስት ወር እንደተጠቀመ ተቆጥሮ ከተሰላ በኋላ ኦፊሰሩ በአባሪ 6.3 በተጠቀሰው መሰረት ያለውን ፍጆታ ያሰላል፡፡

የምርመራ ውጤቱ ለደንበኛው ይቀርባል፡፡ ደንበኛው አቤቱታውን ካቀረበ በኋላ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

- በምርመራ ውጤቱ መሰረት በስርቆት የተገኘው የኃይል መጠን ሂሳብ በታሪፍ መደቡ ላይ ተፈፃሚ በሚሆነው ታሪፍ 1½ ተባዝቶ የሚሰላ ይሆናል፡፡

V. በደንበኛው ላይ የሚደረገው የምርመራ ሒደት በሀገሪቱ በሚኖረው ህግ መሰረት ይከናወናል፡፡

VI. ተጠቃሚው የሚፈለግበትን ክፍያ ይህ ማስታወቂያ በደረሰው በ7 ቀናት ጊዜ ውስጥ ይከፍላል፡፡ ለተጠቃሚው በዚህ ጊዜ አቤቱታውን እንዲያሰማ ቀጠሮ ይያዝለታል፡፡

VII. ማናቸውም ያልተፈቀደ አጠቃቀም የኃይል ፍጆታ ምርመራ የውሳኔ ቅጂ የደረሰው ሰው የመረመረውን የኃይል ፍጆታ ክፍያ በ7 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለኢ.ኤ.አ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ ተጠቃሚው ይህንን መጠን ገቢ ካደረገ ወደፊት በዚሁ ጉዳይ ምንም አይነት ተጠያቂነት አይኖርበትም፡፡

VIII. ማንኛውም በመጨረሻው ትእዛዝ በንዑስ በፊደል ተራ (ሐ) መሰረት አላግባብ ውሳኔ ተወስኖብኛል ብሎ ቅሬታ የሚያቀርብ ግለሰብ ወይም ድርጅት ይህ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ለኢ.ኢ.ባ በአባሪ 6.2 በተጠቀሰው መሰረት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡ ነገር ግን ተጠቃሚው የምርመራ ኦፊሰሩ ያቀረበውን ኃይል ፍጆታ 1/3 ገቢ ካላደረገ እና ይህንን የሚገልፅ ሰነድ ካላቀረበ አቤቱታው አይሰማለትም፡፡

***ማስታወሻ፡*** ፍ/ቤት ይህን በተመለከተ ገምጋሚው የይግባኝ ሰሚው ባለስልጣን ያቀረበውን ውሳኔ የመስማት ስልጣን ይኖረዋል፡፡

መ. የተወሰነውን ክፍያ በአንድ ጊዜ ወይም በተፈቀደለት ጊዜ ገደብ መሰረት አለመክፈል፡፡

I. በምርመራ ኦፊሰሩ በቀረበው እና የተወሰነው መጠን በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ ክፍያ ካልተፈፀመ የጽሁፍ ማስታወቂያ ከተሰጠ በኋላ የኤሌክትሪክ ሀይሉ ተቋርጦ ክስ ይመሰረታል፡፡

II. አንድ ሰው የተወሰነውን የክፍያ መጠን የማይከፍል ከሆነ ከዚህ ክፍያ በተጨማሪ ክፍያው ከተወሰነ ከ30 ቀናት በኋላ በሀገሪቱ ብሄራዊ ባንክ በወቅቱ ተፈጻሚ በሚሆነው መሰረት ወለድ የሚታሰብበት ይሆናል፡፡

III. ያልተፈቀደ የኃይል አጠቃቀም ላይ የሚጣል ክፍያ የዚህ ተግባር ምክንያት እስካልተወገደ ድረስ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

### 6.9 ከተፈቀደው የኃይል ጭነት በላይ በሚኖርበት ጊዜ

- የመኖሪያ ቤት ሆነው ኤም.ዲ.አይ ቆጣሪ ለሌላቸው ተጠቃሚዎች ውል ከተገባበት (ከተፈቀደው) ከቆጣሪው ጋር የተገናኘው ጭነት እስከ 200% ሊደርስ የሚችል የመገልገያ መሳሪያዎች ሊቀመጥ ይችላል፡፡ነገር ግን ከተፈቀደው ጭነት በላይ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡
- የተተከለው ቆጣሪ ማክሲመም ዲማንድ ማንበብ የሚችል ከሆነ ትርፍ የመጣው የኃይል ጭነት በቆጣሪ ላይ በተመዘገበው ማክሲመም ዲማንድ መሰረት የሚሰላ ይሆናል፡፡ ጉዳዩ በሌላ ሁኔታ ሲሆን ማለትም ቆጣሪው ከፍተኛ የኃይል ጭነት የማይመዘግብ ከሆነ ትርፍ የኃይል ጭነቱ በየጊዜው ተሻሽለው በሚወጡት የኢንስፔክሽን ፖሊሲ እና ፕሮሲጀር መሰረት ሆኖ ለሶስተኛ(3) ጊዜ የሃይል ጭነት ከተፈቀደለት በላይ ጭኖ የተገኘ ደንበኛ በፕሮሲጀሩ መሰረት የተወሰነውን የገንዘብ ቅጣት ከተቀጣ በኋላ ሃይል ለ10 ተከታታይ ቀናት እንዲያጣ ይደረጋል፡፡ ለአራተኛ(4) ጊዜ ጥፋት አጥፍቶ ሲገኝ ደንበኝነት ማቋረጥ እና በሀገሪቱ ባለው ህግ መሰረት ክስ የሚመሰረትባቸው ይሆናል፡፡

### 6.10 የክፍያ ስርዓት

I. ሁሉም ክፍያዎች እስከ 4000 ብር ድረስ በጥሬ ገንዘብ መክፈል የሚቻል ሆኖ ከ4000 ብር በላይ ለሆኑ ክፍያዎች ከማንኛው ባንክ ቼክ፣ ሲ.ፒ.ኦ እና ድራፍት ሰነድ ይከፈላሉ፡፡ የክፍያ ቼኮችና ሲፒኦዎች ወይም ድራፍቶች በማናቸውም ለድርጅቱ አቅራቢያ በሚገኝ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ሊመነዘሩ የሚችል መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

II.ቼኩ የሚመነዘርበት ቀን ቼኩ የተሰጠበት ቀን እንደሆነ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን ይህ ቼክ በተሰጠ በ7 ቀናት ጊዜ ውስጥ በባንኩ መመንዘር ይኖርበታል፡፡

III.ቼኩ በ7 ቀናት ጊዜ ውስጥ የማይመነዘር ከሆነ ለተጠቃሚው ተመላሽ የሚሆን ተደርጎ አስፈላጊውን ቅጣት ከተቀጣ በኃላ ክፍያውን በጥሬ ገንዘብ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ይህ ባይሆን ግን በአንድ በጀት አመት ሁለት ቼክ አለመመንዘር ክስተቶች ከተከሰቱ ተጠቃሚው በበጀት አመቱ መጨረሻ ላይ ሁሉንም ክፍያዎች በሲ.ፒ.ኦ እንዲከፈል ይጠየቃል፡፡ በተጨማሪም ኢ.ኤ.አ በደንበኞች አገልግሎት ፖሊሲ ፕሮሲጀር/በሕግ መሰረት እርምጃ ይወስዳል፡፡ ኢ.ኤ.አ በአንቀፅ 4.34 መሰረት የኤሌክትሪክ ኃይሉን ሊያቋርጥ ይችላል፡፡

IV.ክፍያው የሚፈፀመው

1. በኢ.ኤ.አ የገንዘብ ክፍያ ጣቢያ በአካል በመቅረብ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ
2. በፖስታ ወይም በመልክተኛ
3. በኢ.ኤ.አ ሂሳብ በሚገኝበት ባንክ

V.ከላይ በንዑስ አንቀፆቹ የተጠቀሰው ክፍያ በተጨማሪ ኢ.ኤ.አ በኤሌክትሮኒክ ስርአት አማካኝነት በባንክ ወይም በክሬዲት/ዴቢት ካርዶች ወዘተ አማካኝነት ክፍያዎችን ሊቀበል ይችላል፡፡ ነገር ግን በዚህ መሰረት የሚፈፀም ክፍያ ለተጠቃሚው ከዚህ ቀደም ከነበሩ የክፍያ መክፈያ ዘዴዎች ተስማሚ መሆን ይኖርበታል፡፡

VI.የተጣሉ ክፍያዎች መክፈያ ቀን እሁድ እና በህዝብ በዓላት የሚውል ከሆነ ክፍያው በሚቀጥለው ስራ ቀን ይከፈላል፡፡

VII.ለአረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች እና ለሌሎች በልዩ ሁኔታ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች ኢ.ኤ.አ ለነዚህ ተጠቃሚዎች በልዩ ሁኔታ ተስማሚ ነው ብሎ ባመነበት መንገድ ክፍያዎችን ሊሰበስብ ይችላል፡፡

### 6.11 ደረሰኝ

ተጠቃሚው ክፍያውን ሲከፍል ወዲያውኑ ደረሰኝ ይሰጠዋል፡፡ የሃይል ፍጆታ ክፍያዎች ሲስተም ላይ መቀናነሳቸው የሚረጋገጠው በሚቀጥለው ቢል መግለጫ ላይ ነው፡፡

## 6.12 የተሰበሰበውን ገንዘብ ማወራረድ

ተጠቃሚው የሚከፍለው ክፍያ በመጀመሪያ የኤሌክትሪክ ኃይል አጠቃቀም ግብር፣ ወይ ሌላ እዳ ካለ የሚወራረድ ሲሆን ደንበኛው ሙሉ ክፍያ ካልከፈለ በሚከተለው ቅደም ተከተል ይወራረዳል፡፡

ሀ. የጊዜ ገደብ ክፍያ ካለ

ለ. ቀሪ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ክፍያ ካለ

ሐ. የወቅቱ የኤሌክትሪክ ክፍያ ካለ

መ. የክፍያ መዘግየት ቅጣት ካለ

ሠ. በቀሪ የኤሌክትሪክ ክፍዎች ላይ የሚጣል ክፍያ ካለ

ረ ልዩ ልዩ ክፍያዎች ካሉ

## 6.13 ተመላሽና ለዘገዩ ክፍያዎች ቅጣት

በክፍያ መዘግየት ላይ የሚጣለው ክፍያ በኢ.ኢ.ባ/በመንግስት በሚጣለው ተመን መሰረት ይሆናል፡፡

## 6.14 ክፍያን በጊዜ ገደብ ከፋፍሎ መክፈል (installment payment)

1. በኢ.ኤ.አ በተፈጠረ የአሰራር ክፍተት ምክንያት ለምሳሌ በወቅቱ ንባብ ባለመውሰድ፣ ወደ ሲስተም በወቅቱ ላልተዋወቁ ቆጣሪዎች፣ ቆጣሪ ተበላሽቶ በወቅቱ ባለመቀየሩ ወዘተ የሚመጡ ውዝፍ ክፍያዎች ሲኖሩ እና ደንበኛው በአንድ ጊዜ ለመክፈል የማይችል ከሆነ በጊዜ ገደብ ክፍያ ከፋፍሎ የመክፈል አማራጭ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ነገር ግን ደንበኛው በሚፈጥራቸው የተለያዩ ጥፋቶች ምክንያት ለሚመጡ ውዝፍ ሂሳቦች እና የቅጣት ክፍያዎች የጊዜ ገደብ የሚሰጠው በኃላፊው ውሳኔ ሆኖ የደንበኛውን የወቅቱን የመክፈል አቅም፣ የነበረውን መልካም የደንበኝነት ታሪክ ወዘተ በማገናዘብ የጊዜ ገደብ ተጠቃሚ ሊደረግ ይችላል፡፡ የሚፈቀደው የጊዜ ገደብ እርዝመት እና እጥረት የሚወሰነው ችግሩ

ተፈጥሮ በቆየበት ጊዜ መሰረት ሆኖ ደንበኛው በአጭር ጊዜ ከፍሎ የመጨረስ ፍላጎት ካለው ግን ሊያጥር ይችላል፡፡

2. ከዲስትሪክት ዳሬክተር በታች ያለ ማንኛውም ኃላፊ እንደዚህ አይነት ክፍያ የመፍቀድ ስልጣን የለውም፡፡ ዲስትሪክት ዳይሬክተር፣ የሪጅን ስራ አስፈጻሚ እና ዋና ሥራ አስፈጻሚ እንደ አቀማመጣቸው እስከ 3 ወራት፣ 6 ወራት እና ያለተገደበ ጊዜ ከፋፍሎ የማስከፈል ፈቃድ ሊሰጡ የሚችሉ ሲሆን የሚፈቅዱት ከፍተኛው የብር መጠን ፡ ለዲስትሪክት ዳይሬክተር እስከ 6 ሚሊዮን፣ ለሪጅን ስራ አስፈጻሚ እስከ 25 ሚሊዮን እና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ያለተገደበ የገንዘብ መጠን መፍቀድ ይችላሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በጊዜ ገደብ የሚከፈል የመጀመሪያው ክፍያ ከጠቅላላ ክፍያ 20% በማስከፈል ይሆናል ፡፡

- በየጊዜው ተከፋፍሎ የሚከፈለው የክፍያ መጠን 5000 ብር በላይ ከሆነ ተጠቃሚው ለኢ.ኤ.አ ከጠቅላላው ክፍያ ላይ የመጀመሪያውን ክፍያ ቀንሶ ጊዜው ያልደረሰ(post dated) ቼክ እንዲያስገባ የሚጠየቅ ሲሆን ሁሉም ክፍያ ተጠናቆ ሲከፈል ጊዜው ያልደረሰው ቼክ ለደንበኘው ተመላሽ ይደረጋል፡፡ ከዚህ ውጪ ያሉ ሁኔታዎች በኢ.ኤ.አ ዋና ስራ አስፈፃሚ ወይም ቦርድ የሚወሰን ይሆናል፡፡

### 6.15 ቀሪ ክፍያዎችን መሰብሰብ

ሀ. ለኢ.ኤ.አ ተከፋይ የሆኑ ውዝፍ ሂሳቦች በደአፖፕ እና ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚሻሻለው በዚሁ መመሪያ መሰረት የሚተገበር ይሆናል፡፡

ለ. በሌሎች የህግ ዝርዝሮች የተካተተው እንደ ተጠበቀ ሆኖ በአንድ ተጠቃሚ ላይ ቀሪ የሆነ ሂሳብ መከፈል ካለበት ቀን ጀምሮ ከ5 ዓመት በኋላ ሊጠየቅ አይችልም፡፡ ይህም የሚሆነው ይህ መከፈል ያለበት ክፍያ በተደጋጋሚ መከፈል እንዳለበት በሰነዶች ሲጠቀስ እና ለተጠቃሚው የሚቀርበው ኃይል ሳይቋረጥ ሲቀር ነው፡፡

***ማብራሪያ፡*** ክፍያዎቹ መከፈል ያለባቸው የመጨረሻ ቀናት በትክክል መታወቅ አለበት፡፡ መደበኛው ቆጣሪ ንባብ /ለተጠቃሚው የተተከለው መሳሪያ ንባብ በሚያመለክተው መሰረት የሚጣሉ ክፍያዎች/ ቅጣቶች ደንበኛው ይህን በተመለከተ ማስታወቂያው

በደረሰው እስከ 15 ቀን መክፈል ይኖርበታል፡፡ የክፍያ ዝርዝሩ ለተጠቃሚው እንደ መክፈያ የጊዜ ሰሌዳው ከ 2 ክፍያ ሳይክሎች ሳይዘገይ መከፈል አለበት፡፡

# 7. የስራ አፈፃፀም የጥራት ደረጃ፣ የቅሬታ መስተንግዶ እና የካሳ ክፍያ

## 7.1 አጠቃላይ መመሪያ

ሀ. ኢ.ኤ.አ በስሩ ያሉትን ሲስተሞች እና ስራ ሂደቶች የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ለተጠቃሚዎች በማቅረብ ረገድ ወጥ የሆነ የስራ አፈፃፀም ጥራት እንዲኖራቸው ማድርግ አለበት፡፡

ለ. የደንበኞችን consumer indexing ለጥገናና ለማሻሻል ስራ የቦታ አቅጣጫን በመጠቀም ረገድ ጂ.አይ.ኤስ/ጂ.ፒ.ኤስ መሰረት ያደረጉ የመጠቆሚያ መሳሪያዎች በመረጃ ስርአት አማካኝነት ጥቅም ላይ መዋል ይኖርባቸዋል፡፡ የተጠቃሚዎች ፍላጎት መተንተኛ/የሐይል መመርመሪያ መሳሪያዎች የተጠረጠሩ ልዩነቶች/ችግሮችን ለመለየት በቆጣሪ፣ በክፍያ ስሌት እና ክፍያ አሰባሰብ ላይ ተጨማሪ እርምጃ መውሰድ የሚያስፈልግ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው፡፡

ሐ. ምርጥ የሚባሉ ተሞክሮዎችን ለመደገፍ ኢ.ኤ.አ የላን፣ ዋን እና ቪሳት እንዲሁም የኦፕቲካል ኬብል ፋይበር ኔትወርክ በሚቀርበው ጥያቄ መሰረት ሊዘረጋ ይችላል፡፡ እጅግ ወቅታዊ የሆነ ስካዳ የርቀት ሰብስቴሽን መቆጣጣሪያ ስርዓት በተቻለ ሁኔታ ጥበቃ ለማከናወን፣ እንዲሁም የሐይል ጭነቱን በአግባቡ ለመያዝ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ከፍተኛ የሆነ ታይም ባውንድ ፕሮግራም በሰብስቴሽን ጣቢያ አውቶሜሽን መሳሪያ፣ የመረጃ አያያዝ ስርአት፣ እንዲሁም ችግር ሲፈጠር ማሳወቂያ ዘዴዎችን፣ ማይክሮ ኮንትሮለር (የኃይል አቅርቦትና ቁጥጥር) ለመትከል ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የኃይል ስርጭት ስርአቱ በተዋጣ መልኩ እንዲሳካ በየፌዙ በኃይል አቅርቦት መጋቢ መስመሮች ላይ ኢንተለጀንት ዲቲአርስ (DTr's) እና የመረጃ ማስገቢያ አሰራሮች ይተገበራሉ፡፡

መ. በስርጭት ስርዐቱ ላይ የኦንላይን አውቶ ቮልቴጅ፣ ቡስተሮች፣ ስዊችድ ካፓሲተር ባንክስ (switched capacitor banks)፣ በየፌዙ በሰፊው ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

7.1.1 ኢ.ኤ.አ ተጠቃሚዎች መብት እና ግዴታዎቻቸውን በተመለከተ ወቅታዊ የሆነ መረጃ እንዲኖራቸው ተገቢውን ጥረት ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ቅሬታዎቻቸውን በመቀበል አስፈላጊውን ፍትሃዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡ የተጠቃሚዎች መብት እና ግዴታ በኤሌክትሪክ ቢሉ ጀርባ ይታተማል፡፡

7.1.2 ኢ.ኤ.አ ከተጠቃሚዎች ጋር የተገናኙ ማናቸውንም አሰራሮች በበራሪ ወረቀት፣ በጋዜጣ እንዲሁም በኤሌክትሮኒክ ሚዲያ ሰፊ የሆነ ማስታወቂያ ያስነግራል፡፡ የነዚህ አሰራሮች ቅጂ ለሁሉም የአስተዳደር ቢሮዎች ከክፍያ ነፃ ተልከው የአካባቢ ቢሮዎች በሚከፍሉት አነስተኛ ሂሳብ ለተጠቃሚው እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ እነዚህ አሰራሮች በኢ.ኤ.አ ድረ ገፅ እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ አሰራሮቹ ሲቀየሩም ሆነ ሲሻሻሉ ህዝብ እንዲያውቅ ይደረጋል፡፡

7.1.3 የኢ.ኤ.አ ሃላፊዎች/ተወካዮች ተጠቃሚዎችን ለማናገር ቀድመው በተነገሩ የስራ ሰዓታት በቢሮአቸው ይገኛሉ፡፡ የሪጅን ስራ አስፈጻሚ ስልጣን የተሰጠው ሃላፊ በሳምንት አንድ ጊዜ በስራ ሰዓት ቅሬታ ለመስማት ከተጠቃሚዎች ጋር ይገናኛል፡፡

7.1.4 በአንቀፅ 7.2 የተጠቀሰውን ሁኔታ ለማሟላት ያለው ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳት ለደረሰበት ተጠቃሚ ካሳ መክፈልን ያስከትላል፡፡ ኢ.ኤ.አ የካሳ መጠኑን እና የሚከፈልበትን ቀን በየጊዜው ከተጠቃሚው እና ከኢ.ኢ.ባ/መንግስት ጋር በመነጋገር ይከልሳል፡፡

7.1.5 በኢ.ኤ.አ ለተጠቃሚው የሚከፈለው ካሳ ላይ የሚጣለው ቅጣት ኢ.ኢ.ባ/መንግስት አመታዊ ገቢ አሰባሰብን በተመለከተ የታሪፍ ስሌት ሲወስን ለካሳ የሚከፈለውን ወጭ ከግምት ውስጥ አያስገባም፡፡

## 7.2 የስራ አፈፃፀም የጥራት ደረጃ

1. የሚከተሉት የደንበኞች አገልግሎት የጥራት ደረጃዎች ናቸው፡፡

ሀ. ከአቅርቦት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች

ለ. አዳዲስ የኃይል አቅርቦት/የኃይል መቆራረጥ/መልሶ ማገናኘት እና ተያያዥ ጉዳዮች

ሐ. የቆጣሪ ስራ (ጥራት ያለው ቆጣሪን መትከል  እና የንባብ ጥራት መጠበቅ )

መ. የቢል ዝግጅት እና ሽያጭ

ሠ. የባለቤት ማስተላለፍና የአገልግሎት ለውጥ

ረ. የቆጣሪ እና ተያያዥ እቃዎች ምርመራ

ሰ. የቅሬታ አፈታት

2. ኢ.ኤ.አ በዚህ መመሪያ ላይ የተጠቀሱትን የጥራት ደረጃዎች ያከብራል፡፡ እነዚህ የጥራት ደረጃዎች ኢ.ኤ.አ የሚያሳካቸውና በዚህ መመሪያ መሰረት ግዴታዎቹን ሲወጣ የሚተገብራቸው አነስተኛ የጥራት ደረጃዎች ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም እነዚህ ስራ አፈፃፀም የጥራት ደረጃዎች በኢ.ኤ.አ/ኢ.ኢ.ባ/መንግስት ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

### 7.2.1 ከኃይል አቅርቦት ጋር የተገናኙ ጉዳዮች

**ማጠቃለያ**

ሀ. ኢ.ኤ.አ ማዕከላዊ የጥሪ ማዕከል ለማቋቋም ጥረት ያደርጋል፡፡

ለ. የጥሪ ማእከል በቂ ብዛት ያላቸው ስልኮች የሚይዝ ሲሆን ይህ ማእከል በአገሪቱ ካሉ ቢሮዎች/ሰብስቴሽኖች ጋር በስልክ የሚገናኝ ይሆናል፡፡

ሐ. አንድ ተጠቃሚ ለጥሪ ማእከሉ ቅሬታውን ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ ቅሬታ ወይም ጥያቄ የቀረበለት የጥሪ ማእከል ጥያቄውን በስልክ በአውቶሜትድ ስርአት አማካኝነት ለሚመለከተው አስቸኳይ ጥገና፣ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማእከል ማቅረብ ወይም ማስገባት የሚኖርበት ሲሆን ነገር ግን ኢ.ኤ.አ ቀሪ ክፍያ ያለበትን ተጠቃሚ ጥያቄ በዚህ የመረጃ ስርአት ውስጥ የማስገባት ሀላፊነት የለበትም፡፡

መ. የጥሪ ማእከሉ አውቶማቲክ የመልስ መስጫ አገልግሎት የሚኖረው ሲሆን ይህ አገልግሎት መብራት በጠፋባቸው አካባቢዎች ኃይል መልሶ መቼ እንደሚለቀቅ እንዲሁም ኤሌክትሪክ ኃይል መቼ ሊቋረጥ እንደሚችል እና ሊመጣ የሚችልበትን ቀን የሚያሳውቅ ይሆናል፡፡

ሠ. ኢ.ኤ.አ በማናቸውም ቦታ በጥገና እና ሌሎች ምክንያቶች ሆን ተብሎ የመብራት ኃይል የሚያቋርጥ ከሆነ እና የሚቋረጠው ሃይል ከአንድ የማከፋፈያ ጣቢያ ከሚወጣ ፊደር እና ከዚያ በላይ ከሆነ ከ24 ሰዓት በፊት በብዙሃን መገናኛ የሚቋረጥበትን እና

መልሶ የሚገናኝበትን ጊዜ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም የሚቋረጠው መስመር የተወሰኑ አካባቢዎችን ብቻ የሚሸፍንና በአካባቢው በሚገኝ የብዙሃን መገናኛ ወይም ማንኛውም ተደራሽ በሆነ መንገድ ማሳወቅ ይችላል፡፡

ረ. ኢ.ኤ.አ በድንገት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ የሚቋረጥ ኤሌክትሪክን ችግሩ ከተፈጠረ በኃላ የችግሩ ምክንያት ከታወቀ እና ችግሩ ከ8 ሰዓታ በላይ የሚቆይ መሆኑ ከተረጋገጠ ከላይ በተራ ቁጥር (ሠ) መሰረት በብዙሃን መገናኛ የሚያሳውቅ ይሆናል፡፡

ሰ.ኢ.ኤ.አ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚቋረጠው እቅድ በተያዘበት መልኩ እና በተጠቃሚዎች እጅግ ዝቅተኛ በሆነ መስተጓጎል በሚፈጥርበት ሁኔታ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲሁም ከምሽት በፊት ኃይል በድጋሚ መገናኘቱን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ሁሉ ጥረት ያደርጋል፡፡

ሸ. ሁሉም የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እና/ወይም የአቅርቦት ጥራትን በተመለከተ የሚቀርቡ ቅሬታዎች በፅሁፍ ወይም በስልክ ወይም በኢንተርኔት ባለበት ቦታ ይቀርባሉ፡፡

ቀ. ኢ.ኤ.አ ከዚህ ጋር የተያያዘውን ቅሬታ በሁሉም የሳምንቱ ቀናት 24 ሰዓት ይቀበላል፡፡ እነዚህ ቅሬታ ወይም ጥያቄዎች በኮምፒውተር ሶፍትዌር ተመዝግበው ለተጠቃሚው ቁጥር የሚሰጠው ሲሆን በዚህ ጊዜ የኃይል አቅርቦቱ መቼ እንደሚቀጠል ለተጠቃሚው መነገር ይኖርበታል፡፡

በ. ኢ.ኤ.አ ከላይ የተጠቀሱትን አሰራሮች በኢንተርኔት ለተሻለ የቅሬታ አቀራረብ እና አያያዝ አሰራር ከኢ.ኤአ ቦርድ/ኢ.ኢ.ባ/መንግስት ፈቃድ ካገኘ በኋላ ሊተገብር ይችላል፡፡

### 7.2.2 የኃይል መቋረጥ (በአንቀፅ 9.1 መሰረት በተጠቀሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት) ሲሆን

1. ዲትሪቢዩሽን ቦክስ ወይም ከፓናል ፊዩዝ ሲቃጠል፤

➢ አገልግሎት መስጫ ማዕከል ባለባቸው አካባቢዎች በ4 ሰዓታት ውስጥ እንዲሁም አገ/መ/ማዕከል በሌላቸው (ሳተላይቶች) ቦታዎች በ8 ሰዓታት ውስጥ

2. በምሰሶ የሚዘረጋ መስመር ሲወድቅ /ከጥቅም ውጭ ሲሆን

ሀ. የወደቀው /የተበላሸው መስመር እስከ 5 ምሰሶዎች ከሆነ አገ/መ/ማዕከል ባላቸው አካባቢዎች በ8 ሰዓታ ውስጥ፤ አገ/መ/ማዕከል በሌላቸው በ48 ሰዓታት ውስጥ

ለ. ከ5 ምሰሶ በላይ ለወደቀባቸው/ለተበላሸ መስመር (ሀ)ን መሰረት በማድረግ ሃይሉ መልሶ የሚገናኝ ይሆናል፡፡

3. በመሬት ውስጥ የተቀበረ ኬብል ወይም ስዊችጊር ሲበላሽ

➢ በዝቅተኛ መስመር ላይ ለደረሰ ጉዳት ከሆነ በ24 ሰዓታት ውስጥ እንዲሁም ለመካከለኛ እና ከፍተኛ የመሬት ውስጥ ኬብል ለደረሰ ጉዳት እስከ 96 ሰዓታት ውስጥ አቅርቦቱ ይቀጥላል፡፡

4. የዲስትሪቢዩሽን ትራንስፎርመር ሲበላሽ

➢ አገ/መ/ማዕከል ባላቸው አካባቢዎች በ24 ሰዓታት እንዲሁም ፤አገ/መ/ማዕከል በሌላቸው በ72 ሰዓታት ውስጥ አቅርቦቱ ይቀጥላል፡፡

5. የፓወር ትራንስፎርመር (33ኪ.ቮ እና ከዛ በላይ) ሲበላሽ

በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ (በተቻለ መጠን አማራጭ የኃይል አቅርቦት እንዲኖር ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡)

### 7.2.3 የቮልቴጅ መዋዠቅ

ኢ.ኤ.አ በተጠቃሚው የኃይል አቅርቦት ሲሰጥ ከዚህ በታች በተጠቀሰው ገደብ ውስጥ የቮልቴጅ መጠኑን መጠበቅ አለበት፡፡

I. ዝቅተኛ ቮልቴጅ ሲሆን + 10% እና -10%

II. መካከለኛ ቮልቴጅ ሲሆን + 7% እና -7%

III. ከፍተኛ ቮልቴጅ ሲሆን +5% እና -5% እና

IV. በጣም ከፍተኛ ቮልቴጅ ሲሆን +4 እና -4%

ነገር ግን አቅርቦቱ ሲጀመር ከላይ ከተጠቀሰው በላይ ቮልቴጅ መዋዠቅ ካለ ኢ.ኤ.አ በሚከተሉት የጊዜ ገደቦች ውስጥ ቅሬታው ከቀረበለት በኋላ ማስተካከል ይኖርበታል፡፡

I. ጉዳዩ የአካባቢ ችግር ከሆነ በ24 ሰዓት ውስጥ

II. ችግሩ የ(ዝ.መ) ዲስትሪቢዩሽን ሲስተም ከሆነ በ3 ወራት ጊዜ ውስጥ

III. የ(ከመ) ዲስትሪቢዩሽን ሲስተም ችግር ከሆነ በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ

IV. የ(በኪ.መ) ዲስትሪቢዩሽን ሲስተም ችግር ከሆነ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ

### 7.2.4 አዲስ አቅርቦት/የኃይል አቅርቦት ማቋረጥ /የኃይል አቅርቦትን መልሶ ማገናኘትና ተያያዥ ጉዳዮች-

(በአንቀጽ 4 እንደተገለጸው) ኢ.ኤ.አ የመጀመሪያውን ቢል ኃይሉን ማቅረብ ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሁለት የክፍያ ጊዜአት (ሳይክል) ያቀርባል፡፡ ይህ ቢል በዚህ ጊዜ ካልቀረበ ይህንኑ ለሚመለከተው ኢ.ኤ.አ የደንበኞች አገልግሎት መሽጫ ኃላፊ በማሳወቅ ኢ.ኤ.አ በሚቀጥሉት 7 ቀናት ውስጥ ቢሉን ለተጠቃሚው ይሰጣል፡፡

ኢ.ኤ.አ ነባር የቅሬታ አፈታት አሰራሮችን ይህ ደ.አ.ፖ.ፕ በኢ.ኢ.ባ ከፀደቀ በኋላ ለመቀየር ጥረት ያደርጋል፡፡

## 1. የ ቅሬታ ዓይነ ቶች

| ተ.ቁ | የ ቅሬታ ምድብ | የ ቅሬታ ዓይነ ት |
|---|---|---|
| 1 | **አ ቅር ቦ ት /Supply/** | • የ ተ ቃጠለ አ ውቶማቲ ክ<br>• የ አ ውቶማቲ ክ ተር ሚ ና ል ማላ ላ ት<br>• የ ኮ ን ዳ ክ ተር ማሳ በ ር (አ ን ድፌዝ)<br>• የ ኮ ን ዳ ክ ተር ማሳ በ ር (ሁለ ት ፌዝ)<br>• የ ኮ ን ዳ ክ ተር ማሳ በ ር (ሶ ስ ት ፌዝ)<br>• የ ኬብል ብል ሽ ት<br>• የ ኬብል ላ ግ ብል ሽ ት |

| ተ.ቁ | የቅሬታ ምድብ | የቅሬታ ዓይነት |
|---|---|---|
| | | • የኬብል ላግ መላላት<br>• የክላምፕ ብልሽት<br>• የክላምፕ መላላት<br>• የኤሌክትሪክ ሽቦ ከሌላ እቃ ጋር መነካካት<br>• የፒን ኢንሱሌተር ብልሽት<br>• በጉዳት ምክንያት የመቆየር ምሰሶ (መካከለኛ መስመር)<br>• የወደቀ ምሰሶ<br>• በጉዳት ምክንያት የመቆየር ምሰሶ(ዝቅተኛ መስመር)<br>• የሰብስቴሽን ወጪመስመር መቋረጥ(ለአጭር ጊዜ)<br>• ቆረጣቅጠላ<br>• የፒን ኢንሱሌተር መቀል<br>• የፖል ማውንት ፊውዝ በክስ መቃጠል<br>• የኬብል ብልሽት (ሁለት ፌዝ)<br>• የድሮፕ አውት ፊውዝ መውረድ(አንድ ፌዝ)<br>• የድሮፕ አውትፊውዝ መውረድ(ሁለት ፌዝ)<br>• የድሮፕ አውት ፊውዝ መውረድ(ሶስት ፌዝ)<br>•<br>• የፊውዝ ማቀፊያ መቃጠል (አንድ ፌዝ)<br>• የፊውዝ ማቀፊያ መቃጠል (ሁለት ፌዝ)<br>• የፊውዝ መቃጠል (አንድ ፌዝ) |

| ተ.ቁ | የቅሬታ ምድብ | የቅሬታ ዓይነት |
|---|---|---|
| | | • የፊውዝ መቃጠል (ሁለት ፌዝ)<br>• የፊውዝ መቃጠል (ሶስት ፌዝ)<br>• የፊውዝ ኤለመንት መቃጠል (አንድ ፌዝ)<br>• የፊውዝ ኤለመንት መቃጠል (ሁለተ ፌዝ)<br>• የፊውዝ ኤለመንት መቃጠል (ሶስት ፌዝ)<br>• የፊውዝ ማቀፊያ መቃጠል (ሶስት ፌዝ)<br>• የበሰበሰ ምሰሶ (የሜቀየር)<br>• የካሪኮላ መላላት<br>• በሌላ ደንበኞ ይዞታ ላይ የተዘረጋ ማስመር<br>• ሾርት ሰርኪዉት<br>• የኤሌክትሪክ ስርጭት ፈረቃ<br>• የኒዉትራል መላላት /ምሰሶ ላይ/<br>• የፌዝ እና ኒዉትራል መላላት /ምሰሶ ላይ/<br>• የፌዝ አለመጣጣጠን<br>• የፌዝ መላላት /ምሰሶ ላይ/<br>• የፌዝ እና ኒዉራል መገ ካካት / Short Circuit/<br>• የፌዝ እና ፌዝ መገ ካካት / Short Circuit/<br>• የቤት ገቢ ኒዉትራል ማስመር መቋረጠ<br>• የቤት ገቢ ፌዝ ማስመር መቋረጠ<br>• የእቃ አቅርቦት እጥረት / ለአዲስ ቆጣር ፤ ለኃይል ማሻሻያ እና ለማሰሉት/<br>• የነጠላ ፌዝ ማስመር ኬብል ብልሽት |

| ተ.ቁ | የቅሬታ ምድብ | የቅሬታ ዓይነት |
|---|---|---|
| | | • የዘመመ ምሰሶ (የማቃና)<br>• አድራሻው ያልተገኘ<br>• የኬብል ብልሽት (ሶስትፌዝ)<br>• የትራንስፎርመር ቡሽ ብልሽት<br>• የትራንስፎርመር ዘይት ማፍሰስ<br>• የማቢ ማስመር ብሬከር መዘለል<br>• የሰብስቴሽን ስዉቺንግ ስቴሽን ማስመር መቋረጥ (ለአጭር ጊዜ)<br>• የቮልቴጅ ማነ ስ ችግር<br>• ያረጀ ኮንዳክተር (የ ማቀየር)<br>• ያረጀ ምሰሶ (የማቀየር) |
| 2 | የድህረ ክፍያ ቆጣሪ /Post Paid Meter/ | • የከረንት ትራንስፎርመር ብልሽት<br>• የቆጣሪ ብልሽት<br>• ባዕድነገር ቆጣሪው ውስጥ መግባት<br>• የተሰሰተ የቆጣሪ ዲጅት<br>• የጠፋ ቆጣሪ<br>• የቆጣሪ በርድ መቃጠል<br>• የተቃጠለ ቆጣሪ<br>• ያለደንበኛው እውቅና የተቀየረ ቆጣሪ |

| ተ.ቁ | የቅሬታ ምድብ | የቅሬታ ዓይነት |
|---|---|---|
| | | • ተስማሚ ባልሆነ በታ የተለጠፈ ቆጣሪ<br>• የሜትር ሜልትፕላየር ስህተት<br>• ድርጅቱ የማያውቀው ቆጣሪ በደንበኛው አድራሻ መገኘት<br>• የቆጣሪ ማሽጊያ መቆረጥ /አለመኖር<br>• የቆጣሪ ተርሚናል መላላት<br>• የቆጣሪ ምሪመራ (በደንበኛውጥያቄ)<br>• ያልተተከ ለቆጣሪ (ለአዲስ ጥያቄ)<br>• ወደ ኃላ የሚቆጥር ቆጣሪ<br>• ቆጣሪ አንባቢ አለማንበብ<br>• የቮልቴጅ ትራንስፎርሞር ብልሽት<br>• የሜልቲፕላየር ፋክተር ስህተት |
| 3 | ቢል /Billing/ | • የተከፈለ ሒሳብ በድጋሜመጠየቅ /BBF/<br>• የሌላ ደንበኛ ቢል በስህተት መገዛት<br>• የተሳሳተ የቢል ሂሳብ<br>• የቢል አለማዘጋጀት<br>• በድጋሚየ ተዘጋጀ ቢል |

| ተ.ቁ | የቅሬታ ምድብ | የቅሬታ ዓይነት |
|---|---|---|
| | | • የግምት ንባብ<br>• የተጋነነ የፍጆታ ሒሳብ<br>• የስምማዞወሪያ ፣ አዲስ ቆጣሪ ፣ ማሻሻያ እና ማነል የደንበኛ ጥያቄዎችን በአግባቡ አለማስተናገድ<br>• የአንድን ደንበኛ ክፍያ ለሌላ ደንበኛ ማስተለለፍ<br>• የተሳሳተ የቢል ዋጋ<br>• የተሳሳተ የቆጣሪ ንባብ<br>• የተሳሳተ ክፈያ<br>• የተሳሳተ የታሪፍ መደብ |
| 4 | የቅጣት /ስርቆት ቢል Penal billing/ Theft | • ያለ አግባብ ኤሌክትሪክ ቀጥታ መጠቀም /Direct Connection Found/<br>• ያለ አግባብ ኤሌክትሪክ ከቆጣሪ በፊት ቀጥታ መጠቀም /Direct Connection Before Meter<br>• የኤሌክትሪክ ኃይል ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ ማስጠት<br>• ህገ ወጥየኤሌክትክ አጠቃቀም- የቆጣሪ ሻንት ማክፈ /የኤሌክትሪክ ማስመር ቀጥታ ማስርቅ፣ ማጠቀም/ የኤሌክትሪክ ኃይል ለሶስተኛ ወገን ማሻጥ<br>• ከ EEU እውቅና ውጭቆጣሪ/ ማስመር ማዞወር<br>• በማጭበርበር የተጠረጠረ |
| 5 | የተለያዩ /Miscellaneous/ | • ሌሎች |
| 6 | ደንበኛ /Customer/ | • የደንበኛውየ ውስጥ ማስመር ችግር |
| 7 | የድርጅቱ ሰራተኛ | • በማኅና የተጠረጠረ |


| ተ.ቁ | የቅሬታ ምድብ | የቅሬታ ዓይነት |
|---|---|---|
| | /EEU Employee/ | የድርጅቱ ሰራተኛ<br>• ከድርጅቱ ሰራተኛ በወቅቱ ምላሽ አለማግኘት<br>• ከድርጅቱ ሰራተኛ የታየ ያልተገባ ባህሪ<br>• የድርጅቱ ኃላፊ በቢሮ አለማ ኘት<br>• የችሎታ ማነስ |
| 8 | የድርጅቱ አገልግሎት /EEU Service/ | • ኃይል እንዲፈቀድለት የጠየቀ ደንበኛ<br>• በሌላ ደንበኛ ይዞታ ላይ አዲስ ኃይል መገመት<br>• የማስገመቻ ሒሳብ ፤ የግምት ሒሳብ እና ማነል ጥያቄዎች<br>• የደንበኛውፋይል መጥፋት<br>• የእዳ ማጣሪያ እና የቴክኒካል አዋጭጥናት ጥያቄ<br>• የቃላት አጻጻፍ ስህተት /የስም፤ የአድራሻ እና የማነሰሉት/ |
| 9 | የቅድመ ክፍያ ቆጣሪ /Pre-Paid Meter/ | • ካርድ ማጥፋት/ማበላሸት<br>• ማስነሻ ማስተር ካርድ ሚፈለግ<br>• የቅድመክፍያ ቆጣሪ ነጋቲቭንባብ ማሳየት<br>• ፓራሜትር/Parameter card/ ማስፈለግ<br>• ገንዘብ ከካርድ ወደ ቆጣሪ አለማልበጥ/የባትሪ ችግር/ የሪለይ ችግር<br>• የቅድመክፍያ ቆጣሪ ብልሽት/ጉዳት |

- ***ከላይ የተዘረዘሩት የቅሬታ አይነቶች የሚቀርቡት በአባሪ 7.2 መሰረት ይሆናል***

1. **ቅሬታ/ጥያቄ የሚቀርብባቸው ቦታዎች**

ተጠቃሚዎች ቅሬታዎቻቸውን/ጥያቄዎቻቸውን በሚከተለው መልኩ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

- ቅሬታ የሚቀርቡባቸው ስልክ ቁጥሮችና የሚያናግሩት ሰራተኛ ስም በአገልግሎት መስጫ ማዕከል በመለጠፍ
- በኢ.ኤ.አ ድረ ገፅ በማስታወቅ
- በጽሁፍ ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ከኤሌክትሪክ ኃይል ፍጆታ ክፍያ ቢሉ ጋር አብሮ በማያያዝ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- የኢኤአ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በሚከተለው የቅሬታ አፈታት ሰንሰለት መሰረት ይፈታል



2. **የኤሌክትሪክ ከረንት አለመኖር/የኤሌክትሪክ ኃይል አለመኖር**

በደንበኛው ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ኤሌክትሪክ ሊቋረጥ ይችላል፡፡

I. በኤም.ሲ.ቢ.(MCB) ችግር ምክንያት የፊውዝ መቃጠል
II. የቆጣሪ መቃጠል
III. የኃይል መስመር መበጠስ
IV. የኃይል መስመር ከምሰሶ መበጠስ
V. የዋናው ማሰራጫ መስመር ብልሽት
VI. የትራንፎርመር ብልሽት/መቃጠል
VII. የበኪ.መ ዋና ማሰራጫ ብልሽት
VIII. በግሪድ የሰብስቴሽን ብልሽት
IX. የታቀደ የመርሃ ግብር የጥገና ስራ
X. የኃይል ጭነት ሼዲንግ
XI. በልዩ ልዩ የተፈጥሮ አደጋዎች

***ማስታወሻ፡***

- የመስመር ብልሽት ወይም የኃይል መቋረጥ ሲያጋጥም ይህንን በተመለከተ ቅሬታ/ጥያቄ የቦታውን አድራሻና የጥያቄውን ባህሪ ባጭሩ በመግለፅ ለኢ.ኤ.አ ማዕከላዊ ጥሪ ማእከል ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡
- የኃይል አቅርቦት በመቋረጡ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የጥሪ ማእከሉ ከተቀበለ በኋላ ወዲያውኑ ለቅሬታ አቅራቢው ለቅሬታ መለያ ቁጥር በመስጠት ጥያቄውን መቀበሉን እውቅና ይሰጣል፡፡ የጥሪ ማእከሉ የተቀበለውን ጥያቄ/ቅሬታ ዝርዝር በዳታ ቤዝ/ በመመዝገብ ይይዛል፡፡
- የጥሪ ማእከሉ የቀረበው ቅሬታ/ጥያቄ ከላይ በተራ ቁጥር (I-XI) በቀረቡት ምክንያቶች መሆኑን ካወቀ ይህንኑ ጥያቄ የተቀበለው ሰራተኛ ወይም ኃላፊ ኃይሉ የተቋረጠበትን ምክንያት ለተጠቃሚው በማስታወቅ የኤሌክትሪክ ኃይሉ መልሶ የሚቀጠልበትን ጊዜ ያሳውቃል፡፡ በተጨማሪም ሰራተኛው የተቀበላቸው እያንዳንዱ ቅሬታዎች/ጥያቄዎች ልዩ መለያ ቁጥር መስጠት ይኖርበታል፡፡
- የጥሪ ማእከሉ የደረሰውን ጥያቄ/ጥቆማ/ቅሬታ ለሚመለከተው ተንቀሳቃሽ ቴክኒሻኖች ወይም የአስቸኳይ ጥገና ቡድን አገልግሎት ማእከል ያስተላልፋል፡፡ የተንቀሳቃሽ አገልግሎት ሰጭ ቡድኑ ጥያቄ ወደቀረበበት አድራሻ በመሄድ የቅሬታ/የጥያቄውን ምክንያት ከገመገመ በኋላ ችግሩን ይፈታል፡፡ ቅሬታው/ችግሩ ከተፈታ በኋላ ቅሬታው የደረሰው ማዕከል ይህንን እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡
- የቀረበው ቅሬታ/ጥያቄ እጅግ አስቸጋሪ ከሆነ ተንቀሳቃሽ የአስቸኳይ ጥገና ቡድኑ የችግሩን ምክንያት በአስቸኳይ ለማስተካከል ይህንኑ ለቅሬታ አቅራቢው ያሳውቃል፡፡ ተንቀሳቃሽ የጥገና ቡድኑ በቀጣይ በኃላፊነት ላይ ላለው አካል አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ ሁኔታውን ያሳውቃል፡፡
- ሁሉም የቀረቡ ቅሬታዎች በጥሪ ማእከሉ በአንቀፅ 7.7 በቀረበው መሰረት መፍትሄ የተሰጣቸው ለመሆኑ ክትትል ይደረግባቸዋል፡፡
- ለቅሬታ ተቀባይ ማእከሉ ምንም አይነት መረጃ ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ የማይደርስ ከሆነ የጥሪ ማእከሉ ጥያቄውን ለሚመለከተው ኃላፊ ከ 2 ሠዓት በኋላ ያሳውቃል፡፡
- ይህ ለሚመለከተው አካል መረጃ እንዲተላለፍ የሚደረግበት ሂደት በአጠቃላይ ሲስተም ውስጥ የሚዘረጋ እና የስልክ ጥሪዎቹ በየ2 ሰዓቱ በሰርቨር አማካኝነት ለሚደረግ ሲስተም

መፍትሄ እስኪያገኝ ድረስ ወደ ተከታዩ የሚመለከተው አካል ይተላለፋሉ፡፡ ሁሉም የቅሬታ ተቀባይ ኦፊሰሮች ለቅሬታ መስተንግዶ የሚሆን ሽቦ አልባ ስልክ ይሰጣቸዋል፡፡

- የሚመለከተው አካል ይህንን በተመለከተ የጥሪ ማእከሉ መፍትሄ አሰጣጥ ላይ ያለውን ሁኔታ በተመለከተ ግምገማ ያከናውናል፡፡
- በስልጣን እርከን ላይ ያለው ሃላፊ የማይገኝ ከሆነ ወይም ችግሩን መፍታት የማይችል ከሆነ ቅሬታው/ጥያቄው በየደረጃው ባለው የስልጣን እርከን መሰረት ለኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ኃላፊ ጉዳዩን በተመለከተ ከመረጃ ጋር ይቀርባል፡፡
- የቀረቡ ቅሬታዎች ቁጥር እና በወቅቱ መፍትሄ ሊሰጣቸው ያልቻሉ የቅሬታዎቹን ዝርዝር የያዘ የኤም.አይ.ኤስ ሪፖርት በየሩብ አመቱ ለኢ.ኤ.አ ይቀርባል፡

### 3. ቮልቴጅን በተመለከተ የሚቀርቡ ቅሬታዎች

ሀ. አነስተኛ/ከፍተኛ ቮልቴጅ በሚሆንበት ጊዜ ቅሬታው በጥሪ ማእከሉ የቅሬታ አቅራቢውን ስም፣ አድራሻ ከችግሩ ባህሪ ጋር በአንድ ላይ መያዝ ያስፈልጋል፡፡ በስራ ላይ ያለው ኦፕሬተር የቅሬታ መለያ ቁጥሩን ለእያንዳዱ ኬዝ መመዝገብ አለበት፡፡

ለ. የጥሪ ማእከሉ ቅሬታውን በአቅራቢያው ባለው የአገልግሎት መስጫ ማእከል የጥገና ተንቀሳቃሽ ቡድን ያሳውቃል፡፡ ተንቀሳቃሽ የጥገና አገልግሎት ቡድኑም ቅሬታ ወደ ቀረበበት ቦታ በመሄድ ችግሩን በመመርመር ይፈታል፡፡

ሐ. ችግሩ የአካባቢ ከሆነ ለምሳሌ የኃይል መስመር መላላት ከሆነ ቡድኑ በራሱ ችግሩን ይፈታል፡፡ የቮልቴጅ ችግሩ በሌሎች ምክንያቶች ለምሳሌ ባጠቃላይ የኤሌክትሪክ ሲስተም ችግር ከሆነ የተንቀሳቃሽ ቡድኑ ይህንኑ ለቅርብ ሃላፊው ያሳውቃል፡፡

መ. ጉዳዩ የሚመለከተው ሰብትራንስሚሽን ጣቢያ ሃላፊ የትራንስፎርመሮችን Tap Changer ችግሩን መፈታት የሚችል መሆኑን ካወቀ ይህንኑ ሰብትራንስሚሽን ሃላፊ ፈቃድ ካገኘ በኋላ ያከናውናል፡፡ ነገር ግን ሰብትራንስሚሽን ጣቢያ ሃላፊው ችግሩ በመላ የኤሌክትሪክ ስርአቱ የተከሰተ እና የማሰራጫ መስመሮችን፣ ትራንስፎርመሮችን፣ ካፓሲተሮችን ወዘተ ማስተካከል የሚያስፈልግ መሆኑን ከተረዳ በመቀጠል አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው ሃላፊ ያሳውቃል፡፡

ሠ. የቮልቴጅ ችግሩ በአንቀፅ 7.2.3 በተገለፀው የጊዜ መርሃ ግብር መሰረት ይፈታል፡፡ ኢ.ኤ አ በኢ.ኢ.ባ በተቀመጠው ቀነ ገደብ በቅሬታ መደባቸው የቀረቡ በቀረበው ጊዜ የተፈቱና ሊፈቱ ያልቻሉ ቅሬታዎችን ቁጥር እና ምክንያት በተመለከተ የኤም.አይ.ኤስ ሪፖርት በየሩብ አመቱ ያቀርባል፡፡

### 4. በፕሮግራም የኃይል መቋረጥ/ጭነት መቀነስ shadding

ተደጋጋሚ የኃይል መቀነስ ከ12 ሰዓታት በላይ በፕሮግራም የኃይል መቀነስ ሲደረግ ወይም የኃይል መቋረጥ ሲኖር (በዚህ ፕሮሲጀር ከተቀመጠው) ይህን የተመለከተው ቅሬታ ለዲስትሪክቱ ዳይሬክተር በአባሪ 7.2 በቀረበው ፎርማት መሰረት ይቀርባል፡፡ ለዲስትሪክቱ ዳይሬክተር ይህንን ቅሬታ መቀበሉን እውቅና በመስጠት እንደዚህ አይነት ጉዳዮች እንዳይከሰቱ ወደፊት ሁኔታዎች ማመቻቸት አለበት፡፡

## 7.3 የደንበኛ ቅሬታ አያያዝና መስተንግዶ

ሀ.ኢ.ኤ.አ በደ.አ.ፖ.ፕ መሰረት የደንበኞች ቅሬታና አቤቱታ የማስተናገጃ ፎረም ያቋቁማል፡፡

ለ.ማናቸውም በኢ.ኤ.አ ድርጊት ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ተጠቃሚ ከአንቀፅ 7.2.1 እስከ 7.2.4 ወይም በተገልጹት ህጎችና ደንቦች መሰረት ፋይል ይከፍታል የተመለከቱትን ጉዳዮች በተመለከተ ባሉት ደንቦች መሰረት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

ሐ. ኢ.ኤ.አ በተቀመጠው ቀነ ገደብ ቅሬታውን መፍታት ካልቻለ ወይም ደንበኛው በመፍትሄው ካልረካ ተጠቃሚው ቅሬታውን በኢ.ኤ.አ በተዘረጋው የተጠቃሚዎች ቅሬታ ሰሚ መድረክ ማቅረብ ይችላል፡፡

መ. ማናቸውም ቅሬታው ባለመስተናገዱ ምክንያት ጉዳት ደረሰብኝ የሚል ተጠቃሚ ቅሬታውን ለኢ.ኢ.ባ ማቅረብ ይችላል፡፡

ሠ. ማናቸውም ጉዳት የደረሰበት አካል የኢ.ኤ.አ መዛኝ ሃላፊ በዚህ መመሪያ ክፍሎች በቀረበው መሰረት የመጨረሻውን ትእዛዝ ከሰጠ በኋላ በሚኖሩት 30 ቀናት ለይግባኝ ሰሚ ባለስልጣን ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

ረ. እያንዳንዱ ይግባኝ በጽሁፍ ቃለ መሃላ መረጋገጥ ያለበት ሲሆን ይግባኙ ያቀረበው ሰው ሙሉ ስም፣ እና አድራሻ እንዲሁም ኃላፊነት ተገልፆ ቃለ መሀላ ለማቅረብ ስልጣን ባለው መ/ቤት ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ሰ. እያንዳንዱ ቃለ መሀላ የይግባኝ ባዩ እምነት ፣ የይግባኝ ባዩ እውቀት ፣ ለይግባኝ ባዩ የደረሰው መረጃ ሊካተትበት ይገባል፡፡

ሸ. ማናቸውም ቃለ መሀላ ለይግባኝ ባዩ የቀረበው መረጃ ትክክለኛ እንደሆነ የሚገልፅ ከሆነ ቃለ መሀላው ይግባኝ ባዩ መረጃውን ያገኘበትን ምንጭ መግለፅ ይኖርበታል፡፡

## 7.4 ግምገማና ውሳኔ

በወሳኝ ኦፊሰሩ የመጨረሻ ውሳኔ አቤቱታ ያለው ተጠቃሚ ውሳኔው በተላለፈ በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በአባሪ 6.2 በቀረበው መሰረት በኢኤእ/የፌደራል መንግስቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚያስቀምጠው አሰራር ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## 7.5 የስራ አፈፃፀም የጥራት ደረጃን የተመለከተ መረጃ

ሀ. ኢ.ኤ.እ የአገልግሎት የጥራት ደረጃዎችን በተመለከተ የክትትል ስርአት መዘርጋት ያለበት ሲሆን ይህንን ለኢ.ኢ.ባ/ለመንግስት በየሩብ አመቱ ሪፖርት ይልካል፡፡

ለ. መረጃው በሪፖርት ዘመኑ የተከሰቱ ክስተቶችን እንዲሁም ውሳኔ እየተጠባበቁ ያሉ ጉዳዮችን ራሳቸውን በቻሉ ደብዳቤዎች በሩብ አመቱ ወር ማብቂያ መላክ ይኖርበታል፡፡

## 8. የኤሌክትሪክ አውታር፣ ቆጣሪዎች ወዘተን በመነካካት ማጭበርበር፣ ማበላሸት ወይም ስርቆት መፈጸም

*ቆጣሪ መነካካት እና የኤሌክትሪክ የቀጥታ ስርቆት*

1. **ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት እምነትን በማጉደል**

ሀ. በአየር ላይ የሚዘረጉ፣ በምድር ውስጥ የሚቀበሩ እና በውሃ ውስጥ የሚዘረጉ መስመሮችን ወይም ኬብሎችን ወይም የአገልግሎት ሽቦዎችን ወይም የኢ.ኤ.አ. አገልግሎት ማቅረቢያዎችን የሚጠልፍ ወይም፤

ለ. ቆጣሪን አላግባብ የሚነካካ፣ የተጭበረበረ ቆጣሪ የሚተክል ወይም የሚጠቀም፣ ከረንትን አቅጣጫ የሚቀይር ትራንስፎርመር የሚተክል እና የሚጠቀም፣ የኤሌክትሪክ መስመርን አቅርቦትን የሚጠልፍ ወይም ትክክለኛ እና ተገቢ ከሆነ የኤሌክትሪክ ፍሰት ምዝገባ ወይም የቆጣሪ ስራ ላይ ጣልቃ የሚገባ መሳሪያ የሚተክል ወይም ኤሌክትሪክ እንዲሰረቅ ወይም እንዲባክን የሚያደርግ ወይም፤

ሐ. የኤሌክትሪክ ቆጣሪ፣ መሳሪያ፣ መገልገያ ወይም ሽቦ የሚያበላሽ ወይም የሚያወድም ወይም እነዚህ እቃዎች እና መገልገያዎች እንዲጎዱ ወይም እንዲወድሙ በማድረግ ትክክለኛ ኤሌክትሪክ ንባብ እንዳይኖር የሚያደርግ እና በዚህ የኤሌክትሪክ ኃይልን ለራሱ ፍጆታ የሚጠቀም ማንኛውም ተገልጋይ የጠፋውን ንብረት እና የፍጆታ ሂሳብ በኢ.ኤ.አ. በየጊዜው እያሻሻለ በሚያወጣው የኢንስፔክሽን ፖሊሲ እና ፕሮሲጀር በተቀመጠው የቅጣት መጠን የሚቀጡ ሆኖ ለሁለተኛ እና ለሶስተኛ ጊዜ ጥፋት ለሚፈጽሙ ደንበኞች ለመጀመሪያ ጥፋት የተቀመጠውን ቅጣት በጥፋቱ ቁጥር ልክ በማባዛት የሚፈጸም ይሆናል፡፡ ሆኖም ለሶስተኛ ጊዜ ጥፋት የሚፈጽሙ ደንበኞች ተገቢውን ክፍያ ከከፈሉ በኋም እንደ ተጨማሪ ቅጣት ለተከታታይ 10 ቀናት ኤሌክትሪክ እንዲቋረጥባቸው ይደረጋል፡፡ ለአራተኛ ጊዜ ጥፋት አጥፍቶ ሲገኝ ደንበኝነት ማቋረጥ እና በሀገሪቱ ባለው ህግ መሰረት ክስ የሚመሰረትባቸው ይሆናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በሚመለከተው ባለስልጣን ሳይፈቀድ ማናቸውም ሰው ሰራሽ መሳሪያዎች በመጠቀም የኤሌክትሪክ ኃይልን ለማስተጓጎል ተግባር ላይ መዋሉ

ከተረጋገጠ ሁኔታው በተቃራኒው እስኪረጋገጥ ድረስ የኤሌክትሪክ ሀይሉ በተጠቃሚው እንደ ተጭበረበረ ይቆጠራል፡፡

**2. ማናቸውም በፌደራሉ መንግስት ስልጣን የተሰጠው ኃላፊ**

ሀ. ኤሌክትሪክ ኃይል ያለ ተገቢው ፈቃድ ጥቅም ላይ እየዋለ ወይም ሊውል እንደሚችል በሚያምንበት ጊዜ ይፈትሻል እንዲሁም ምርመራ ያካሂዳል፡፡

ለ. ሳይፈቀድ ኤሌክትሪክ ኃይልን ለመጠቀም ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉ ወይም ሊውሉ የሚችሉ መሳሪያዎችን፣ መገልገያዎችን፣ ሽቦዎችን ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ሁኔታዎችን ይይዛል፣ ከቦታቸው ያነሳል፡

ሐ. በንዑስ ክፍል 1. ላይ የተጠቀሱትን ጥፋቶች በተመለከተ ደጋፊ ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ የሚያምንባቸውን መዛግብት ወይም ሰነዶች ይመረምራል እንዲሁም ሰነዶቹ ወይም መዛግብቱ በአደራነት ከሚጠብቀው ግለሰብ በተገኘበት ቅጂ እንዲደረግ ያደርጋል፡፡

3. ፍለጋው የሚደረግበት ቦታ ባለ ይዞታ የሚገኝ ሲሆን በዚህ ወቅት የተያዙ ነገሮችን ዝርዝር በመያዝ ለባለ ይዞታው ወይም ተወካዩ ዝርዝሩን በመስጠት ዝርዝሩ ላይ እንዲፈርም ያደርጋል፡፡

መርማሪው አካል በፌደራል መንግስት/በፍርድ ቤት ስልጣን የተሰጠው ቢሆንም እድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ የቤተሰብ አባል የሆነ ግለሰብ እስካልተገኘ ድረስ ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ በመኖሪያ ቅጥር ግቢዎች ምንም አይነት ፍተሻ/ፍለጋ ወይም እቃዎችን መያዝ ተግባር አይከናወንም፡፡

## የኤሌክትሪክ መስመሮችና ተያያዥ እቃዎች ስርቆት

1. ማናቸውም ግለሰብ በማጭበርበር፤

ሀ. የኤሌክትሪክ ገመድ፣ ዕቃዎች፣ ቆጣሪዎች፣ ከታወር ምሰሶና ከማንኛውም የተገጠመበት በትርፍ ቢሆንም ባይሆንም የቆረጠ፣ የወሰደ፣ ያዛወረ በህጋዊ መንገድ የተከማቸበትን፣ የተቀመጠበትን፣ የተሰካበትን ወይም የሚገኝበትን እንዲሁም የሚተላለፍበትን ታወር፣

ምሰሶ ወይም ሌሎች ማናቸውም ተከላዎች ያለ ኢ.ኤ.አ ወይም ባለቤቱ ስምምነት ለትርፍ ወይም ገቢ ለማግኘት የሚቆርጥ ወይም የሚያስወግድ፣ የሚወስድ ወይም፤

ለ. በቀጥር ግቢው ያለ ኢ.ኤ.አ ፈቃድ ትርፍ ለማግኘትም ሆነ ለሌላ አላማ የኤሌክትሪክ መስመር፣ እቃ ወይም ቆጣሪ የሚወስድ ወይም በአደራ የሚያስቀምጥ፤

ሐ. ያለ ኢ.ኤ.አ ፈቃድ ትርፍ ለማግኘትም ሆነ ለሌላ አላማ ኤሌክትሪክ መስመሮችን፣ ማቴሪያሎችን ወይም ቆጣሪዎችን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚጭን፣ የሚወስድ ኤሌክትሪክ መስመር እና ማቴሪያል ስርቆት እንደፈፀመ ተወስዶ ርእሰ ጉዳዩን በሚመለከተው አዋጅ መሰረት የሚቀጣ ይሆናል፡፡

2. አንድ ግለሰብ በንዑስ ክፍል አንድ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በኋላ በድጋሚ በዚሁ ንዑስ ክፍል የሚገኝ ጥፋት እንዳጠፋ ከተረጋገጠ በአዋጁ መሰረት ለ2ኛ ጥፋት የሚጣለው መቀጮ ተፈፃሚ ይሆንበታል፡፡

## የተሰረቁ ንብረቶችን በመቀበል ምክንያት የሚጣል ቅጣት

ማናቸውም በማጭበርበር ወይም ከቅን ልቦና ውጪ የኤሌክትሪክ መስመር ወይም ማቴሪያል የተሰረቀ ንብረት መሆኑን እያወቀ ወይም ለማወቅ በቂ ምክንያት እያለው የሚቀበል በሚመለከተው አዋጅ መሰረት ይቀጣል፡፡

## በኢ.ኤ.አ ቆጣሪዎች ወይም ስራዎች ማስተጓጎል

1. ማናቸውም ግለሰብ፤

ሀ. ሳይፈቀድለት ማናቸውንም ቆጣሪ፣ አመላካች መሳሪያ ከማናቸውም በኢ.ኤ.አ የሚቀርበው ኤሌክትሪክ ኃይል መስመር ጋር የሚያገናኝ ወይም እነዚህን መሳሪያዎች ከኤሌክትሪክ መስመሩ የሚነቅል ወይም የሚያለያይ፤

ለ. ሳይፈቀድለት ማናቸውንም ቆጣሪ/አመላካች መሳሪያ የኢ.ኤ.አ ንብረት የሆነን እና ከመስመር እንዲቋረጥ የተደረገ ኤሌክትሪክ መስመርን መልሶ የሚያገናኝ፤

ሐ. ሳይፈቀድለት የኢ.ኤ.አ ንብረት ከሆኑ ሌሎች ስራዎች ጋር ለማገናኘት መስመሮችን የሚዘረጋ ወይም እንዲዘረጉ የሚያደርግ፣

መ. በእኩይ መንፈስ እና አላማ ማናቸውንም ቆጣሪ፣ አመላካች መሳሪያ ወይም በኢኤአ ንብረት የሆኑ ኤሌክትሪክ መገልገያዎች ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም ሆን ብሎ ወይም በማጭበርበር ቆጣሪዎችን አመላካች ቁጥር፣ ማመልከቻ ቀስት የሚቀይር ወይም እንደዚህ አይነት ቆጣሪ፣ አመላካች ምልክቶች በአግባቡ ንባብ እንዳይመዘግቡ የሚያደርግ በሚመለከተው አዋጅ መሰረት የሚቀጣ ሲሆን በተጨማሪም በአንቀጽ (ሀ) የተጠቀሰው አይነት አቅርቦት ያለ ከሆነ ወይም በአንቀጽ (ለ) የተጠቀሰው ያለ ፈቃድ የማገናኘት ድርጊት ወይም በአንቀጽ (ሐ) የተጠቀሰው የማገናኘት ሁኔታ ወይም በአንቀጽ (መ) የተጠቀሰው የቆጣሪ ንባብን ማጭበርበር ሁኔታ ካለ ቆጣሪው ተጠቃሚው ሆነም አልሆነ በተቃራኒው እስኪረጋገጥ ድረስ እንደዚህ አይነት ያለፈቃድ የማገናኘት፣ የተቆረጠ መስመርን መልሶ የማገናኘት፣ ከመስመር ጋር ማገናኘት፣ አግባብ ያለው የኤሌክትሪክ ንባብ እንዳይኖር ወይም አላግባብ አጠቃቀም በተጠቃሚው ሆን ተብሎ በማወቅ የተከናወነ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

## በቸልተኝነት የኤሌክትሪክ ኃይልን ማባከን ወይም ስራዎች ላይ ጉዳት ማድረስ

ማናቸውም በቸልተኝነት ኤሌክትሪክ እንዲባክን የሚያደርግ ወይም መስመሩ እንዲቀየር ወይም በቸልተኝነት ማናቸውም ከኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ጋር የተገናኙ ማቴሪያሎችን የሚሰብር፣ የሚያበላሽ፣ የሚወረውር ወይም የሚጎዳ ግለሰብ በሚመለከተው አዋጅ መሰረት የሚቀጣ ይሆናል፡፡

## ሆን ተብሎ በተንኮል የሚደረግ ኤሌክትሪክ ኃይል ማባከን ወይም ስራዎችን የማበላሸት ድርጊት

ማናቸውም ኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን ለማቋረጥ በማሰብ የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲባክን ወይም ወደ ሌላ መስመር እንዲቀለበስ የሚያደርግ፣ ማናቸውንም የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት መስመር ወይም ስራ የሚቆርጥ፣ ወይም የሚያበላሽ፣ ለመቁረጥ ወይም ለማበላሸት የሚሞክር በሚመለከተው አዋጅ መሰረት የሚቀጣ ይሆናል፡፡

**የህዝብ መገልገያ መብራቶችን ማጥፋት**

ማናቸውም የህዝብ መገልገያ መብራቶችን ሆን ብሎ በተንኮል የሚያጠፋ ግለሰብ በዚህ አዋጅ በቀረቡ ዝርዝሮች መሰረት የሚቀጣ ይሆናል፡፡

**ተደራራቢ ጥፋቶች**

በዚህ የደንበኛ አገልግሎት ፖሊሲ እና አሰራር መሰረት ማናቸውም የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ወይም ግለሰብ የኤሌክትሪክ ስርቆት ጥፋት ማጥፋት የተረጋገጠ ወይም ተጠርጣሪ ለመሆን በቂ ምክንያት ካለ የሚመለከተው የመንግስት አካል ወይም ሃላፊ ርእሰ ጉዳዩን በተመለከተ በወጣው በአዋጅ ላይ በተጠቀሰው መሰረት የጥፋቶቹን ተደራራቢነት ከግምት በማስገባት ቅጣት የሚጥል ይሆናል፡፡

## 8.1 በኤሌክትሪክ ተጠቃሚዎች የተፈጸመ የኃይል ስርቆት ጉዳይ አያያዝና አመዘጋገብ

I. በዚህ መመሪያ ስልጣን የተሰጠው ሃላፊ የኤሌክትሪክ ኃይል ስርቆትን በተመለከተ በራሱ ተነሳሽነት ወይም አስተማማኝ መረጃ ሲደርሰው ወዲያውኑ ክስተቱ የተከሰተበትን ቅጥር ግቢ በጥንቃቄ እና በትጋት ምርመራ ያካሂዳል፡፡

II. የፈታሽ ቡድኑ ኃላፊ እና ሌሎች የቡድኑ፣ ማንነታቸውን የሚገልፅ መታወቂያ ወደ ቅጥር ግቢው ከመግባታቸው በፊት ለተጠቃሚው/ለደንበኛው ያሳያሉ፡፡

III. የተፈቀደለት ሃላፊ የተገናኘውን የኤሌክትሪክ መስመር ጭነት (ከደንበኛ በሚመጣ ጥያቄ መሰረት ከሚሰጡ የኃይል ጭነቶች በስተቀር) እንዲሁም እሽጎችን ወዘተ በተመለከተ ዝርዝር ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡ በተጨማሪም የቆጣሪዎችን ተግባር እንዲሁም የታዩ ከመደበኛ ውጪ የሆኑ ሁኔታዎች (ለምሳሌ ኃይል ለመስረቅ ጥቅም ላይ የዋሉ ሰው ሰራሽ ዘዴዎች) በአባሪ 6.4 ላይ በተቀመጠው ፎርማት መሰረት ዝርዝር ሪፖርት ያቀርባል፡፡

IV. ሪፖርቱ የኃይል ስርቆት መገኘት አለመገኘቱን የሚያረጋግጥ ድምዳሜ ላይ የደረሰ ማስረጃ መገኘቱን ወይም አለመገኘቱን ማሳየት ይኖርበታል፡፡ የእንደዚህ አይነት ማስረጃዎች ዝርዝር በሪፖርቱ መካተት ይኖርባቸዋል፡፡

V. የስርቆት ጥርጣሬ ካለ የተፈቀደለት ኃላፊ የማጭበርበር ድርጊት የተደረገበትን ቆጣሪ የማይነቅል ሲሆን ነገር ግን የኃይል አቅርቦትን በማቋረጥ ተገቢውን ንባብ የሚያሳይ አዲስ ቆጣሪ የሚተክል ይሆናል፡፡ ይህ ለመኖሪያ ቤት ለእርሻ እና የንግድ ተጠቃሚዎች ተፈፃሚ የሚሆን ነው፡፡ በዚህ ረገድ ኢ.ኤ.አ በቅጥር ግቢው ውስጥ የተገናኘውን ጭነት በማየት የማጭበርበር ተግባር በተከናወነበት ቆጣሪ ላይ ቁጥር የተሰጠው እና ህጋዊ እውቅና ባለው ወረቀት ያሽጋል፡፡ እንዲሁም በሪፖርቱ ላይ ይህን የተመለከተ ዝርዝር ያካትታል፡፡ የመ.መ/በከ.መ አቅርቦት በሚሆንበት ጊዜ በፎቶ ግራፍ/MRI የTBM ቆጣሪዎች ሪፖርት ወይም ማስረጃ በተጠቃሚው የተነሳ መሆኑን እርግጠኛ የሆነ ማስረጃ ከተገኘ የኤሌክትሪክ አቅርቦቱ ከሚመለከተው ኃላፊ በሚገኝ ፈቃድ የሚቋረጥ ይሆናል፡፡ ሆኖም አቤቱታ መስማቱና ምርመራው ከዚህ በታች በሚገለጸው ፕሮሲጀር መሰረት ይከናወናል፡፡

VI. ሪፖርቱ በሚመለከተው ስልጣን በተሰጠው ሃላፊ እና በፈታሽ ቡድኑ አባላት ከተፈረመ በኋላ ለተጠቃሚው ወይም ለተወካዩ ወዲያውኑ በቦታው የሚሰጠው ይሆናል፡፡ ተጠቃሚ ወይም ወኪሉ ሪፖርቱን ለመቀበል እምቢተኝነት የሚያሳዩ ከሆነ የፍተሻ ሪፖርቱ ቅጂ በሚታይ ቦታ በቅጥር ግቢው ውስጥ ወይም ውጪ ተለጥፎ ፎቶ ግራፍ ይነሳል፡፡ በተመሳሳይም ሪፖርቱ ለደንበኛው በተመዘገበ ፖስታ አድራሻ ወይም አስቸኳይ መልእክት ይላካል፡፡

VII. የኢ.ኤ.አ ፍተሻ በተደረገ በ3 ቀናት ውስጥ እንደዚህ አይነት የስርቆት ኬዝ በደንበኛው ላይ ለምን መመዝገብ እንዳለበት የሚያሳይ ምክያቱን የሚገልፅ ማስታወቂያ ይሰጣል፡፡ ማስታወቂያው ለተሰጠው ምላሽ የሚሰጥበትን ጊዜ፣ ቀን እና ቦታ እንዲሁም ምላሹ የሚቀርብለትን ኃላፊ መጥቀስ ይኖርበታል፡፡

## 8.2 የተከሰቱ ወይም ሪፖርት የቀረበባቸው አቤቱታዎች ስለመስማት

የተጠቃሚው ምላሽ በቀረበ በ4 የስራ ቀናት ውስጥ ምላሹ በተጠቀሰው ቀነ ገደብ የሚቀርብ ከሆነ ኢ.ኤ.አ ጉዳዩን ለመስማት ከደንበኛው ጋር ቀጠሮ ያመቻቻል፡፡

I. ጉዳዩን መስማት ከመጀመሩ በፊት ለዚህ የተሾመው የኢ.ኤ.አ የበላይ ሃላፊ ጉዳዩን ሁሉንም ሰነዶች፣ በደንበኛው የቀረቡ ምክንያቶችና ማስረጃዎች በመዝገብ የተያያዙ እውነታዎችን እንዲሁም አስፈላጊም ከሆነ የፍጆታ ሁኔታን የሚያሳዩ ማስረጃዎችን ከግምት ያስገባል፡፡ የኢ.ኤ.አ በአባሪ 6.3 ላይ በተጠቀሰው መሰረት ላለፉት ጊዜአት የነበረውን የኃይል አጠቃቀም ይመረምራል፡፡ ስርቆት እንደተፈፀመ ጥርጣሬ እንዳለ የቀረበበት ጉዳይ በተመለከተ ላለፉት አንድ አመት አማካኝ ወርሃዊ ፍጆታው ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ሲታይ ወጥ እና ከተመረመረው ወርሃዊ ፍጆታ 75% የማያንስ ከሆነ ሌላ ተጨማሪ ሂደት ሳያስፈልግ ለተጠቃሚው ተገቢ በሆነ ማስረጃ በ3 ቀናት ጊዜ ውስጥ ውሳኔው እንዲደርሰው ተደርጎ ተገቢው ምርመራ/መልሶ የማሸግ ተግባር ከተከናወነ በኋላ የኃይል አቅርቦት በአዲስ ቆጣሪ ይቀጠላል፡፡

II. ጉዳዩን በመስማት ሂደት ወቅት ኢ.ኤ.አ በተጠቃሚው የቀረበውን እውነታዎች ከግምት የሚያስገባ ሲሆን ጉዳዩን ከተመለከተ በኋላ በ15 ቀናት ውስጥ የተጠረጠረው ስርቆት መኖሩ መረጋገጥ ወይም አለመረጋገጡን ያሳውቃል፡፡ የደንበኛው ቅሬታ አቀራረብ የምርመራ ሪፖርት የፅሁፍ የምርመራ ሪፖርቱን መቀበል አለመቀበሉን ያቀርባል፡፡

III. የተጠረጠረው ስርቆት እንደሌለ ውሳኔ ከተሰጠ ሌላ ተጨማሪ ሂደት ሳያስፈልግ ኤሌክትሪክ መስመሩ በነባሩ ቆጣሪ አማካኝነት መልሶ እንዲገጠም ይደረጋል፡፡

IV. የኃይል ስርቆት እንዳለ ከተረጋገጠ በኢ.ኤ.አ በየጊዜው እያሻሻለ በሚያወጣው ኢንስፔክሽን ፖሊሲ እና ፕሮሲጀር በተቀመጠው የቅጣት መጠን የሚቀጡ ሆኖ ለሁለተኛ እና ሰስተኛ ጊዜ ጥፋት ለሚፈጽሙ ደንበኞች ለመጀመሪያ ጥፋት የተቀመጠውን ቅጣት በጥፋቱ ቁጥር ልክ በማባዛት የሚፈጸም ይሆናል፡፡ ሆኖም ለሶስተኛ ጊዜ ጥፋት የሚፈጽሙ ደንበኞች ተገቢውን ክፍያ ከከፈሉ በኋላም እንደ ተጨማሪ ቅጣት ለተከታታይ 10 ቀናት ኤሌክትሪክ እንዲቋረጥባቸው ይደረጋል፡፡ ለአራተኛ ጊዜ ጥፋት አጥፍቶ ሲገኝ ደንበኝነት ማቋረጥ እና በሀገሪቱ ባለው ህግ መሰረት ክስ የሚመሰረትባቸው ይሆናል፡፡

## 8.3 ውሳኔ የተሰጠበትን ክፍያ ወይም በጊዜ ገደብ የተሰጡ እዳዎች አለመክፈል፡፡

I. እንዲከፈል የተወሰነለትን መጠን ተጠቃሚው ሳይከፍል ሲቀር ኢ.ኤ.አ በፅሁፍ የ15 ቀናት ማስታወቂያ ከሰጠ በኋላ የኤሌክትሪክ ሀይሉን አቅርቦት በማቋረጥ ጉዳዩን በህግ ይጠይቃል፡፡

II. ኢ.ኤ.አ ስምምነት የደረሰበትን በጊዜ ገደብ በተለያየ ጊዜ ክፍያ እንዲከፈል(installement) በተወሰነው ውሳኔ መሰረት ተጠቃሚው የማይከፍል ከሆነ ኢ.ኤ.አ ማስታወቂያው በፅሁፍ ከተሰጠ ከ15 ቀናት በኋላ አስፈላጊ መረጃዎችን በመያዝ እና በማደራጀት የኤሌክትሪክ መስመሩን በማቋረጥ ተጠቃሚውን በሚመለከተው ፍ/ቤት ይከሳል፡፡ ቆጣሪው የሚቀጠለው የክስ ሂደቱ ከተቋጨ እና ደንበኛው ያለበትን ሂሳብ ከከፈለ በኃላ ነው፡፡

## 8.4 የማጭበርበር ተግባር የተከናወነባቸውን ቆጣሪዎች በፈቃደኝነት ስለማሳወቅ

አንድ ተጠቃሚው/ደንበኛ በፍቃደኝነት የሚጠቀምበት ቆጣሪ ላይ የማጭበርበር ተግባር መፈፀሙን ካሳወቀ

ሀ. ማጭበርበር የተከናወነበት ቆጣሪ የማይሰራ ከሆነ በደንበኛው/በኢ.ኤአ እንደ ጉዳዩ ሁኔታ በአዲስ ተተክቶ ለመኖሪያ እና ለእርሻ ተግባር ለሚያገለግሉ ቆጣሪዎች በስርቆቱ ምክንያት ያልተከፈለው የፍጆታ ሂሳብ እንዳለ ሆኖ በምርመራ ተገኝቶባቸው በዚህ ምክንያት ከሚቀጡ ደንበኞች በኢንስፔክሽን ፖሊሲና ፕሮሲጀር ከተቀመጠው ቅጣት 1/3ኛ በመቀነስ እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡ ለንግድ ተጠቃሚዎች የቅጣቱን 1/4ኛ በመቀነስ፣ ለዝቅተኛ ኢንዱስትሪዎች 1/5ኛ በመቀነስ እንዲሁም ለከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች 1/6ኛ በመቀነስ እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

ለ. ቆጣሪው ላልተቀየረበት ጊዜ ለሚከፈለው የኃይል ክፍያ በተበላሹ ቆሪዎች አሰራር መሰረት የሚሰላ ይሆናል፡፡

ሐ. ደንበኛው የተጭበረበረ ተግባር የተከናወነበትን ቆጣሪ በተመለከተ በፈቃደኝነት ካሳወቀ እና የተጠየቀውን ክፍያ በወቅቱ ከከፈለ ምንም አይነት ክስ በተጠቃሚው ላይ አይቀርብም፡፡

መ. ክፍያውን ተጠቃሚው የማይከፍል ከሆነ ደንበኛውን የመክሰስ ሂደት ተግባር ላይ ይውላል፡፡

### 8.5 ማጠቃለያ

የምርመራ ቢል ሲዘጋጅ ተጠቃሚው የከፈላቸው ሂሳቦች ተቀናሽ የሚደረግለት ሲሆን ክፍያው በግልፅ የሚከፈልበትን ጊዜ ቀንና ቦታ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 9. አጠቃላይ ዝርዝር ሁኔታዎች

### 9.1 ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች እና የኃይል አቅርቦት ላይ የተጣሉ ገደቦች

ኢ.ኤ.አ ተጠቃሚዎች ከሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ በአንዱ ኤሌክትሪክ አቅርቦትን ከመጠቀም እንዲታገዱ ወይም እንዲቆጠቡ ትእዛዝ ሊሰጥ የሚችል ሲሆን እነዚህን ሁኔታዎች ባለ መፈጸም ለሚደርሱ ኪሳራዎች ወይም ጉዳቶች ተጠያቂ አይሆንም፡፡

i. በአውሎንፋስ፣ ጎርፍ፣ ወጀብ ወይም ሌሎች ከድርጅቱ ቁጥጥር ውጪ በሆኑ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሚደርሱ የተፈጥሮ አደጋዎች፣ በጦርነት፣ በአድማ፣ በህዝብ አለመረጋጋት፣ አመፅ፣ በስራ ማቆም አድማ፣ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣ እሳት፣ መብረቅ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ ወይም ሌሎች እንደ መሳሪያ ብልሽት፣ ተንጠልጣይ መስመሮችና ኬብሎች፣ ሳይፈቀድ የተለቀቀ ከአቅም በላይ የሆነ የጭነት ፍጆታ ወይም ሌሎች ከኢ.ኤ.አ ቁጥጥር ውጪ በሆኑ ምክንያቶች

ii. በኢ.ኤ.አ በማናቸውም አዋጅ/የኢትዮጵያ መንግስት ህግ የተጣሉ የኃይል አቅርቦት ገደቦች በሚከሰቱበት ወቅት

iii. በኤሌክትሪክ መስመር ስርአት ውስጥ ከሚፈለገው መጠን በላይ የኤሌክትሪክ ኃይል ጭነት ሲከሰት ወይም በኢ.ኤ.አ እንደ ዋናው ማሰራጫ (ግሪድ) ብልሽት ሲገጥም እና ይህም ብልሽት የኤሌክትሪክ ኃይል ጭነቱ እንዲገደብ ሲደርግ

### 9.2 የኤሌክትሪክ ኃይልን በአግባቡ ስለመያዝ

የኤሌክትሪክ አጠቃቀም ብክነትን በተጠቃሚው በኩል (energy management) የማቆምና የመከላከል እንዲሁም ለኢ.ኤ.አ ወደ ፊት የሚጀመረውን በፍላጎት ላይ የተመሰረተ አመራር ትግበራ በሚጀመርበት ወቅት አስፈላጊውን ትብብር የማድረግ ኃላፊነት የእያንዳንዱ ተጠቃሚ ነው፡፡

## 9.3 ማስታወቂያዎችን ስለ መስጠት

ማናቸውም ለደንበኛ ወይም ለተጠቃሚው የሚሰጡ ማስታወቂዎች በአካል ለተጠቃሚው በኢ.ኤ.አ የሚመለከተው ሃላፊ በመስጠት ወይም በተመዘገበ ፖስታ በመላክ ወይም በእለታዊና በሰፊ ተነባቢ በሆኑ ጋዜጦች የሚወጣ ሲሆን ማስታወቂያውም በኢ.ኤ.አ ማህደር ይያዛል፡፡ ተጠቃሚው ግለሰብ ሲሆን ማስታወቂያው ለተጠቃሚው ህጋዊ ባለቤት ወይም ተወካይ እንዲሁም ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ ለዋና ሃላፊ ወይም ም/ሃላፊ ወይም ለሚመለከተው አካል የሚሰጥ ሲሆን ይህም በዚህ መመሪያ መሰረት ማስታወቂያው በበቂ ሁኔታ እንደተሰጠ ተደርጎ የሚያስወስድ ነው፡፡ የኢሜይል አገልግሎትም ከዚህ በተጨማሪ ከላይ የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው በተግባር ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡፡

ተጠቃሚው እነዚህን ማስታወቂዎች ከመቀበል የሚሸሽ ወይም አሻፈረኝ የሚል ከሆነ ማስታወቂያው ቅጥር ግቢ ላይ 2 ምስክሮች በተገኙበት የሚለጠፍ ወይም በአካባቢው በሚገኝ እና በሰፊው ተነባቢ በሆነ ማስታወቂያ የሚወጣ ሲሆን በዚህ ወቅት ግን በማስታወቂያው ላይ ማረጋገጫ መስፈር ይኖርበታል፡፡ ይህ ማስታወቂያ ለተጠቃሚው በበቂ ሁኔታ የደረሰ ማስታወቂያ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

## 9.4 አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የማስወገድ ስልጣን

1. ይህን መመሪያ በማስፈፀም ሂደት ወቅት ማናቸውም ችግሮች የሚያጋጥሙ ከሆነ ወይም የዚህን መመሪያ አተረጓጎም በተመለከተ አለመግባባት የሚመነጭ ከሆነ ኢ.ኤ.አ እንደዚህ አይነት አስቸጋሪ ሁኔታዎችን እና የአተረጓጎም አለመግባባቶች ለማስወገድ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፡፡
2. በዚህ መመሪያ አማርኛውና እንግሊዝኛው ሰነድ መካከል አለመጣጣም ቢኖር በአማርኛው ሰነድ ላይ የተዘረዘሩት ዝርዝሮችና ትርጓሜዎች ገዢ ይሆናሉ፡፡

## 9.5 ልዩ ልዩ

ሀ. በደንበኞች አገልግሎት ፖሊሲ መመሪያ መሰረት ኢ.ኤ.አ በየጊዜው የዚህን ደንብ አተገባበር እንዲሁም የተለያዩ ጉዳዮችን በተመለከተ ሊተገበሩ የሚገባቸው አሰራሮች መመሪያ ያወጣል፡፡

ለ. ኢ.ኤ.አ በማንኛውም ጊዜ ከመንግስት ፈቃድ ካገኘ በኋላ በደንበኞች አገልግሎት ፖሊሲ መመሪያን ሊጨምር፣ ሊቀይር፣ ሊያስተካክል ወይም ሊያሻሽል ይችላል፡፡

ሐ. በማንኛውም ጊዜ የዚህን ደንብ ዝርዝሮች በማስፈጸም ረገድ አስቸጋሪ ሁኔታዎች የሚፈጠሩ ከሆነ ኢ.ኤ.አ በአጠቃላይ እንዲሁም ልዩ በሆነ ትእዛዝ የይግባኝ ባለስልጣኑ ኢ.ኤ.አ ችግሮቹን ለማስወገድ አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነባቸውን እርምጃዎች እንዲወስድ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## 10. አባሪዎች